# መጽሐፍ ቅዱስን እናጥና

# ማውጫ


| ቁጥር | | ገጽ |
|---|---|---|
| | መቅድም | ፩ |
| ፩· | ኃጢአት | ፮ |
| ፪· | ንስሐ | ፰ |
| ፫· | እምነት | ፲፪ |
| ፬· | ማስተስሪያ | ፲፬ |
| ፭· | መ ስ ዋዕት | ፲፮ |
| ፮· | መዋጀት | ፲፰ |
| ፯· | ጽድቅ | ፳፩ |
| ፰· | ወንጌል | ፳፪ |
| ፱· | ይቅርታ | ፳፬ |
| ፲· | የዘላለም ሕይወት | ፳፭ |
| ፲፩· | ዳግመኛ መወለድ | ፳፯ |
| ፲፪· | እርግጠኛነት | ፳፱ |
| ፲፫· | መለየት | ፴፩ |
| ፲፬· | ቅድስና | ፴፫ |
| ፲፭· | አሸናፊው ሕይወትና የበረሃው ጉዞ | ፴፯ |
| ፲፮· | አሸናፊው ሕይወትና በፍጹም እራስን ማስረከብ | ፴፱ |
| ፲፯· | መንፈስ ቅዱስ | ፵፰ |
| ፲፰· | እግዚአብሔር | ፶፩ |
| ፲፱· | ክርስቶስ | ፶፬ |
| ፳· | ጸሎት | ፶፱ |
| ፳፩· | ሕግ | ፷፩ |
| ፳፪· | ጸጋ | ፷፪ |
| ፳፫· | ፈተና | ፷፮ |
| ፳፬· | የመሰቃየት ችግር | ፷፯ |
| ፳፭· | ጥርጥርና እየቀዘቀዙ የመሄድ ምክንያት | ፷፱ |
| ፳፮· | ሥጋ | ፸፩ |
| ፳፯· | ግብዝነት | ፸፫ |

ቁጥር


| | | |
|---|---|---|
| | | ገጽ |
| ፳፰· | መስጠት | ፸፬ |
| ፳፱· | መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር እስትንፋሳዊ ቃል | ፸፰ |
| ፴· | ሰይጣን | ፸፱ |
| ፴፩· | ሥጋዊ ሞት | ፹፩ |
| ፴፪· | መንፈሳዊ ሞት | ፹፫ |
| ፴፫· | ሥጋዊና መንፈሳዊ ፈውስ | ፹፭ |
| ፴፬· | እውነተኛይቱ ቤተ ክርስቲያን | ፹፰ |
| ፴፭· | ቅስና | ፺፪ |
| ፴፮· | ለውድቀት የሚያደርሱ መንገዶች | ፺፯ |
| ፴፯· | መጠጥ የሚያስከትለው ችግር | ፻፩ |
| ፴፰· | ጥምቀት | ፻፭ |
| ፴፱· | የጌታ እራት | ፻፲ |
| ፵· | ፍቅር | ፻፲፭ |
| ፵፩· | የወንጌላውያን ጥሪ | ፻፲፰ |
| ፵፪· | ዳግም ምፅዓት | ፻፳ |

# መቅድም ።

## የዛሬ መጽሐፍ ቅዱስ ።

መጽሐፍ ቅዱስ ያለ ጥርጥር ከመጻሕፍቶች ሁሉ በላይ የሆነ መጽሐፍ ነው ። ሆኖም በዚህ በፈጣኑ ክፍለ ዘመን ናቅ ባለ ሁናቴ ላይ ስለሚገኝ አስጊ በሆነ አቋም ላይ እንዳለ ይገመታል ።

የአሁኑም ዘመን ሰው በቅርብ አንብቦ ለማጥናት ያለው ጊዜ አጭር ነው ። ስለዚህ የመጽሐፉን ትምህርት ማቅለልና በፍጥነት ተነባቢ ማድረግ መልካም ነው ። እስቲ ስለዚህ ከመጽሐፍቶች ሁሉ በላይ ስለሆነው መጽ ሐፍ ታሪክ የሚያወሳ እርግጠኛ የሆነ ጥቂት ጉላ ብሎ የሚታየውን መግለጫ እንመልከት ። ምክንያቱም እግዚ አብሔር ከሰብአዊ ፍጥረቱ ጋር ያለውን ይዞታ ስለሚገ ልጽልን ነው ።

ይህ መጽሐፍ ፸፪ ጥቃቅን መጽሐፍቶችን አጠ ቃሎ የያዘ ሲሆን የነዚህ ሁሉ ገለጻና ግብ ክርስቶስና መዋጀቱ ነው ። ብሉይ ኪዳን ለመጀመሪያ ጊዜ በእብራ ይስጥ የተጻፈ ቢሆንም ጸሐፊዎቹ ሰዱቃውያን እንደሆ ኑና ግልባጩም በታላቅ ጥንቃቄ እንደ ነበረ በብዙዎቹ ዘንድ የተሰወረ አይደለም ።

ጌታ ከመወለዱ ከሦስት መቶ ዓመታት አስቀድሞ በግብፅ አገር ብሉይ ኪዳን ለመጀመሪያ ጊዜ ከእብራይ ስጥ ወደ ግሪክ ተተረጐመ ። ይህም ትርጉም እንደተር ጓሚዎቹ ብዛት ሰፕቱአጅንት ተብሎ ተጠራ ። (ሰፕቱአ ጅንት) በላቲን ቋንቋ ሰባ ማለት ነው ። ጀሮም የሚባል ሰው ከ፫፻፹፫ እስከ ፬፻፭ ዓ. ም. መጽሐፍ ቅዱስን በሙሉ ወደ ላቲን ተረጐመ ። ጽሑፉም (ቨልጌት ቨር ዥን) ተብሎ ተሰየመ ።

ይህም ትርጉም በመኻከላዊ ዘመን በአውሮፓ ለብዙ መቶ ዓመታት ከሕዝብ ተሰውሮ በቀሳውስት እጅ

ብቻ በመገኘት በላቲን ቋንቋ እየተነበበ ቆየ። ከዚህም በኋላ የአንዳንድ ሰዎች ለአንባቢው ሕዝብ በሚያመቸው በእንግሊዝኛ ቋንቋ መጽሐፍ ቅዱስን መተርጐም አንድ አስደናቂ የሆነ የታሪክ ምዕራፍ ከፍቶአል። ለዚህ አድ ራጐት በ፲፫፻፸፫ ዓ. ም. እንደ ዋና ሆኖ የመራው ዮሐ ንስ ዋይክሊፍ ይባላል።

ይኸው ሰው በቀሳውስት እጅ ብቻ ተወስኖ የቀረ ውን መጽሐፍ በሕዝቡ ቋንቋ ተርጉሞ ለሕዝቡ ስለ ገለጸ ተቃዋሚዎቹ ቅዱስ መጽሐፍ በአሳማዎች ተረገጠ ብለው ከተቹ በኋላ የሞት ፍርድ ፈርደው እንዲሞት አደረጉ።

ብዙዎችም ከዚህ መጽሐፍ የተነሳ በሰማዕትነት አርፈዋል። ከነዚህም በኋላ መጽሐፉን ወደ እንግሊዝኛ ተርጉሞ በመጨረሻ በ፲፭፻፳፰ ዓ. ም. በእሳት የመቃጠ ልን ፍርድ ተቀብሎ የሞተው መንፈሳዊ አርበኛ ቲንዴል ይባላል። ይህም በዚያን ጊዜ በተቃዋሚዎቹ ዘንድ እንደ ተረትና አጉል ባሕል ተገምቶ ቢታለፍም መንፈሳውያ ኖቹ አርበኞች በአድራጐታቸው ድሉን ተቀዳጅተው አልፈዋል። ወዲያው ከጥቂት ዓመታት በኋላ በ፲፭፻ ፴፩ ዓ. ም. ክሮምዌል የተባለው አገረ ገዢ መጽሐፍ ቅዱስ ሕዝቡ በሚያውቀው ቋንቋ ተተርጉሞ በየቤተ ክርስቲያኑ ሁሉ እንዲነበብ ክራንመር ለተባለው ጳጳስ ትዕዛዙን አስተላለፈ።

ሕዝቡም እንደ ትዕዛዙ መሠረት ይህንኑ መጽሐፍ የሚያነበው ከጠረጴዛ ጋር በሰንሰለት በመታሰር ነበር። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ እንግሊዝ መጽሐፍ ቅዱስ አጥታ አታውቅም። መቶኛው ዓመት ሊገበደድ አቅራቢያ ዓለም ታላቅ የወንጌላውያን መነቃቃት አይታለች። በዚ ህም የመነቃቃት ውጤት ዓለም በሬዲዮና በጽሑፍ አማ ካይነት የመጽሐፉን ታላቅ ዜና በትውልድ ቋንቋዋ እን ድትሰማ አድርጓታል። ከዚህም በቀር ይህ ዜና እስከ

ዓለም ዳርቻ ድረስ ዘልቋል ። ቢሆንም በዚህ የሰው ልጅ በጥበብ በተራመደበት ወቅት ሰይጣን የተለየ መንገድ በመውሰድ ዘመናዊው ሰው የመንፈሳዊነትን ነገር እንዳያስተውል ሕሊናውን አሳውሮታል ። ይኸውም በሥጋ አስተያየት ዘመናዊነት ጥርጥር ተሞልቶ መጽሐፉን በማክፋፋት ነው ። የዚህም ውጤት መጽሐፉ በአዋራ ተሸፍኖ በየመጽሐፍት ቤቱ መደርደሪያ ላይ እንዲቀመጥ አድርጎታል ። አልፎ አልፎ ለሚያነቡት አብዛኛዎቹ ሰዎች የተሰወረ አዲስ ቋንቋ ሆኖባቸዋል ። ይህ መጽሐፍ በያንዳንዱ ሰው ዘንድ ተገኝቶ ቢነበብ ሰላምን በእግዚአብሔርና በእርስ በርስ መኃል ሊፈጥር ይችላል ። የዓለም ሕዝቦች (የከሐዲዎችን) የወሬ ውሽንፍርና የዘልማድን ወግ በመከተል ላይ ይገኛሉ ። ነገር ግን እውነተኛውን ሰላም የሚሰጠው በመጽሐፍ ቅዱስ ገጽ የሚገኘው የምስራች መልዕክት ተዘንግቶአል ። ይህም መጽሐፍ በዘመናት እርዝማኔ መኃል ያለፉትን ትሑታን አንባቢዎች በሰላምና በመንፈስ ቅዱስ አጠንክሮአል ።

**ማብራሪያና ዕቅድ ያለው የመጽሐፍ ቅዱስ የንባብ ዘዴ ።**

ሀ) ትምህርቱ ። የትምህርቱ ዓይነት ኃጢአት ከሚለው ቅደም ተከተል አርእስት ጀምሮ ከብዙ የትምህርቱ ማብራሪያ ጥቅሶች ጋር ለአንባቢው ጉልህ ሆነው ሊታዩ በሚችሉበት መንገድ ተዘጋጅተው ቀርበዋል ። የትምህርቱ አርእስትና ገጽ ከያንዳንዱ ትምህርት በስተራስጌ ሲሰፍር ለየትምህርቱ መግለጫ ይሆን ዘንድ በቀላል አማርኛ ለያንያንዱ ትምህርት ማብራሪያ ተሰጥቶአል ።

ለ) የትምህርቱ ጉልህ ገለጻ ። ማንኛቸውም የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ከአጠቃላዩ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ውጭ ተነጥሎ በብቃት እራሱን ሊገልጽ አይችልም ። ይኸውም ከዘፍጥረት እስከ ዮሐንስ ራእይ ድረስ ያለውን ያጠቃልላል ማለት ነው ። በዚህ ዓይነት በእስኩፌልድ

መጽሐፍ አገላለጽ የትምህርቱ ጉልህ ገለጻ ይታያል ። የትምህርቱ ማብራሪያ ከአርዕስቱ የወጣ እንዳይሆን ይጠበቃል ። ብዙው ማብራሪያ የሚሰጠው ገለጻው አርዕስቱን ሊገልጽ እንዲችል በማድረግ ነው ።

ሐ) ተጨማሪ ማስገንዘቢያ ።

ማስገንዘቢያ ከአርዕስቱ መጨረሻ ሊታከልና ለጥቅሶችም ማስፈርያ ሥፈ ቦታ ሊኖር እንደሚያስፈልግ ሁሉ በተጨማሪም ለተማሪዎቹ የፊደል መሙያ ስፍራ ሊኖረው ይገባል ።

መ) የጸጥታ ጊዜ ትምህርትና የቤተ ሰብ ጸሎት ።

በየዕለቱ የጸጥታ ጊዜ በየአርዕስቱ ቢነበብ ከየጥቅሱ መልካም የሆነ ጠቃሚ ትምህርት ሊገኝ ይቻላል ። በዚህ ሁኔታ መጽሐፍ በቀላሉ ሊጠናና በማስተዋል ሊዘለቅ ይቻላል ። ለክፍል ትምህርትና ለመልዕክት ዝግጅት ይኸው ተመሳሳይ መምሪያ ይጠቅማል ። በዚህ ዓይነት መንገድ በወር ወይም ከወር በበለጠ ጊዜ የአንድ አርዕስት ትምህርት ሊሰራጭ ይችላል ።

ሠ) የጥቁር ሰሌዳ ጥቅም ።

በመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ ጊዜ አርዕስቱንና አንዳንድ ማብራሪያ ጥቅሶችን ለመጻፍያ ጥቁር ሰሌዳ አስፈላጊ ነው ። የትምህርቱ ተከታታዮች በትምህርቱ ጊዜ ደብተራቸውን ይዘው እንዲመጡ ማሳሰብ ይገባል ። መነታታት ከመጽሐፍ ቅዱስ አዳዲስ አርዕስተ ትምህርትና የጥናት ፍቅር ጋር ተያይዞ ይመጣል ።

ረ) የአንድነት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ።

የዚህን ዓይነት የጥናት ዘዴ ማወቅ በጣም ይጠቅማል ። መጽሐፍ ቅዱስ የጸጋ መንገድ መሆኑን አውቀን በፍጹም ልብ በምላካችን ፊት ተስተካክለን ብንቀበለው እርሱም ይቀበለናል ። ለተራቡት ይመግባቸዋል ። ለተጠሙት የሕይወት ውሃ ያጠጣቸዋል ። እየቀዘቀዙ

ለሚሄዱትም የእሳት ንዳድ ይጠብቃቸዋል ። ሆኖም አሁን በብዛት በልቅሶ ላይ ያለን ሁሉ ሴትም ሆነች ወንድ ስጦታውን ከእጁ ለመቀበል በአንድነት ወደ እርሱ እንቀርባለን ።

አንዱ ትምህርቱን እያዘጋጀ መምራት ሲኖርበት ሌሎቹም ደግሞ በልዩ መንገድ የሥራው ተከፋዮች ሊሆኑ ይችላሉ ። ይኸውም ጥቅስ በማንበብና ጥያቄ ዎችን በማቅረብ ሊሆን ይችላል ። ለፍርሃት ፣ ለተቃራኒ ነገርና ለበላይነት በርሱ ማዕድ ስፍራ የላቸውም ። ነፃነ ትና ፍቅር በሌለበት ቦታ ምክር የሚሰጠን ተራ መጽ ሐፍ አይደለም ። ቅዱስ ዮሐንስ በራእይ ፪ ፣ ፲፩ ፣ ፲፯ ፣ ፳፱ ደግሞ ፫ ፣ ፯ ፣ ፳፪ ላይ ጆሮ ያለው ሁሉ መንፈስ ቅዱስ የሚለውን ይስማ በማለት ተናግርአል ። መንፈስ ቅዱስን ያደመጡት ብቻ እርሱ ያለውን ሰሙ ። ሆኖም ጠቀላላው ዓለም ከመቅጽበት ከመጽሐፍ አንብቦ ሊረዳ ሲችል ከአንዳንድ የሃይማኖት ሊቆች ሊረዳ ይጥራል ። ዳሩ ግን የተጠየቀው የኢብያተ ክርስቲያን ሊቅ በመን ፈስ መሪነት እግዚአብሔር የማይጠቀምበት ከሆነ ሰሚዎ ቹን ከባሰ አዘቅት እንደሚጥላቸው አይካድም ።

ምክንያቱም መንፈሳዊ ተግባር በመንፈስ ቅዱስ ኃይል እንደሚሠራ መሪው እርግጠኛ ያልሆነ እንደሆነ ማለት ነው ። ስለዚህ መንፈሳዊን ነገር በሥጋ አስተሳሰ ብና ምርምር ለመረዳት አይቻልም ።

በመንፈሳዊ በኩል ያለውን ምስጢር ለመረዳት የሚችለው እራሱን በየዋህነት ላምላኩ ያስገዛ ሰው ከዘ መናዊው ጥበበኛ በላቀ ሁኔታ ሊረዳና ሊገለጽለት ይች ላል ተብሎ ይገመታል ። ይኸውም ሁለንተናውን ለክር ስቶስ በሙላት ያስረከበ እንደሆነ ነው ።

# ፩ኛ ። ኃጢአት ።

ኃጢአት ምንድር ነው ? ሰዎች በሦስት ታላላቅ መንገድ በምላካቸው ላይ የሚያደርጉት ተጻራሪነትና ጠላትነት ነው ። ይኸውም በሥራ በጠባይና በሁናቴ ነው ። እነዚህም እንደሚከተሉት ናቸው ። መስረቅ የኃጢአት ሥራ ነው ። ግብዝነት የኃጢአት ጠባይ ነው ። ሰው አለመዳኑ የኃጢአት ሁናቴ ነው ።

ስለዚህ ሰው በአካሉ ፥ በባሕርዩ ፥ በነፍሱ ፥ ከእግዚአብሔር የተለየ ሆኖ የሚኖር ነው ።

ኃጢአት የተጀመረበትን ወይም የኃጢአትን መነሻ የሚገልጽ መጽሐፍ ቅዱስ ብቻ ነው ።

ኃጢአት በዓለም ላይ መኖሩ የማይጠረጠር ነው ። የኃጢአትም ጨለማነት በቅዱስ መጽሐፍ ተገልጾ በሰው ሕይወት ሁሉ ይታያል ።

ዘፍጥረት ፪ ፥ ፲፯ ፤ ፫ ፥ ፩ - ፲፫ ፤ ፲፰ ፥ ፲፱ ፤ ፲፫ ፥ ፲፫ ፤ ዘኁልቁ ፴፪ ፥ ፳፫ ።
መዝሙር ፶ (፶፩) ፥ ፭ ።
ምሳሌ ፲፬ ፥ ፱ ።
ኢሳይያስ ፩ ፥ ፭ ፥ ፮ ፤ ፲፬ ፥ ፲፪ - ፲፬ ።
ማርቆስ ፯ ፥ ፳ ፥ ፳፫ ።
የሥራ ኃጢአት ፥ ገላትያ ፭ ፥ ፲፯ - ፳፩ ።
የጠባይ ኃጢአት ፥ ማቴዎስ ፭ ፥ ፳፩ ፥ ፳፪ ፥ ፳፰ ።
ማቴዎስ ፳፫ ፥ ፳፰ ።
መዝሙር ፳፭ (፳፮) ፥ ፲፰ ።
ሉቃስ ፲፰ ፥ ፲፩ - ፲፬ ።
ያዕቆብ ፪ ፥ ፰ ፥ ፱ ።
የሁናቴ ኃጢአት ፥ ዮሐንስ ፲፮ ፥ ፰ ፥ ፱ ።
ያዕቆብ ፬ ፥ ፲፯ ።
ሮሜ ፯ ፥ ፳ ፤ ሮሜ ፰ ፥ ፳፱ ።

፩ኛ ቆሮንቶስ ፲፭ ፡ ፳፩ ፣ ፳፪ ።
ገላትያ ፫ ፡ ፳፪ ።
፩ኛ ዮሐንስ ፩ ፣ ፮ ፡ ፯ ፤ ፫ ፣ ፬ ፡ ፯
፰ ፣ ፲፯ ፡ ፲፱ ።

<u>የኃጢአት በዓለም ሁሉ መኖር ።</u> በተፈጥሮአችን በኃጢአት ተወለድን ። ኃጢአት እያንዳንዱ ሰብዓዊ ፍጥረት በሕይወቱ ይዞት የመጣ ተፈጥሮው ሲሆን ዳግመኛ በተወለዱት ሰዎች ላይ እንኳን አልፎ አልፎ ይታያል ። ኃጢአት ሊወገድና በየጊዜውም ወደ ጌታ ሊቀርብ የሚገባ ከመሆኑ በላይ በመርዘኛ የሥጋ ደዌ የሚመሰል የተፈጥሮ በሽታን ይመስላል ። (ዮሐ· ፲፫ ፣ ፲) ኃጢአት ወርዶ ሊቀበር እንደሚገባውና እንደተቀበረ በሰው ትከሻ ላይ የተጫነን ከባድ ሸክም ይመስላል ። ኃጢአት የሌለበት ክርስቶስ ብቻ ነው ።

ሮሜ ፫ ፣ ፱ ፡ ፳፫ ፤ ፭ ፣ ፲፪ ፤ ፯ ፣ ፳፬ ፣ ፳፭ ።
የሐዋርያት ሥራ ፲፯ ፣ ፳፯ ።
ኤፌሶን ፪ ፣ ፩ - ፫ ።
ዕብራውያን ፬ ፣ ፲፭ ።
፩ኛ ዮሐንስ ፫ ፣ ፭ ።
፩ኛ ጴጥሮስ ፪ ፣ ፳፪ ።
ዘፍጥረት ፫ ፣ ፯ - ፲ ፣ ፳፫ ፡ ፳፬ ፤ ፯ ፣ ፯ ።
ኢሳይያስ ፶፫ ፣ ፳፪ ።
ኢያሱ ፯ ፣ ፲ - ፲፪ ፣ ፳፭ ፣ ፳፯ ።

ከአዳም ጊዜ ጀምሮ እግዚአብሔር የምንድንበትን መንገድ አዘጋጅቷል ።

ሰውዬው ከልቡ ኃጢአቱን ተናዞ ካቀረበ የሚታረደው እንስሳ ደም የኃጢአቱን ስርየት ያስገኝለታል ። ሆኖም ከዕለታት አንድ ቀን እግዚአብሔር እራሱ በሰው ልጅ አምሳል መጥቶ በፈቃዱ ለዓለም ኃጢአት አንዴ ለሁሉ ሞተ ። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ በርሱና ከርሱ ስለ ኃጢአታችን በፈሰሰው ደም በማመን ከዳግመኛ ሞት

ይኸውም ለዘለዓለም ከእግዚአብሔር ከመለየት ድነናል ።

ሕዝቅኤል ፲፰ ፥ ፬ ፥ ፳ ።
ኢሳይያስ ፩ ፥ ፲፫ ፥ ፲፰ ።
የሐዋርያት ሥራ ፬ ፥ ፲፪ ፤ ፲፫ ፥ ፴፰ ።
ዕብራውያን ፱ ፥ ፳፯ - ፳፰ ።
፩ኛ ዮሐንስ ፩ ፥ ፯ ።
ሮሜ ፭ ፥ ፲፱ ፤ ፯ ፥ ፲፩ ፥ ፲፪ ፥ ፳፫ ።
፪ኛ ቆሮንቶስ ፭ ፥ ፲፬ ፥ ፳፩ ።
ማቴዎስ ፲፩ ፥ ፳፰ ።
ዮሐንስ ፩ ፥ ፳፱ ።

## ፪ኛ ። ንስሐ ።

እውነተኛ ንስሐ መግባት የተባለው ወትሮ በኃጢአት የተጨማለቀውን ጠባይ ለውጦ በንጹህ ሕሊና በእግዚአብሔር ፊት መገኘት ማለት ነው ። ስለ ኃጢአት ማዘን በልብ አሳብና አእምሮ መለወጥ ነው ። በጠባይና በአእምሮ በሥራ ሁሉ ተለውጦ ካልተገኙ መጸጸት ብቻ (በራሱ) እርግጠኛ ንስሐ ነው ለማለት አይቻልም ።

ማቴዎስ ፳፩ ፥ ፳፰ - ፴፩ ፤ ፳፯ ፥ ፫ - ፭ ።
ሉቃስ ፲፭ ፥ ፲፯ ፥ ፲፰ ፥ ፳ ።
፪ኛ ሳሙኤል ፲፪ ፥ ፲፫ - ፲፰ ።
መዝሙር ፶ (፶፩) ፥ ፲ ።
የሐዋርያት ሥራ ፰ ፥ ፳፩ ፥ ፳፪ ።
፪ኛ ቆሮንቶስ ፯ ፥ ፱ ፥ ፲ ።
ሉቃስ ፲፭ ፥ ፯ ።

ንስሐ ሁለተኛ መወለድን መቅደም አለበት ። ይህም ደግሞ በዓለም ሁሉ መሰበክ አለበት ። ይኸውም አንድ ሰው በእምነት ወደ ዘለዓለም ሕይወት መጥቶ መግቢያውን በር የሚከፍትበት ቁልፍ ነው ።

የሚያድንን እምነት ያለ ንስሐ ማግኘት ዘበት ነው ።

ማቴዎስ ፫ ፥ ፪ ፡ ፰ ፤ ፬ ፥ ፲፯ ፤ ፱ ፥ ፲፫ ።
ሉቃስ ፳፬ ፥ ፵፯ ፥ ፵፰ ።
የሐዋርያት ሥራ ፲፯ ፥ ፴ ፤ ፭ ፥ ፴–፴፩ ፤
፳፮ ፥ ፲፱ ፥ ፳ ።

ንስሐ ለመግባት ፈቃደኛ አለመሆን ሰውን ያሳውራል ። በመጨረሻውም ሕሊናን ያፈዛል ።

ማቴዎስ ፳፩ ፥ ፳፰ ፥ ፴ ፥ ፴፪ ።
ኢሳይያስ ፩ ፥ ፲፫ - ፳፰ ።
ሉቃስ ፲፫ ፥ ፫ ።
፩ኛ ዮሐንስ ፩ ፥ ፮ ፥ ፰ ፥ ፲ ።
ዕብራውያን ፮ ፡ ፮ ።

እግዚአብሔር እየደጋገመ ንስሐ የማይገባውን ሰው ያስጠነቅቀዋል ። ነገር ግን እጆቹም እርሱን ለመቀበል የተዘረጉ ናቸው ።

ሕዝቅኤል ፲፰ ፥ ፴፩ ፥ ፴፪ ።
ራእይ ፪ ፥ ፭ ፤ ፲፮ ፥ ፳፩ ፤ ፫ ፥ ፫ ፥ ፲፱ ።
፪ኛ ቆሮንቶስ ፯ ፥ ፱ ፤ ፲ ፥ ፪ ።
ሮሜ ፪ ፥ ፬ ።
ሉቃስ ፲፭ ፥ ፯ ፥ ፲ ።

## ማስገንዘቢያ ።

### የሸንጎ መኃል ኑዛዜ ።

ለክርስቲያን በሸንጎ መኃል ኑዛዜ አስፈላጊ ነውን ? ይህ በክርስቲያን የመነቃቃት ጊዜ ተከታትሎ የሚቀርብ ጥያቄ ነው ።

ሰዎች ኃጢአታቸው በመንፈስ ቅዱስ ሲገለጽላቸው እንዳይገልጹት ሊገታቸው ማንም አይችልም ። የመንፈስን እንቅስቃሴ በአግባብ ለመምራት ታላቅ ጥንቃቄ መውሰድ ያስፈልጋል ።

በጠቀላላው በዚህ እንቅስቃሴ ወቅት በግልጽ በሸንጎ መኃል ለጌታ የተደበቀውን ኃጢአት መናዘዝ ከዚሁ

ጋር ተያይዞ ይፈጸማል ። ይህም የበረከት ጉርፍ ሲሆን ለመባረክ ልባችንን እንከፈትለት ። በሌላው በኩል ደግሞ በኤፌሶን ፭ ፥ ፲፪ እንደምናነበው እንደ ፍትወት ያለውን አሳፋሪ ኑዛዜ በሸንጎ ውስጥ መናገር ለብዙዎች እንቅፋት ስለሚሆን ከጥቅሙ ጉዳቱ ያመዝናል ።

እንደዚህ ያሉ ኑዛዜዎች በሚነሱበት ጊዜ ከፍ ያለ ጥንቃቄ መውሰድ ያስፈልጋል ። ጳውሎስ እንኳን በልሳን የመናገር መምሪያ ከመስጠት አልበዘነም ።(፩ኛ ቆሮንቶስ ፲፬ ፥ ፳፯ - ፴፫) ግልጽ የሆነ የሸንጎ ውስጥ ኑዛዜ ሁልጊዜ ጠቃሚ አይደለም ።

መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ሸንጎ ውስጥ ኑዛዜ ምን ያስተምረናል ?

ሀ) ኑዛዜ ወደ እግዚአብሔር ነው ። በሰው ፊት ሆነ ለብቻ ትክክለኛው ኑዛዜ የሚታወቀው ሰውዬው ለእግዚአብሔር በተናዘዘ ጊዜ ነው ። ይኸውም አምላኩን መበደሉ እንደታወቀው ያስረዳል ።

«መተላለፌን ለጌታ እናዘዛለሁ ።» (መዝሙር ፴፩ (፴፪) ፥ ፭)

«አንተን ብቻ በደልኩ በፊትህም ክፉትን አደረግሁ ።» (መዝሙር ፶ (፶፩) ፥ ፬)

«የክርስቶስ ደም ብቻ ከኃጢአት ሁሉ እንደሚያነጻ የታወቀ ነው ።» (፩ኛ ዮሐንስ ፩ ፥ ፯)

«በተሰበረና በተዋረደ ልበና መናዘዝ ያስፈልጋል ።» (መዝሙር ፶ (፶፩) ፥ ፲፯)

ለ) ኑዛዜ ተገቢ ነው ። ሆኖም በሸንጎ ውስጥ አስፈላጊ አይደለም ። (፩ኛ ዮሐንስ ፩ ፥ ፱)

መነቃቃት ባልተናዘዙት ኃጢአት ይታገዳል ። ኢያሱ አካንን ያልተገለጸ ኃጢአቱን እንዲናዘዝ አጥብቆ ጠየቀው ። (ኢያሱ ፯ ፥ ፲፱) ኑዛዜ እስኪደረግ ድረስ ድል መሆን የተረጋገጠ ነው ። ይህም ሁልጊዜ ከእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ጋር ያለ ነው ። ኑዛዜ ከክህደት

ጋር የተጣመረ መሆን አለበት ። (ምሳሌ ፳፰ ፥ ፲፫)

ሐ) <u>ለተበደለው ተናዘ ይቅርታ መጠየቅ ።</u> እግዚአብሔር ለእስራኤላውያን እንደሚከተለው መምሪያ ሰጣቸው ።

አንድ ሰው ሴትም ሆነች ወንድ ኃጢአት ቢሠራና ወንጀለኛ ቢሆን ኃጢአቱን መናዘዝ አለበት ። ስለ አደረገውም ኃጢአት (በደል) ለእግዚአብሔር መስዋዕት ያቅርብ ። ከአምስት አንድ ጨምሮ ወስዶ ለተበዳዩ ይስጥ ። (ዘኁልቁ ፭ ፥ ፮ ፥ ፯)

ያዕቆብ በመልእክቱ ኃጢአታችሁን እርስ በርሳችሁ ተናዘዙ ይላል ። (ያዕቆብ ፭ ፥ ፲፮) ክርስቶስ እንዳለው በግልጽ ንስሐ መግባት የሚፈልግ ሰው ወደ ክርስቶስ ከመቅረቡ በፊት አንዳች ከሰው በግፍ የወሰደው ነገር እንዳለ መመለስ እንዳለበት ያስረዳል ። እንግዲህ መባህን በመሠዊያው ላይ ብታቀርብ ፥ በዚያም ወንድምህ አንዳች በአንተ ላይ እንዳለው ብታስብ ፥ በዚያ በመሠዊያው ፊት መባህን ትተህ ሂድ ፥ አስቀድመህም ከወንድምህ ጋር ታረቅ በኋላም መጥተህ መባህን አቅርብ ። (ማቴዎስ ፭ ፥ ፳፫ ፥ ፳፬)

ይህም የሚያመለክተው ተበዳዩ ሰው ግፍ እንደተዋለበት የሚያረጋግጥበት መንገድ ነው ። መበደሉን ካላወቀ ግን ሂዶ የተደረገበትን መናገር ሰውዬውን በበለጠ መጉዳት ነው ። ልምምድ ካላቸው ክርስቲያኖች ጋር መነጋገር የሚከተሉትን ዓይነት ጥያቄዎች ለመጠየቅ ይረዳል ።

ኃጢአትን ገልጾ መወያየት ኃጢአትን ማስወገጃ ዘዴ ሊያስገኝልን ይችል ይሆናል ። ነገር ግን ሁልጊዜ መወያየት እውነተኛው መናዘዝ አይደለም ። ይኸውም ልክ በየጊዜው ለቄስ እንደመናዘዝ ዓይነት ነው ።

ይህም ጥሩ አይደለም ።

መ) <u>በስብሰባ መናዘዝ</u>፡፡ ይህ ኑዛዜ ስብሰባው እየሰማ ለእግዚአብሔር መሆን አለበት። የታወቀው ክርስቲያን በይፋ ኑዛዜ መልካም መስሎ እየታየው ለሌሎቹ እን ቅፋት ይሆናል። ኢያሱ በሰዎች መኃል አካን እንዲ ናዘዝ ፈልጎ የግድ በማለት ልጄ ሆይ፤ ለእስራኤል አም ላክ ለእግዚአብሔር ክብር ስጥ፤ ለእርሱም ተናዘዝ፤ ያደ ረከውንም ንገረኝ፤ አትሸሽገኝ አለው። (ኢያሱ ፯፡ ፲፱)

ሠ) <u>ስሕተት በሆነ መንገድ መናዘዝ</u>፡፡ እንደሚከተለው ዓይነት ንስሐ ስሕተት ነው።

፩. ክርስቶስ በመስቀል ላይ ኃጢአታችንን ከላስወ ገደልን በቀር ኑዛዜ በማድረጋችን እንጸድቃለን ብሎ ተስፋ ማድረግ ስሕተት ነው።

፪. ንስሐ በመግባት ከሌሎች ክርስቲያኖች ዝናን ለማግኘት መሞከር ስሕተት ነው።

፫. የሌሎቹን ክርስቲያኖች ምሳሌ ለመቅሰም ብቻ ቢያደርግ ትክክል አይደለም።

፬. የታወቀ ሰው እንዲሆን እራሱን ለማሳየት ይህን ቢያደርግ ስሕተት ነው።

፭. በልብ የተሰወረውን ኃጢአት በስብሰባ መሐል ስለአልተናዘዘ ከጉባኤው ጋር ያለው አንድነት እንደተቋ ረጠ አድርጎ ማሰብ ስሕተት ነው።

እኛ ደግሞ በስብሰባ መሐል ሌሎች የሚያደርጉ ትን ስሕተት ከማጋነን መጠንቀቅ አለብን። ከዚህም በቀር በስብሰባ መሐል ያልመሰከረውን ደግሞ እውነተኛ አማኝ እንዳልሆነ አድርገን ከመገመት እንጠንቀቅ።

## <u>፫ኛ። እምነት ።</u>

እምነት ፍጹም የተረጋገጠ በእግዚአብሔር ላይ ያለን ምኬትና ቃል ኪዳኑን በቃሉ ፈጽሞ የተሰጠንን ኢየሱስ ክርስቶስን አዳኝና ጌታ ማድረግ ነው።

እምነት የማይታየውን ግልጽ ያደርገዋል ። (ዕብ. ፲፩ ፥ ፩) ይህም የእውነተኛ ክርስቲያን የዘወትር ጠባይ ነው ። በብሉይ ኪዳን ዘመን ደጎንነት ብዙ ጊዜ በሥዕላዊ ምሳሌ ተገልጸአል ። እንዲሁም ደግሞ በዚያን ጊዜ የነበሩ ቅዱሳን በተደጋገመው በእግዚአብሔር ተስፋና ኪዳን ጽኑ እምነት ነበራቸው ።

ዘፍጥረት ፮ ፥ ፳፪ ፤ ፲፪ ፥ ፩ - ፭ ፤
፲፫ ፥ ፲፬ - ፲፯ ።
ዕብራውያን ፲፩ ፥ ፯ - ፲ ።
ዘፍጥረት ፳፪ ፥ ፩ - ፲፱ ።
ዕብራውያን ፲፩ ፥ ፲፯ - ፲፱ ።
ዘፍጥረት ፶ ፥ ፳፬ ፡ ፳፭ ።
ዕብራውያን ፲፩ ፥ ፳፪ ።
ዘፀአት ፱ ፥ ፳ ፡ ፳፩ ፤ ፲፪ ፥ ፳፩ - ፳፭ ።
ዕብራውያን ፲፩ ፥ ፳፰ ።
ኢያሱ ፮ ፥ ፳ ።
ዕብራውያን ፲፩ ፥ ፴ ።
ሩት ፪ ፥ ፲፪ ።
መዝሙር ፺፭ (፺፮) ፥ ፫ ።

በአዲስ ኪዳን ክርስቶስ የብሉይ ኪዳን መፈጸሚያ ተስፋ ስለሆነ እምነት በርሱ መሆን አለበት ተብሎ ተወሰነ ።

ማቴዎስ ፲፯ ፥ ፳ ።
ማርቆስ ፮ ፥ ፭ ፡ ፮ ፤ ፱ ፥ ፳፫ ፤ ፲ ፥ ፶፪ ።
ሉቃስ ፯ ፥ ፱ ፤ ፰ ፥ ፶ ፤ ፲፯ ፥ ፭ ፡ ፮ ፤ ፳፪ ፥ ፴፪
ዮሐንስ ፩ ፥ ፲፪ ፤ ፫ ፥ ፲፭ ፡ ፲፮ ፡ ፴፮ ፤
፮ ፥ ፴፭ ፡ ፴፮ ፤ ፯ ፥ ፴፰ ፤ ፲ ፥ ፳፰ ፤ ፲፩ ፥
፳፭ ፡ ፳፮ ፤ ፲፪ ፥ ፵፮ ።

ሐዋርያት በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ እመን የምትለውን መልእክት ይዘው ወደ ዓለም ወጡ ።

የሐዋርያት ሥራ ፫ ፥ ፲፮ ፤ ፬ ፥ ፲፪ ፤ ፳ ፥ ፳፩ ፥
፴፩ ፤ ፲ ፥ ፵፫ ።
ሮሜ ፫ ፥ ፳፭ ፥ ፳፪ ፤ ፭ ፥ ፩ ፥ ፪ ፤ ፲ ፥ ፱ ፥ ፲ ።
፩ኛ ቆሮንቶስ ፩ ፥ ፳፫ ፤ ፪ ፥ ፪ ።
፪ኛ ቆሮንቶስ ፬ ፥ ፭ ።
ገላትያ ፪ ፥ ፲፭ ፥ ፲፮ ፥ ፳ ፤ ፫ ፥ ፳፪ ።
፪ኛ ተሰሎንቄ ፩ ፥ ፫ ።
፩ኛ ጴጥሮስ ፩ ፥ ፲ ፥ ፳፩ ፤ ፪ ፥ ፯ ።

በእምነት ድነናል ። ነገር ግን የእምነታችን ፍሬ በሥራችን ይገለጻል ። እምነት ከራሳችን እንደተገኘ ነገር የምንኰራበት ሳይሆን ከአምላካችን እጅን በመዘርጋት ብቻ የምንቀበለው የደኅንነት ስጦታ ነው ።

ሮሜ ፬ ፥ ፩ - ፭ ፤ ፲ ፥ ፱ ፥ ፲ ።
ያዕቆብ ፪ ፥ ፲፬ ፥ ፲፯ ፥ ፳፬ ።
ቲቶ ፫ ፥ ፬ - ፰ ።
ገላትያ ፪ ፥ ፳፮ ።
ኤፌሶን ፪ ፥ ፰ - ፲ ።
ራእይ ፮ ፥ ፲፮ ።
፩ኛ ጢሞቴዎስ ፮ ፥ ፲፪ ።
፩ኛ ዮሐንስ ፭ ፥ ፬ ።

<u>የመጽሐፍ ቅዱስ አስተዋጽኦ</u> ፥ በእምነት ያለፉና ያሉ እንደደመና የከበቡንን ምስክሮች እንመልከት ።

ዕብራውያን ፲፪ ፥ ፩ ፥ ፪ ። ያለውን ከዕብራውያን ምዕራፍ ፲፩ ጋር አስተያይ ።

## ፬ኛ ። ማስተስሪያ ።

ማስተስሪያ በዕብራይስጥ ድርሰታዊ ቃሉ (ካፓር ይባላል ።) የዚሁም ቃል ትርጉም መሸፈን ማለት ነው ። ማስተስሪያ የተባለው ቃል «ካፓር» ከሚባለው ከዕብራይስጥ ብሉይ ኪዳን የተተረጐመ ነው ። ይኸውም ተሸ

ፈን ማለት ነው ። ይህ የሚያመለክተን ኀጢአተኛው በቀረበው የመስዋዕት ደም ኀጢአቱ እንደተሸፈነና ከእግዚአብሔር ጋር አንድነትን እንዳገኘ ማረጋገጫ ነው ። አሁን ግን በመንፈሳዊ ትምህርቱ እንደምንረዳው ማስተስረያ የሚለው ቃል በክርስቶስ ደም ያገኘነውን የኀጢአት ስርየትና መዋጀት ያጠቃልላል ። በአዲስ ኪዳን ይህ ቃል አንድ ጊዜ ብቻ ሲጠቀስ ማስታረቂያነቱን በመግለጽ ነው ። ሮሜ ፭ ፡ ፲፩ ። (በ፰ኛው ቁጥር መስዋዕት የሚለውንና በ፲ተኛው ቁጥር መዋጀት የሚለውን ማብራሪያ ተመልከት ።)

በብሉይ ኪዳን ዘመን እግዚአብሔር ወደፊት በክርስቶስ መስቀል የሚፈጸመውን የኀጢአት ስርየት አስተውሎ ኀጢአትን ይሸፍን ነበር ።

ከልቡ በኀጢአቱ ይናዘዝ የነበረው ሰው በደል የሌለበትን እንስሳ ይሰዋ ነበር ። ይህንንም የሚያደርገው በቀረበው እንስሳ ደም የራሱ ኀጢአት እንደሚነፃለት እግዚአብሔር የሰጠውን ተስፋ እንደሚያሟላ ባለመጠራጠር ነው ።

ዘጸአት ፴ ፡ ፲ ።
ዕብራውያን ፲ ፡ ፬ ።
ዘሌዋውያን ፩ ፡ ፫ ፡ ፬ ፤ ፬ ፡ ፳፯ - ፴፩ ፤ ፲፮ ፡
ፍ፲፮ ፡ ፲፯ ፡ ፴ ፤ ፲፯ ፡ ፲፩ ፤ ፳፫ ፡ ፳፯ ።

የእንስሳት መስዋዕት ክርስቶስ መጥቶ ሊፈጽመው ላለው ትክክለኛ መስዋዕት ጥላ ነበር ።

ዕብራውያን ፲ ፡ ፩ ።
ዮሐንስ ፩ ፡ ፳፱ ።
፩ኛ ዮሐንስ ፪ ፡ ፪ ።
ዕብራውያን ፱ ፡ ፲፫ - ፲፰ ፡ ፳፪ ፡ ፳፮ ፤
፲ ፡ ፲ ፡ ፲፬ ።

ሮሜ ፫ ፥ ፳፭ ፤ ፲ ፥ ፫ ።
፩ኛ ቆሮንቶስ ፭ ፥ ፯ ።

አሁን ግን ከጸጋ በታች ነን ። ኃጢአታችንን በመናዘዝና ለኛ በፈሰሰው በክርስቶስ ደም በማመን ከእግዚአብሔር ጋር ታርቀናል ። ማስተስሪያ ተደረገልን ፤ ደሙም የዓለም መዋጃ ዋጋ ነው ። የኢየሱስ ክርስቶስ ሞት ከዓለም ታሪኮች መኃል እጅግ በጣም የላቀ ነው ።

ማርቆስ ፲ ፥ ፵፭ ።
ዮሐንስ ፲ ፥ ፲፩ ።
ሮሜ ፫ ፥ ፳፩ - ፳፭ ፤ ፭ ፥ ፲ ፥ ፲፩ ።
፪ኛ ቆሮንቶስ ፭ ፥ ፳፩ ።
ኤፌሶን ፩ ፥ ፯ ።
፩ኛ ጴጥሮስ ፩ ፥ ፲፰ ፥ ፲፱ ።
፩ኛ ዮሐንስ ፬ ፥ ፲ ።

<u>ማስገንዘቢያ ።</u>

ምትክ ፥ የክርስቶስ ሞት ለሰው ልጆች ምትክ ነበር ። ዕብራውያን ፪ ፥ ፲፬ - ፲፯ ። እርሱም ፍጹም ሰው ሳለ ለሰው ልጆች ምትክ በመሆን ሞተላቸው ። ኢሳይያስ ፶፫ ፥ ፭ ፥ ፮ ፤ ፩ኛ ጴጥሮስ ፪ ፥ ፳፬ ።

## ፫ኛ ። መስዋዕት ።

መስዋዕት በቀድሞ አስተሳሰብ በየግል ሰብአዊ ወንጀል የሚደረግ የንጹሕ እንስሳ መስዋዕት ነው ። ይህ መስዋዕት ገና ክርስቶስ ሊፈጽመው ካለው መስዋዕት ጋር የተጣመረ እግዚአብሔር ተመልክቶት በክርስቶስ ሞት ላይ ያጠናቀቀው ነው ። በብሉይ ኪዳን በእግዚአብሔር ትዕዛዝ የቆመው እውነተኛ መስዋዕት ለእርግጠኛው ክርስቶስ ላደረገው መስዋዕት ጥላ ነው ። ነገር ግን የተናቀው የቃየን መስዋዕት ዓለም ለጣዖት ከሚሰዋው መስ

ዋዕት ጋርና ከግብረገባዊ አለመታዘዝ ጋር ይመሳሰላል ።

ዘፍጥረት ፬ ፡ ፫ ፡ ፭ ፤ ፰ ፡ ፳ ፤ ፳፪ ፡ ፰ ፡ ፲፫ ፤
፴፩ ፡ ፶፬ ፤ ፵፮ ፡ ፩ ።
ዘጸአት ፲፰ ፡ ፲፪ ፤ ፲፪ ፡ ፫ - ፲፫ ።
ዘሌዋውያን ፩ ፡ ፪ ፡ ፫ ፤ ፬ ፡ ፲፮ ።
ዘዳግም ፴፪ ፡ ፲፮ ፡ ፲፯ ።
፩ኛ ሳሙኤል ፲፭ ፡ ፳፪ ።
ምሳሌ ፲፯ ፡ ፩ ።
ዕብራውያን ፲፩ ፡ ፬ ፤ ፲ ፡ ፩ ።
፩ኛ ቆሮንቶስ ፲ ፡ ፳ ።

ከሕግ በታች ለነበረው ማስተስሪያ ሁለት ጠቃሚ ነገር ያስፈልገው ነበር ። አንደኛ በሚደረገው የደም መስዋዕት እምነት ። (ዕብራውያን ፲፩ ፡ ፳፰ ፤ ዘኁልቁ ፭ ፡ ፯ ።) ከመስዋዕቱ ሥነ ሥርዓት ውስጥ ጠቃሚ ሆኖ የሚታየው የመታጠብ ሥነ ሥርዓት ሲሆን አሁን ለምና ደርገው ክርስቲያናዊ ጥምቀት ማመሳከሪያ መግለጫ የሆነ ከኃጢአት እድፊት መታጠባችንን የሚያሳይ ነው ። ዘሌዋውያን ፲፬ ፡ ፰ ፡ ፱ ፤ ዘኁልቁ ፲፱ ፡ ፲፫ ፤ ፰ ፡ ፯ ።

የአዲስ ኪዳን ዘመን በዮሐንስ የድል ድምፅ ጩኸት ተከፈተ ። «እነሆ የእግዚአብሔር በግ !» መጽሐፍ ቅዱስም በዮሐንስ ራእይ ከዓለም መጀመሪያ ለታረደው በግ ክብር እየሰጠ ተፈጸመ ።

ዮሐንስ ፩ ፡ ፳፱ ፤ ፫ ፡ ፲፮ ።
፩ኛ ቆሮንቶስ ፭ ፡ ፯ ።
ዕብራውያን ፱ ፡ ፲፫ ፡ ፲፬ ።
የዮሐንስ ራእይ ፲፫ ፡ ፰ ።

የክርስቶስ መስዋዕትነት ለዓለም ጠቅላላ ኃጢአት ነው ። ሌላ መዳኛ መንገድና ሌላ ወንጌል የለም ። የአይሁዶች ቤተ መቅደስ መጋረጃ ተቀዶአል ። ስለዚህ ከጥንት ጀምረው የነበሩት ክርስቲያኖች እጣን ማጤስንና መስዋ

ዕት መሰዋትን ከእንግዲህ ወዲያ ለክርስቶስ ክብር ማቅረብ ጥቅም እንደሌለው በመረዳት ጸሎትንና ምስጋናን እንዲሁም የዋህ ልባቸውን ይሰውለት ጀመር ። ስለዚህ ከእንግዲህ ወዲያ ማናቸውም ዓይነት የማስተስሪያ መስዋዕት አያስፈልግም ።

ዮሐንስ ፲፯ ፡ ፩ ፤ ፲ ፡ ፲፰ ፤ ፲፱ ፡ ፴ ።
ገላትያ ፫ ፡ ፲፫ ።
፩ኛ ጴጥሮስ ፪ ፡ ፳፫ ፤ ፩ ፡ ፲፰ ፡ ፲፱ ።
ኤፌሶን ፩ ፡ ፯ ።
፩ኛ ቆሮንቶስ ፮ ፡ ፳ ።
ሮሜ ፫ ፡ ፳፭ ፤ ፭ ፡ ፱ ።
፪ኛ ቆሮንቶስ ፭ ፡ ፲፱ ።
ቆላስይስ ፩ ፡ ፳፩ ፡ ፳፪ ።
ዮሐንስ ፲፪ ፡ ፴፪ ፡ ፴፫ ።
ዕብራውያን ፱ ፡ ፲፪ ፤ ፲ ፡ ፲ - ፲፰ ።

ከጸጋ በታች ላለው መስዋዕት ሁለት ነገሮች ይጠቅማሉ ።

፩ኛ በእርሱ ደም ሥርየት ወይም መስዋዕትነት ማመን ። (ሮሜ ፫ ፡ ፳፩ ፡ ፳፭ ፤ ዕብራውያን ፲ ፡ ፲፱)

፪ኛ መናዘዝ ። (የሐዋርያት ሥራ ፳ ፡ ፳፩ ፤ ማቴዎስ ፭ ፡ ፳፫ ፡ ፳፬)

## ማስገንዘቢያ ።

አንዴ ለማስተስሪያ በተሰጠው መስዋዕትና እኛ ደግሞ እንደትዕዛዙ መሠረት እራሳችንን በመስዋዕትነት መስጠታችንን በሚያስረዳው መካከል ያለውን ልዩነት ለይተህ እወቅ ።

## ፮ኛ ። መዋጀት ።

መዋጀት የሚለው ቃል በቀላሉ በሁለት በኩል ይብራራል ።

ሀ) ያንዱን እስረኛ ሙሉ የቅጣት ዋጋ ከፍሎ አርነት ማስወጣት ።

ለ) ቀደም ብሎ የተሸጠውን ነገር በሙሉ ዋጋው መልሶ መግዛት ። የዚህ ቃል መንፈሳዊ አጠቃቀሙ የሚያመለክተን አንድን ኃጢአተኛ ከሰይጣን በርነት ፥ ከኃጢአት እስራትና ከሞት ተገዥነት ቅዱሱ የክርስቶስ ደም ሊዋጀው እንደሚችል ነው ። እርሱም ዋጂያችንና ዕዳ ከፋያችን ነው ።

የብሉይ ኪዳን የቤተሰብ መቤዠ በዕብራይስጥ ቋንቋ «ጐዮኤል» ይባላል ። ይህ የኛ ዋጂ ለሆነው ለክርስቶስ ጥሩ ሥዕላዊ ምሳሌ ነው ።

ሁለት አስፈላጊ ነገሮች ነበሩ ፤ ከነዚህም የመጀመሪያው የቅርብ ዘመድ ሊሆን ይገባል ። ከዚህም በቀር ሙሉ ዋጋ መክፈል የሚቻለው መሆን አለበት ።

ዘሌዋውያን ፳፭ ፡ ፳፭ ፡ ፳፮ ፡ ፵፰ ፡ ፵፱ ።
መዝሙር ፲፰ (፲፱) ፡ ፲፬ ።
ሩት ፫ ፡ ፲፪ ፡ ፲፫ ፡ ፬ ፡ ፬ - ፮ ።
ኢዮብ ፲፱ ፡ ፳፭ ።
ኢሳይያስ ፶፱ ፡ ፳ ።

መዋጀት በብሉይ ኪዳን እንደ ምሳሌ ሲሆን በአዲስ ኪዳን ግን በእርግጠኝነት ተፈጸመ ። ሆኖም ሦስት የግሪክ ቃላቶች ለዚሁ ማብራሪያ ተተርጉመዋል ።

፩ኛ አጉራዘ ፡— ከገቢያ ውስጥ ባርያ መግዛት ።
፪ኛ ኢክሳጎራዘ ፡— ከገቢያ ውጭ ባርያ መግዛት ።
፫ኛ ሉትሩ ፡— ዋጋውን ከፍሎ ከባርነት ወይም ከሞት ማዳን ።

ማርቆስ ፲ ፡ ፵፭ ።
ሉቃስ ፩ ፡ ፷፰ ።
ሮሜ ፫ ፡ ፲ ፡ ፲፱ ፡ ፳፬ ፡ ፯ ፡ ፲፬ ፡ ፳፫ ፡ ፰ ።
፩ኛ ቆሮንቶስ ፩ ፡ ፴ ።

ኤፌሶን ፩ ፥ ፯ ፥ ፲፬ ።
ገላትያ ፫ ፥ ፲ ፤ ፬ ፥ ፬ ፥ ፭ ።
፩ኛ ጢሞቴዎስ ፪ ፥ ፮ ።
ቲቶ ፪ ፥ ፲፬ ።

የግዥው ዋጋ ብር ወይም ወርቅ ሳይሆን ስለኛ በጎልጎታ የፈሰሰው የዋጂያችን ደም ነው ። ስለዚህ ከነበረብን ከኃጢአት በደል ባርነት አርነት ወጥተናል ።

ዮሐንስ ፩ ፥ ፳፱ ።
ማቴዎስ ፳ ፥ ፳፰ ።
መዝሙር ፵፰ (፵፱) ፥ ፲፭ ።
፪ኛ ቆሮንቶስ ፭ ፥ ፳፩ ።
ገላትያ ፫ ፥ ፲፫ ።
፩ኛ ጴጥሮስ ፩ ፥ ፲፰ ፣ ፲፱ ።
የዮሐንስ ራእይ ፭ ፥ ፱ ።

ሦስት አስፈላጊ ሁናቴዎች አሉ ። እነርሱም ፡—

፩ኛ በባርነት ያለ ሰው በዋጂው ማመን አለበት ።

፪ኛ የከፈለው ዋጋ ለደኅንነት በቂ መሆኑን ማመን አለበት ።

፫ኛ የገዛው ሲጠራው ሰንሰለቱን ጥሎ ዋጂውን መከተል አለበት ።

አርነት የወጣ ባርያ ሁለተኛ ተመልሶ ለመሸጥ ወደ ገቢያ መውጣት የለበትም ።

ዮሐንስ ፫ ፥ ፲፰ ፥ ፲፱ ፤ ፰ ፥ ፳፬ ።
መዝሙር ፶ (፶፩) ፥ ፭ ።
ኢሳይያስ ፶፫ ፥ ፮ ።
ሮሜ ፯ ፥ ፳ - ፳፫ ።
የሐዋርያት ሥራ ፳ ፥ ፲፫ ፥ ፳፩ - ፳፫ ።
ሮሜ ፰ ፥ ፪ ።
ገላትያ ፬ ፥ ፴፩ ፤ ፭ ፥ ፲፫ ።

## ፯ኛ ። ጽድቅ ።

ጽድቅ ማለት ምን ማለት ነው ? ከኃጢአት ፍርድ መላቀቅ ማለት ነው ። (ኢሳይያስ ፭ ፡ ፳፫ ፤ ምሳሌ ፲፯ ፡ ፲፭ ተመልከት) ይህ ደግሞ ጽድቅ የሚለውን ቃል ስለ ሰው ጽድቅ እንዴት እንደሚያመለክት ያሳያል ። ይኸውም አማኞችን እንደ ጻድቅ አድርጎ መቁጠር ነው ። ይህም ከዳኙ አምላክ በነፃ የምንቀበለው ስጦታ ነው ።

ጻድቁ አማኝ ወደ ፍርድ በሚቀርብበት ጊዜ ዳኛው ጥፋት እንደሌለው ይነግረዋል ።

ኢሳይያስ ፶ ፡ ፰ ።
ዮሐንስ ፭ ፡ ፳፬ ።
ሮሜ ፭ ፡ ፩ ፤ ፫ ፡ ፲፱ ፡ ፳ ፡ ፳፭ ፡ ፳፮ ፤ ፬ ፡ ፭ -
፰ ፤ ፰ ፡ ፴፩ - ፴፬ ።
፩ኛ ቆሮንቶስ ፩ ፡ ፴ ።
፪ኛ ቆሮንቶስ ፭ ፡ ፳፩ ።

ክርስቶስ ኃጢአታችንን በመስቀል ላይ ስለ ተሸከመልን እኛ ጻድቀናል ።

በእግዚአብሔር ዳኝነት እንደ ተነገረው ሁሉ በክርስቶስ ያመነ ጻድቅና ቅዱስ ነው ። ሮሜ ፭ ፡ ፱ ፤ ፰ ፡ ፩ ጽድቅ በጠቅላላው የጸጋ ሥራ ነው ። እኛ የምንኰራበት የጃችን ሥራ ውጤት ያስገኘው ነገር አይደለም ። ሌላም ዓይነት እንደ ራስን አሳልፎ ለመሥዋዕት ማቅረብና ሐብትን መስጠት ለማጽደቅ ጥቅም የለውም ።

ሮሜ ፫ ፡ ፳፬ ፡ ፳፰ - ፴ ፤ ፭ ፡ ፲፮ - ፲፰ ።
ገላትያ ፪ ፡ ፲፮ ፤ ፫ ፡ ፰ ፡ ፲፩ ፡ ፳፬ ፤ ፭ ፡ ፬ ።
ሉቃስ ፲፰ ፡ ፲፬ ።

ከቅዱሱ ፈራጅ ፊት አጥፊዎች መሆናችንን ብንናዘዝ እርሱ ያጸድቀናል ። ከዚያ በኋላ ሕይወታችን እርሱ

የደኅንነቱን ምስክርነት ይዞ መገኘት አለበት ።

ኤፌሶን ፮ ፡ ፳ – ፲ ።
ቲቶ ፫ ፡ ፬ ፡ ፭ ፡ ፯ ።
ያዕቆብ ፩ ፡ ፳፩ – ፳፬ ።

## ፳ኛ ። ወንጌል ።

ወንጌል ማለት ጥሩ ወሬ ወይም የምስራች ቃል ማለት ነው ። በግሪክ «ኢቫንጀሊዮን» የሚለው ቃል ጥሩ መልዕክት ማለት እንደሆነ እንረዳለን ።

በአዲስ ኪዳንም ወንጌል ተብሎ ተተርጉሟል ። ደኅንነት ለዓለም ሁሉ እንደተዘጋጀ ለክርስቶስ አገልጋዮች የተሰጠ የምስራች ቃል ነው ። ይህም ደኅንነት እንዴት እንደተበራከተና እኛም እንዴት ልናገኘው እንደምንችል ያስረዳል ።

በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና ። (ዮሐንስ ፫ ፡ ፲፮)

መድህን ወደ ዓለም እንደሚመጣ በብሉይ ኪዳን ውስጥ በብዙ ቦታ ተነግሯል ።

ዘፍጥረት ፫ ፡ ፲፭ ፤ ፲፪ ፡ ፩ – ፫ ።
ኢሳይያስ ፱ ፡ ፮ ፡ ፳፯ ፤ ፵፪ ፡ ፯ ፤ ፶፫ ።
ገላትያ ፫ ፡ ፳ ።

ክርስቶስ በዚህ ዓለም በነበረበት ወቅት እነዚህን ተስፋዎች ሊፈጽም እንደመጣ ተናግሮ ፈጽሞአቸዋል ። የርሱ ተከታዮች ስለ እርሱ ለዓለም እንዲናገሩ ተመርጠዋል ። ከዚህም በኋላ የዓለም ፍጻሜ ይሆናል ።

ማቴዎስ ፳፬ ፡ ፲፬ ።
ማርቆስ ፲፫ ፡ ፲ ፤ ፲፮ ፡ ፲፭ ።
የሐዋርያት ሥራ ፳ ፡ ፩ ፡ ፬ ፡ ፳፭ ፤ ፲፫ ፡ ፩ – ፬

፲፬ ፥ ፳፪ ፤ ፲፭ ፥ ፯ ፤ ፲፮ ፥ ፱ ፡ ፲ ።
ሮሜ ፩ ፥ ፩ ፡ ፲፮ ፤ ፲፭ ፥ ፲፰ - ፳ ።
፩ኛ ቆሮንቶስ ፩ ፥ ፲፯ ፤ ፱ ፥ ፲፪ ።
፪ኛ ቆሮንቶስ ፲ ፥ ፲፮ ።

ክርስቶስ ከሙታን ከተነሣ በኋላ መንፈስ ቅዱስ (አጽናኙ) እንደሚመጣና በርሱ ስፍራ ተተክቶ የጸጋን ወንጌል ሲያስተምሩ እንደሚመራቸው ተናገረ ።

ዮሐንስ ፲፬ ፥ ፲፮ ፤ ፲፭ ፥ ፳፮ ፡ ፳፯ ፤ ፲፮ ፥ ፯ ፡ ፲፫ ፡ ፲፬ ።
ሮሜ ፪ ፥ ፲፮ ፤ ፲፮ ፥ ፳፭ ።
፩ኛ ቆሮንቶስ ፩ ፥ ፲፯ ፤ ፱ ፥ ፲፯ ፡ ፲፰ ።
ኤፌሶን ፫ ፥ ፩ - ፰ ፤ ፮ ፥ ፲፱ ።
የሐዋርያት ሥራ ፳ ፥ ፳፬ ።
፩ኛ ተሰሎንቄ ፩ ፥ ፭ ፤ ፪ ፥ ፪ ።
የዮሐንስ ራእይ ፲፬ ፥ ፮ ።

እዚህ ላይ ሁለት ማስጠንቀቂያዎች አሉ ። የመጀመሪያው ከሰበክንላችሁ የተለየ ሌላ ወንጌል የሚሰብክላችሁ የተወገዘና የተረገመ ይሁን የሚል ነው ። ሁለተኛው ደግሞ እግዚአብሔር እውነተኛውን ወንጌል የሚሰሙ ሁሉ እንደሚቀበሉት ቃል አለመግባቱን የሚያስረዳ ነው ።

ገላትያ ፩ ፥ ፮ - ፱ ፤ ፪ ፥ ፲፩ - ፲፬ ።
ቆላስይስ ፪ ፥ ፲፮ - ፲፰ ።
፪ኛ ቆሮንቶስ ፲፩ ፥ ፩ - ፬ ፡ ፲፫ - ፲፭ ፤ ፪ ፥ ፲፭ ፡ ፲፮ ፤ ፬ ፥ ፫ ፡ ፬ ።
ማቴዎስ ፲፫ ፥ ፲፮ ።

ቅዱስ ጳውሎስ በመልዕክቱ ወንጌልን ባልሰብክ ወዮልኝ ይላል ።

## ፱ኛ ። ይቅርታ ።

የይቅርታ መሠረቱ እንደ መጽሐፉ አገላለጽ ይቅር ተበዩ ኃጢአተኛ ከኃጢአቱ መላቀቅ፤ አንድ ከበድ ሸክም ተሸክሞ ከቆየ በኋላ ሸክሙን አውርዶ የሚዝናና ሰው ይመስላል ።

የሰው ይቅርታ የሚጠቅመው ፍርዱ ከሚያስገኘው ቅጣት ለማምለጥ ብቻ ነው ። መለኮታዊ ይቅርታ ግን ፍጹም ስርየት ነው ። አፌሚ የሚለው ቃል ትርጉም በግሪክኛ አስወጥቶ መስደድ ማለት ነው ። በአዲስ ኪዳን አባባል ግን ሲተረጐም የኃጢአት ማስተስሪያ ይቅርታ ማለት ነው ።

በብሉይ ኪዳን እያንዳንዱ ሰው ከልቡ ተናዞ የደም መስዋዕት በማቅረብ በሕግ የተደነገገበትን ሲፈጽም ይቅ ርታን ይቀበላል ። ነገር ግን የአውራ ፍየልና የበሬዎች ደም ኃጢአትን ሊያስወግድ አይችልም ። ቢሆንም መስ ዋዕቱ በብሉይ ኪዳን ዘመን ለነበሩና አሁንም ላለነው ሰዎች የኃጢአት ይቅርታ የተሰዋው ክርስቶስን በሥዕል መልክ ያሳየናል ።

ሮሜ ፫ ፣ ፳፭ ፣ ፳፮ ።
ዘፍጥረት ፬ ፣ ፩ - ፭ ።
ዘሌዋውያን ፬ ፣ ፳ ፣ ፳፮ ፤ ፭ ፣ ፲ ፣ ፲፫ ።
ዘኍልቍ ፲፭ ፣ ፳፭ ፣ ፳፮ ።
መዝሙር ፳፱ (፴) ፣ ፭ ፤ ፳፭ (፳፮) ፣ ፲፰ ፤
፺፱ (፻፫) ፣ ፲፱ ።
ኢሳይያስ ፴፰ ፣ ፲፯ ፤ ፵፬ ፣ ፳፪ ።
ኤርምያስ ፴፩ ፣ ፴፬ ።
ዕብራውያን ፱ ፣ ፳፩ ፣ ፳፪ ።

ኢየሱስም አለ ይህ ለኃጢአት ስርየት የሚፈስ ደሜ ነው ። በሌላ ቦታ ደግሞ ደም ሳይፈስ ስርየት የለም የሚለውን ቃል እናነባለን ።

ማቴዎስ ፱ ፥ ፪ ፣ ፭ ፣ ፯ ፤ ፳፮ ፥ ፳፰ ።
ኤፌሶን ፩ ፥ ፯ ።
ዕብራውያን ፱ ፥ ፳፩ ፣ ፳፪ ።

አሁን በጸጋ የማናቸውም ዓይነት ኃጢአት ይቅርታ ነፃ ነው ። ይኸውም በእውነት መናዘዝና ክርስቶስን እንደ ግል መድኃኒት መቀበል ነው ። ሆኖም አንድ የተቀያየምነው ሰው ቢኖር ከርሱ ጋር እርቅ ከማድረጋችን በፊት ለመናዘዝ ብንሞክር ኑዛዜያችን አይሰማልንም ።

ማቴዎስ ፮ ፥ ፲፪ - ፲፭ ፤ ፲፰ ፥ ፳፩ ፣ ፴፪ - ፴፭ ።
ሮሜ ፫ ፥ ፳፬ ፤ ፬ ፥ ፯ ።
ኤፌሶን ፬ ፥ ፴፪ ።
ቆላስይስ ፪ ፥ ፲፫ ፤ ፫ ፥ ፲፫ ።
የሐዋርያት ሥራ ፲ ፥ ፵፫ ።
፩ኛ ዮሐንስ ፩ ፥ ፯ ፤ ፪ ፥ ፪ ።

እግዚአብሔር በማያቋርጥ ፍቅሩ ሁልጊዜ ወደ እራሱ ሊወስደንና ለዘላለም ይቅር ሊለን ዝግጁ ነው ። ይቅርታ መቀበላችን የልብና የሕሊናን እረፍት ይሰጠናል ፤ ለዚሁም የደኅንነት ቀን ዛሬ ነው ። ነገ የሚሆነውን አናውቅምና ያዘገየናል ።

ሉቃስ ፲፫ ፥ ፳፬ - ፳፯ ፤ ፳፫ ፥ ፴፬ ፣ ፵፪ ፣ ፵፫ ።
የሐዋርያት ሥራ ፲፫ ፥ ፴፰ ።
፪ኛ ቆሮንቶስ ፮ ፥ ፪ ።

## ፲ኛ ። የዘላለም ሕይወት ።

የዘላለም ሕይወት የእግዚአብሔር የነፃ ስጦታ ነው ። ለያንዳንዱ ሰው የማይሞት ሕይወት ሲሰጠው ግማሹ በዚህ ሕይወቱ በዘላለም ደስታ ሲኖር የቀረው ደግሞ በስቃይ ለዘላለም ይኖራል ።

የዘላለም ሕይወት ተሳታፊዎች የሆነው ዳግመኛ በተወለድን ጊዜ ነው ። እግዚአብሔር ዘላለማዊና ታላቁ

እኔ ነኝ ሲል ያለ የነበረ ለወደፊትም የሚኖር መሆኑን ይገልጻል ። ከሰው ልጅ ውድቀት የተነሳ ከመጣብን ጥፋት አምልጠን የዘላለም ሕይወት የምናገኘው እግዚአብሔር ባዘጋጀልን መንገድ ብቻ ነው ። ከሥጋዊ ሞት በኋላ ሊሆን ያለውን ነገር ሁሉ በመጽሐፍ ቅዱስ ተጽፎ እናገኛለን ። ሌላም የክርስቲያን የወደፊት የኑሮ መግለጫ ምንጭ የሆነ መጽሐፍ የለም ።

ዘጸአት ፫ ፥ ፲፬ ።
ራእይ ፳፪ ፥ ፲፫ ፤ ፩ ፥ ፰ ፥ ፲፰ ፥ ፳፩ ፥ ፮ ።
፩ኛ ዮሐንስ ፩ ፥ ፩ ፥ ፪ ።
ዮሐ. ፰ ፥ ፶፰ ፤ ፩ ፥ ፩ - ፬ ።

የዘላለም ሕይወት ለእያንዳንዱ ክርስቲያን ዳግመኛ በተወለደ ጊዜ ይሰጠዋል ።

ቲቶ ፩ ፥ ፪ ።
ዮሐንስ ፫ ፥ ፫ - ፲፮ ።
ማቴዎስ ፲፱ ፥ ፳፱ ፤ ፳፭ ፥ ፵፮ ።
ዮሐንስ ፫ ፥ ፴፮ ፤ ፭ ፥ ፳፬ ፥ ፵ ፤ ፮ ፥ ፵፯ ፥ ፷፰ ፤ ፰ ፥ ፲፪ ፤ ፲ ፥ ፲ ፤ ፲፩ ፥ ፳፭ ፤ ፲፪ ፥ ፳፭ ፤ ፳ ፥ ፴፩ ።
፩ኛ ጢሞቴዎስ ፮ ፥ ፲፪ ።

የዘላለም ሕይወት የሚጀምረው በልባችን ባለው ያዲስ ተፈጥሮ ሕይወት ነው ።

ሮሜ ፮ ፥ ፬ ፥ ፳፪ ፥ ፳፫ ፤ ፰ ፥ ፪ ፥ ፲ ።
፪ኛ ቆሮንቶስ ፬ ፥ ፲ ፤ ፭ ፥ ፲፮ ።
ገላትያ ፪ ፥ ፳ ፤ ፮ ፥ ፰ ።
ኤፌሶን ፬ ፥ ፲፮ ፥ ፲፰ ።
ፊልጵስዩስ ፪ ፥ ፲፮ ።
ያዕቆብ ፩ ፥ ፲፪ ።
፩ኛ ዮሐንስ ፫ ፥ ፲፬ ፥ ፲፭ ፤ ፭ ፥ ፲፪ ፥ ፲፫ ።

በመጽሐፍ ቅዱስ ክርስቶስ የሕይወት እራስ ተብሎ ይጠራል ።

የሐዋርያት ሥራ ፫ ፥ ፲፰ ።

ቆላስይስ ፫ ፥ ፬ ።

የአማኞች ስም በሙሉ በሕይወት መጽሐፍ ላይ ተጽፎአል ።

ዘጸአት ፴፪ ፥ ፴፪ ።

ፊልጵስዩስ ፬ ፥ ፫ ።

ራእይ ፫ ፥ ፭ ፤ ፲፫ ፥ ፰ ፤ ፲፯ ፥ ፰ ፤ ፳ ፥ ፲፪ ፥ ፲፭
፪ ፥ ፯ ።

ከዘፍጥረት ፫ ፥ ፳፪ - ፳፬ ጋር አመዛዝን ።

## ፲፩ኛ ። ዳግመኛ መወለድ ።

ዳግመኛ መወለድ ለደኅንነት አስፈላጊ ነው ። አንድ ሰው በእውነት ዳግመኛ ሲወለድ የሕይወትና የልብ መለወጥ ልምምድ ይኖረዋል ። ሕፃን ልጅ በራሱ እንደማይወለድ ሁሉ ሥጋዊ ሰውም በራሱ ጥረት ዳግመኛ ሊወለድ አይችልም ።

የዳግመኛ መወለድ ተግባር በመንፈስ ቅዱስ መሪነትና ገላጭነት ክርስቶስን በተቀበለ ሰው ሕይወትና ልብ ውስጥ ይከሄዳል ። ይህም ዳግመኛ በተወለደ ዕለት በሕይወቱ ውስጥ ይፈጸማል ። ሕይወቱንና ኃጢአቱን አሳልፎ ለክርስቶስ ባስረከበ ጊዜና እንደ አዳኙም አድርጐ በመነው ጊዜ የዳግመኛ መወለድ ተግባር በሕይወቱ ይፈጸማል ። ፍጥረታዊ ሰው ለእግዚአብሔር ነገር ታውሮአል ። ከኃጢአቱ ሊነፃ ያስፈልጋል ፥ ከዚህም በቀር ከፋው የተፈጥሮ ባሕርይ አቅመቢስ እንዲሆን ማድረግ ይገባል ።

ዮሐንስ ፫ ፥ ፫ ፥ ፭ ፥ ፯ ።

መዝሙር ፶ (፶፩) ፥ ፭ ።

ኤርምያስ ፲፯ ፥ ፱ ።

ማርቆስ ፯ ፥ ፳፩ - ፳፫ ።

፩ኛ ቆሮንቶስ ፪ ፥ ፲፬ ።
ሮሜ ፮ ፥ ፮ ፤ ፰ ፥ ፯ ፥ ፰ ።
ኤፌሶን ፪ ፥ ፫ ።

ይህም ውሳኔ በማስተዋልና በጥንቃቄ የሚወሰድ እምነታዊ እርምጃ ነው ። ከኃጢአት በመመለስና በክር ስቶስ ደም ከተማመኑ በኋላ የዳግም መወለድ ሥራ በግ ሩምና ምስጢራዊ በሆነ አኳኋን ይከተላል ። ይህ ልጅ ነት አንዴ በመቀበል ለዘለዓለም የሚኖር ነው ።

የእግዚአብሔር ልጅ የሆነ ሰው ወደ ኋላ ሊያፈገ ፍግ ይችላል ፤ ነገር ግን ፈጽሞ ክልክደ በስተቀር የእግ ዚአብሔር ልጅነቱን የሚቀማው የለም ። ወደ ኋላ ከተ መለሰ በኋላ በየዋህነት ተጸጽቶ ሊመለስ ይችላል ። ዳሩ ግን ይህ አድራጐቱ ሦስተኛ ወይም አራተኛ መወለዱ አይደለም ።

ማቴዎስ ፲፰ ፥ ፫ ።
ዮሐንስ ፩ ፥ ፲፪ ፥ ፲፫ ፤ ፫ ፥ ፲፬ ፥ ፲፭ ፤ ፭ ፥ ፳፬ ።
የሐዋርያት ሥራ ፫ ፥ ፲፱ ፤ ፬ ፥ ፲ ፤ ፲፮ ፥ ፴ ፴፩ ።
ገላትያ ፫ ፥ ፳፬ - ፳፮ ።

ይህ ዳግመኛ መወለድ በገዛ ኃይላችን እራሳችንን የምናሻሽልበት ነገር ሳይሆን ቃሉን በመስማት በመንፈስ ቅዱስ የሚደረግ የአዲስ ተፈጥሮ ለውጥ ነው ። ሰው በገዛ እጁ እንዲህ ያለውን ለውጥ ለማስገኘት ብርታት የለውም ። ይህም በወንጌል እንጂ በጥምቀት አይደለም ።

፩ኛ ቆሮንቶስ ፬ ፥ ፲፭ ።
የሐዋርያት ሥራ ፪ ፥ ፴፯ ፥ ፴፰ ።
ሮሜ ፮ ፥ ፪ ፥ ፬ ፥ ፭ ፤ ፰ ፥ ፲፬ – ፲፯ ።
ገላትያ ፫ ፥ ፪ ።
፪ኛ ቆሮንቶስ ፭ ፥ ፲፯ ።

አዲሱ ሕይወት ካዲሱ ልደት በኋላ ማደግ ሲገባው አማኙም ስለ አዲሱ ለውጥ መመስከር አለበት ። ምክን

ያቱም የመለኮታዊ ባሕርይ ተካፋይ ስለሆነና የክርስቶ ስን ሕይወት ስለተቀበለ ነው። ለመሆኑ ንስሐ የመግባት እርምጃ ወስደህ አምነሃልን? ይህን ባደረግህ ጊዜ መዳ ንህን አውቀሃል ማለት ነው።

፪ኛ ቆሮንቶስ ፭ ፡ ፲፯ ።
ኤፌሶን ፪ ፡ ፲ ፤ ፬ ፡ ፳፬ ።
ገላትያ ፪ ፡ ፳ ፤ ፯ ፡ ፲፭ ።
ቆላስይስ ፫ ፡ ፩ – ፲ ።
፩ኛ ጴጥሮስ ፩ ፡ ፳፫ ።
፪ኛ ጴጥሮስ ፩ ፡ ፬
፩ኛ ዮሐንስ ፭ ፡ ፲፩ ፡ ፲፪ ።

## ፲፪ኛ ። እርግጠኛነት ።

እርግጠኛነት ምን ማለት ነው? የአማኝ የማይናጋ የውስጣዊ እርግጠኛነት በእምነት ያገኘው ለዘላለም የተ ጠበቀ የደኅንነት አለኝታ ነው። ይህ እርግጠኛነት በሚ ለዋወጥ ስሜት ሳይሆን በእግዚአብሔር ላይ ባለን እምነ ትና በማይለወጠው አምላካዊ ቃል ላይ የተመሠረተ ነው።

ከዚህም በኋላ የአማኝ ሕይወት እያደገ ሲሄድ እረ ፍት ያገኛል። ከዚህም በቀር ክርስቶስ በልቡ ውስጥ መኖሩን ስለሚያውቅ ክርስቶስ በማንኛውም ድንገተኛ ነገር ይረዳዋል። እርግጠኛነት ሁለት ዓይነት ትርጉም አለው። ከነዚህም የመጀመሪያው ዳግመኛ ለተወለደ ሰው የሚሰጥ ወዲያው የሚገኝ የልጅነት ነፃነት ሲሆን ሁለተኛው ግን ሕይወታቸውን በሙሉ ባስረከቡ ክርስቲ ያኖች የሚደረግ ዕለታዊ የድል አድራጊነት ውርስ ነው።

ይሁዳ ፩ ።
ኢሳይያስ ፴፪ ፡ ፲፯ ።
፩ኛ ጴጥሮስ ፩ ፡ ፭ ።
፪ኛ ጢሞቴዎስ ፩ ፡ ፲፪ ፤ ፫ ፡ ፲፬ ፡ ፲፭ ፤

፬ ፥ ፰ ፡ ፲፰ ።

ሮሜ ፰ ፥ ፲፭ ፡ ፲፮ ፡ ፴፰ ፡ ፴፱ ።

እውነተኛ እርግጠኛነት እንዴት ይገኛል ? በመጀመሪያ በእግዚአብሔር ቃል ማመንና ከክርስቶስ ጋር ያለንን አንድነት በሰዎች ፊት በመመስከር ነው ። (ዮሐንስ ፭ ፥ ፳፬ ፤ ሮሜ ፲ ፥ ፱ ፡ ፲ ።) ከዚህ በኋላ በድል አድራጐት እርግጠኛነት በንጹሕ ሕሊናና በኛና በሰው ሆነ በእግዚአብሔር መኃል የተገደገደውን ግድግዳ አፍርሶ ማረፍ ነው ።

ይህ እስካልተስተካከለበት ጊዜ ድረስ መንፈስ ቅዱስ ይወቅሰናል ። መንፈስ ቅዱስ ሲወቅሰን በእምቢተኛነት የቀጠልን እንደሆነ እርግጠኛነታችን እየደከመ ይሄዳል ። ነገር ግን ስሕተቱ ሲታረም እርግጠኛነቱ ይመለስልናል ። በራስ ጥረት እንደተገኘ ከሚመስል እርግጠኛነትና ከሰዎች ምስጋና ከሚገኝ እርግጠኛነት ተጠንቀቅ ።

ማቴዎስ ፯ ፥ ፳፪ ፡ ፳፫ ።
ቲቶ ፩ ፥ ፪ ።
ዮሐንስ ፲ ፥ ፲ - ፲፬ ፡ ፳፯ – ፳፱ ፤ ፲፩ ፥ ፳፯ ፤
፲፯ ፥ ፲፩ ።
ሮሜ ፰ ፥ ፳፰ - ፴፬ ፤ ፲፬ ፥ ፴፯ ፤ ፲፬ ፥ ፰ ።
ቆላስይስ ፪ ፥ ፪ ።
ዕብራውያን ፮ ፥ ፲፰ ፤ ፯ ፥ ፳፭ ፤
፲ ፥ ፲፱ ፡ ፳፪ ፡ ፳፫ ።
፪ኛ ቆሮንቶስ ፩ ፥ ፲ ።
ኤፌሶን ፩ ፥ ፲፫ ፤ ፬ ፥ ፴ ።
ፊልጵስዩስ ፩ ፥ ፮ ።
ይሁዳ ፳፬ ።
ራእይ ፫ ፥ ፲ ።
መዝሙር ፲፮ (፲፯) ፥ ፰ ፤ ፺ (፺፩) ፥ ፲፭ ፤ ፻፳
(፻፳፩) ፥ ፫ ፡ ፰ ።
ኢሳይያስ ፵፮ ፥ ፫ ።

# ፲፫ኛ ። መለየት ።

መለየት ምን ማለት ነው ? መለየት በበሕታዊነት ወይም እራስን በዋሻ ውስጥ ሰውሮ በምልኩስና መኖር አይደለም ። ነገር ግን በእውነተኞች መንፈሳውያን ክርስ ቲያኖች አተረጓጐም በዓለም ውስጥ ሆኖ ከዓለም እርኩ ሰት ተለይቶ የመኖር ኃይል ነው ። በዓለማዊ ነገርና ደስታ ተይዞ የነበረ ፍላጐትን ክርስቶስ በሚሰጠው አዲስ ባሕርይ ልብን ተሞልቶ ዓለማዊውን ፍላጐት በድል አድራጊነት መተካት ነው ። ከፋትን ላለመተው ምክንያት መፈለግ የክርስቲያኖችን በረከት ይከለክላል ።

«ጳውሎስ ከማያምኑ ጋር በማይመች አከሄድ አት ጠመዱ ብሎአል ።»

፪ኛ ቆሮንቶስ ፮ ፣ ፲፬ - ፲፯ ።
፩ኛ ዮሐንስ ፪ ፣ ፲፭ - ፲፯ ።
ራእይ ፲፰ ፣ ፬ ፣ ፭ ።

የእስራኤላውያን ከግብፅ መውጣት ከዓለም የመለ የት ጥሩ ምሳሌ ነበር ። ፈርዖን ላለመውጣታቸው በጠላ ትነት መንፈስ ግላዊ መቋቋም አድርጐ ነበር ።

ሀ) የመጀመሪያው ቅውሚያ ። «በአገሩ ውስጥ ለእ ምላካችሁ ሰዉ ።» ባላችሁበት ክርስቲያን ሁኑ ። ሕሊ ናህ የሚያሳይህን በጐ መስሎ የሚታይህን አድርግ ፤ ለምን ዳግመኛ ትወለዳለህ ? የግብፅንም ምድር መልቀቅ አያሻም ።

ዘጸአት ፰ ፣ ፩ ፣ ፳፭ ፤ ፪ ፣ ፲ ፣ ፲፩ ፤
፮ ፣ ፬ ፣ ፭ ፣ ፱ ፤ ፯ ፣ ፲፬ ።

ለ) ሁለተኛው ቅውሚያ ። አንድ ልታደርጉት የሚ ገባ ነገር አለ ፤ ይኸውም «ርቃችሁ አትሂዱ» ክርስቲ ያን ሁኑ ። ነገር ግን እምብዛም አትጥበቡ ። እራቅ ብላችሁም አትሂዱ ። እንደ አገሌና አገሊት አትሁኑ ።

ዘጸአት ፰ ፡ ፳፰ ።

ገላትያ ፭ ፡ ፩ ።

ኤፌሶን ፮ ፡ ፲፭ ።

ሐ) ሦስተኛው ቅውሚያ ። አሁን «ወንዶች የሆናችሁ ብቻ ልትሄዱ ትችላላችሁ ።» ለራስህ ብቻ ክርስቲያን ሁን ፣ ነገር ግን በጋብቻ ስለመጣመርህና ስለ ቤተሰብህ ፈጽሞ አታስብ ። ሐሳብህና የፍትወት ስሜትህ እስከሁን በግብፅ ይኖሩ ይሆናል ።

ዘጸአት ፲ ፡ ፲፩ ።

መ) አራተኛው ቅውሚያ ። «እናንተ ሂዱ በጎቻችሁና ከብቶቻችሁ ግን ይቅሩ ።» ክርስቲያን ሁን ፣ ነገር ግን ሥራህ ከማንኛውም ነገር ጋር ቢተበበር ምንም አይደለም ። እንደመልካም ቤተሰቦች ትጠራ ይሆናል ። ነገር ግን የሥራህ ውጤትና ገንዘብህ እስከሁን በግብፅ ይገኛል ።

ዘጸአት ፲ ፡ ፳፬ ።

፩ኛ ሳሙኤል ፲፭ ፡ ፫–፱ ፡ ፲፫–፲፭ ፡ ፳፪ ፡ ፳፫ ።

ሙሴ የማይለወጥ ነበር ። አንድም ሰኮና አይቀርም ። ተመልሼ ፊትህን አላይም አለው ። ከዚያ በኋላ አገሩን ትቶ ለመሄድ ተዘጋጀ ።

የጳውሎስ ቃል እንዲህ ይላል ፦ ከመካከላቸው ወጥታችሁ የተለያችሁ ሁኑ ።

ዘጸአት ፲ ፡ ፳፮ ፡ ፳፱ ።

በጠቅላላው ክርስቲያኖች ኃጢአት የማድረግ ምክንያት ሊፈጥሩ አይገባም ። ከዘፍጥረት እስከ ራእይ ተጨማሪ ጥቅሶች ።

ዘፍጥረት ፲፱ ፡ ፩ ።

ዘጸአት ፴ ፡ ፲፫ ፡ ፲፬ ።

ዘሌዋውያን ፳ ፡ ፳፮ ።

ዘዳግም ፳፪ ፡ ፲ ።

ዕዝራ ፮ ፡ ፳፩ ።
ነህምያ ፱ ፡ ፪ ።
ዮሐንስ ፲፭ ፡ ፲፰ ፡ ፲፱ ፤ ፲፯ ፡ ፮ ፡ ፲፬ - ፲፯ ።
ሮሜ ፲፪ ፡ ፪ ።
፩ኛ ቆሮንቶስ ፭ ፡ ፱ ፡ ፮ ፡ ፮ ፡ ፲፫ ፤ ፲ ፡ ፳ ፡ ፳፩ ።
፪ኛ ተሰሎንቄ ፫ ፡ ፮ ፡ ፲፬ ።
፩ኛ ጢሞቴዎስ ፮ ፡ ፭ ።
፪ኛ ጢሞቴዎስ ፪ ፡ ፲፱ - ፳፮ ።
ዕብራውያን ፲፩ ፡ ፳፬ ፡ ፳፮ ፤ ፲፫ ፡ ፲፫ ።
፪ኛ ዮሐንስ ፲ ፡ ፲፩ ።

## ፲፬ኛ ። ቅድስና ።

ይህ በመንፈስ ቅዱስ እራስን በገለልተኛነት ለጌታ ክብር ማኖር ነው ። ይኸውም ጸጋ በውስጥ የሚሰራው የውስጣዊ መወለድ ቅድስና ነው ። በየዕለቱ በዓለም ተከበን ብንውል እንኳን ቅድስና ያለው የቅዱሳንን ኑሮ ልንኖር ይገባናል ። ይህም ከዓለም ያልሆነ ነገር ግን በዓለም የሚኖር የአዲስ ተፈጥሮ ሙላት ነው ።

በብሉይ ኪዳን ዘመን ሰው ወይም ዕቃ ተቀድሶ ላንድ ተግባር የሚለይበት የቤተ መቅደስ ውስጥ የአምልኮ ስርአታዊ በዓል ነበር ። (እንዲሁም ከየግል ሰው የሚጠበቅ የተወሰነ ቅድስና አለ ። ዘሌዋውያን ፲፱ ፡ ፪ ፤ ፳ ፡ ፳፮ ።)

ዘጸአት ፴ ፡ ፴ ።
ዘሌዋውያን ፰ ፡ ፲፪ ።
ኢያሱ ፮ ፡ ፲፱ ፤ ፯ ፡ ፲፫ ።
፪ኛ ዜና ፫ ፡ ፭ - ፯ ፤ ፬ ፡ ፲፱ - ፳፪ ፤ ፭ ፡ ፩ ።

በአዲስ ኪዳን ዘመን አማኝ በእውነት በክርስቶስ ባመነበት ጊዜ የተለየ ይሆናል ። ከዚያ በኋላ አማኙ በየዕለቱ ለመንፈስ ቅዱስ እራሱን እንደማስረከቡ መጠን

ቅዱስ ይሆናል ። ይኸውም ከራሱ ያልሆነ ቅድስና ነው ።

ቅድስና በክርስቲያኖች ዘንድ ሁለት ዓይነት ትር ጉም አለው ።

ሀ) የመጀመሪያ ቅድስና ፡፡ ማንኛውም ክርስቲያን በእምነት እንደገና በተወለደበት ወቅት መንፈስ ቅዱስን ይቀበላል ። የክርስቶስ መንፈስ የሌለው ከሆነ ግን ይኸው የእርሱ ወገን አይደለም ። (ሮሜ ፰ ፥ ፱)

ለ) ሙሉ ቅድስና ። የመንፈስ ቅዱስ ሙላት አስፈ ላጊ የሆነ ለድል አድራጊነት ሕይወት የሚሰጥ ነው ። ለዚሁም እራስን በፍጹም አሳልፎ መስጠትን ይጠይቃል ። የሚቀበል እምነት ሊኖረው ይገባል ። ሙላትን በውስጣ ችን ከተቀበልን በኋላ በመንፈስ ቅዱስ ሥራ የቅድስና እድገት እየቀጠለ ይሄዳል ።

ከክርስቶስ ውጭ እስካለህበት ጊዜ ድረስ በቅድስና ማደግ አትችልም ። ዳሩ ግን ክርስቶስን ከተቀበልክ በኋላ በቅድስና ማደግ ትጀምራለህ ።

፩ኛ ቆሮንቶስ ፮ ፥ ፲፱ ።
ዮሐንስ ፲፯ ፥ ፲፯ ።
፪ኛ ቆሮንቶስ ፫ ፥ ፲፰ ።
ኤፌሶን ፭ ፥ ፲፰ ፡ ፳፯ ።
፩ኛ ተሰሎንቄ ፭ ፥ ፳፫ ፡ ፳፬ ።
፪ኛ ቆሮንቶስ ፯ ፥ ፲፮ ፡ ፲፯ ፤ ፯ ፥ ፩ ።
ኤፌሶን ፩ ፥ ፬ ፤ ፪ ፥ ፳፩ ።
ቆላስይስ ፫ ፥ ፲፪ ።
ዕብራውያን ፪ ፥ ፲፩ ፤ ፲ ፥ ፲ ፡ ፲፬ ፤ ፲፪ ፥ ፲፬ ፤
፲፫ ፥ ፲፪ ።
፩ኛ ጴጥሮስ ፩ ፥ ፲፯ ፤ ፪ ፥ ፭ ፡ ፱ ።

ቤተ መቅደሱ በክርስቶስ እንደጸዳ ሁሉ የኛም ልብ አከታትሎ ከሚመጣበት ኃጢአት በክርስቶስ ሊጸዳ ይገባ ዋል ። ምንም ዓይነት የሚያረክስ ነገር በውስጥ ሊኖር

አይገባውም ።

፪ኛ ጢሞቴዎስ ፪ ፡ ፳፭ ።
፩ኛ ቆሮንቶስ ፫ ፡ ፲፯ ፡ ፲፯ ፤ ፯ ፡ ፩ ።
ዮሐንስ ፪ ፡ ፲፫ ፡ ፲፯ ፡ ፳፭ ።
፪ኛ ዜና ፳፱ ፡ ፮ ፡ ፲፯ ፡ ፲፯ ።

የተቀደሰውን ሕይወት ጠብቆ የመኖር ሁናቴ እነዚህ ናቸው ።

፩ኛ ከእግዚአብሔርና ከሕዝቦቹ ጋር በፍቅር የጋለ መተሳሰር እንዲኖረንና ወደኋላም አሸግሽገን እንዳንቀዘቅዝ የሚረዳን በየዕለቱ በጌታ ፊት የምናደርገው የጸጥታ ጊዜ ጸሎት ነው ። (ማቴዎስ ፳፮ ፡ ፵፩)

፪ኛ በቃሉና በሕሊናችን አማካኝነት መንፈስ ቅዱስ ለሚያዘን ነገር ሁሉ ወዲያው መታዘዝ አለብን ። (የሐዋርያት ሥራ ፭ ፡ ፴፪)

<u>ማስገንዘቢያ ።</u>

ኃጢአትን እንዴት አድርገን ለመቋቋም እንደምንችል የሚያስረዱ ሦስት ታላላቅ በአምላክ ገላጭነት ፥ በልምድ ፡ በመታወቅና በቅድስና የተደረሰባቸው ነገሮች ።

፩ኛ መንቀል ፦ የከፋት ዓላማ የሆነውን ኃጢአት ከስሩ እንዲነቀል የማድረግ ሙከራ መጽሐፍ ቅዱስ ስለዚሁ ነገር ከሚገልጸው ሐሳብ ጋር ተቃራኒ ነው ።

፪ኛ መጣል ፦ ጠላትን ለመጣል እንደምናደርገው ትንቅንቅ ያለ ውስጣዊ የማያቋርጥ ትግል ።

፫ኛ መታወም ፦ ከሶው ተፈጥሮ አቅመ ቢስ እንደ መሆኑ በግሪከኛ አጠራር ካታርጉ ይባላል ። ይኸውም የአሮጌው ተፈጥሮ ብርታት በፍጹም መሻር ማለት ነው ። (ሮሜ ፮ ፡ ፮)

# ፲፫ኛ ። አሸናፊው ሕይወትና የበረሃው ጉዞ ።

የክርስቲያን ሕይወት እንደ ጉዞ ነው ። ግብጽና እስረኝነቱ ቀረ ፣ ወደ ተስፋይቱ ምድር ለመድረስ ግን የበረሃውን ጉዞ መጓዝ ግድ ሆነ ። (፩ኛ ቆሮንቶስ ፲ ፥ ፲፩)

በበረሃው ጉዞ ተራርቀው የቆሙ «የኪሎ ሜትር ድንጋዮች» ይገኛሉ ። ይህም እንደ ምሳሌ የሆነ ነገር ብቻ ነው ። ቢሆንም ብዙዎቹ በሕይወታቸው ስለ ተፈ ጸመ እርግጥ እንደሆነ አድርገው ይገምታሉ ።

የእምነትን ጉዞ የጀመርክበትን ቀን አስብ ፥ በቀን የደመና ዓምድ በሌሊት የእሳት ዓምድ መሪህ ይሆናል ። ማርና ወተት ወደሚያፈሰው ምድር ሂድ ! ያንተ ነውና ።

፩ኛ አንደኛው የኪሎ ሜትር ድንጋይ ፍርሃት ነው ። እስራኤላውያን ከፊታቸው የኤርትራ ባሕር ከኋላቸው የፈርዖን ሰረገለኛ በተደቀነ ጊዜ እንደሞኝ ተቆጠሩ ። ሆኖም እግዚአብሔር ቀጥ ብላችሁ ቁሙ አላቸው ። ወዲያው የጠላቶቻቸው እሬሳ በውኃው ዳር ተንሳፎ አዩት ። ምንድነው ይህ ክርስቲያኖችን የሚያሸብር ፍርሃት ? የመ ሸሚጠጥ ፣ የመውደቅ ፣ የበሽታ ፥ የድኅነትና ይህን የመሳ ሰለ ነገር ሁሉ ፍርሃት ነው ።

ዘጸአት ፲፬ ፣ ፫ ፣ ፲ - ፲፫ ፣ ፲፱ ፣ ፴ ።
ኢሳይያስ ፵፩ ፣ ፲ ፤ ፶፰ ፥ ፰ ።

፪ኛ ሁለተኛው የኪሎ ሜትር ድንጋይ ጥማት ነው ። ውኃው መራራ ነው ፤ ሆኖም ዛፉ ጣፋጭ አደረገው ። ለምሳሌ ሥራህ ወይም የሥራ አባሪህ የማይግባባህ ሊሆን ይችላል ። ዳሩ ግን ክርስቶስ ብቻ ሕይወታችንንና የሚ ገጥመንን ከባድ ነገር ሁሉ ጣፋጭ ያደርገዋል ።

ዘጸአት ፲፭ ፣ ፳፪ ፣ ፳፫ ፣ ፳፭ - ፳፯ ።
ገላትያ ፫ ፣ ፲፫ ።

ሮሜ ፭ ፥ ፫ ፡ ፬ ።

ዮሐንስ ፬ ፥ ፲፬ ፤ ፯ ፥ ፴፯ ፡ ፴፰ ።

፫ኛ ሦስተኛው የኪሎ ሜትር ድንጋይ ማጉረምረም ነው ። ምግቡ አለቀ ፤ ሕዝቡ አጉረመረመ ። ሆኖም ማጉረምረማቸው በዳናቸው በእግዚአብሔር ላይ እንደ ሆነ ሙሴ አመለከታቸው ። እኛን ለመውገር ከማየት ይልቅ ቀና ብላችሁ የእሳቱን ዓምድ ተመልከቱ ። ማጉረምረም የተራበች ነፍስ ልማድ ነው ። የጸጥታው ጊዜ ቀረ ፤ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ጊዜም ቸል ተባለ ።

ዘጸአት ፲፮ ፥ ፪ ፡ ፰ ።

፩ኛ ቆሮንቶስ ፲ ፥ ፲ ።

ፊልጵስዩስ ፪ ፥ ፲፬ ።

፬ኛ አራተኛው የኪሎ ሜትር ድንጋይ ረሃብ ነው ። ረሃብ ጠኔ የያዛት ነፍስ ምልክት ነው ። ሆኖም እግዚአብሔር ከሰማይ የሆነውን ምግብ መናን ሰጣቸው ። የእግዚአብሔር ቃል በየዕለቱ ትኩሱን ሊበላ የሚገባ የሕይወት እንጀራ ነው ። ነዋሪ የሆነውን የሕይወት ቃል ክርስቲያን ትኩሱን በየዕለቱ ሊበላ ይገባል ። (ዮሐንስ ፩ ፥ ፩)

ዘጸአት ፲፮ ፥ ፫ ፡ ፬ ፡ ፲፰ - ፳ ።

ዮሐንስ ፯ ፥ ፴፫ ፡ ፴፭ ፡ ፵፩ ፡ ፵፱ ፡ ፶፩ ።

፭ኛ አምስተኛው የኪሎ ሜትር ድንጋይ ጥርጥርና ፈተና ነው ። ጌታ ከኛ ጋር ነው ወይስ አይደለም ብለው ጠየቁ ? የሆነ ሆኖ ለመሆኑ እኔ በእርግጥ ድኛለሁን ? ከዚህ የበለጠ እርቄ ለመሄድ አልችልም ። መንገዱንም አልወድ በማለት ደጋግመው እርሱ በማለት ፈንታ እኔ እያሉ ተናገሩ ።

ከዚህ በኋላ እግዚአብሔር ሙሴን ለጸሎት ወደ ተራራ ሰዶ እስራኤላውያን በአማሌቃውያን እንዲፈተኑና እንዲጨነቁ አደረጋቸው ። እኛ ከሥጋ ጋር እንዋጋለን ፤ ነገር ግን ስለኛ የሚማልደው ክርስቶስ ድል ያደርጋል ።

ጥርጥር ውስጣዊ ሁከትን ይፈጥራል፤ ነገር ግን ሙሴ ፀሐይ እስኪያዘቀዝቅ ድረስ ይቃትት ነበር።

በበረሃው ጉዞ ለሚገጥመን ሁከትና ሌላም ዓይነት ችግር ሊማልድ ክርስቶስ ዘወትር በሕይወት ይኖራል። (ገላትያ ፩፥ ፲፯ን ተመልከት)

ዘጸአት ፲፯፥ ፯ - ፲፯።
ሮሜ ፯፥ ፳፬፥ ፳፭፤ ፰፥ ፳፯ - ፳፰።
ዕብራውያን ፯፥ ፳፭።

፯ኛ ስድስተኛው የኪሎ ሜትር ድንጋይ አምልኮ ነው። ሙሴና የደመናው ዓምድ የተሰወሩባቸው ሳይሆን አይቀርም። ስለዚህ እምነታቸው እየጨለመ ስለ ሄደ አንድ በዓይን የሚታይ አሳባቸውን ሊያሳርፉበት የሚገባ አምላክ እንደሚያስፈልጋቸው ቆረጡ። አሮን በእግዚአብሔር ምትክ ሆኖ የሚመለክ የጥጃ ጣዖት ሰራላቸው። ስለዚህ ሁለተኛው ትዕዛዝ ፈረሰ፤ ከዚህ የተነሳ አሁንም የማይታይ እምነት ስለማያረካቸው፥ ሰዎች በእጅ የሚዳሰስ የመስዋዕት ስርዓትና ጣዖትን በማቆም በሚታይ እምነት ሊረኩ ይሞክራሉ።

በበረሃው ጉዞ ውስጥ ይህ ነገር ከዓለማዊነትና ከሥጋ ምኞት ጋር የተጣመረ አስተሳሰብ አለው። ሆኖም ሙሴ በመጽሐፍ ቅዱስ ተደናቂነት ካላቸው ጸሎቶች አንዱ በሆነው ጸሎቱ ልቡን በእግዚአብሔር ፊት ሰብሮ በመቃተት ይጸልይ ነበር። እንዲሁም ደግሞ መንፈስ ቅዱስ በውስጣችን እየቃተተ በቁዘማ ይማልድልናል።

ዘጸአት ፴፪፥ ፩፥ ፬ - ፯፥ ፳፬፥ ፳፭፥ ፴፩፥ ፴፪።
ሮሜ ፱፥ ፫።
መዝሙር ፻፭ (፻፮)፥ ፳ - ፳፪።

ሕፃን እጁን ተይዞ እንደሚመራ እግዚአብሔር እነዚህን ግልፍተኛና አመጸኛ ሕዝቦች ይዞ ወደ ተስፋይቱ ምድር ዳር አመጣቸው። ወደ ተስፋይቱ ምድር መግባት

እራስን አሳልፎ በመስጠትና በመንፈስ ቅዱስ ሙላት ይመሰላል ።

## ፲፪ኛ ። አሸናፊው ሕይወትና በፍጹም እራስን ማስረከብ ።

ወደ ተስፋይቱ ምድር መግባት ። አድካሚ ሆኖ ጠቃሚ የነበረው የበረሃ ጉዞ አለቀ ። የእስራኤል ልጆች ምንም እንኳን በዛ ያሉ ኃጢአቶችን ቢያደርጉ ወደ ተስ ፋይቱ ምድር ዳር መጡ ። በዮርዳኖስ ባሕረ ሰላጤ በስተ ምዕራብ ዳርቻ ለምለም የሆኑትን ተራራዎችና ዛፎች አሻ ቅበው ተመለከቱ ። በመጀመሪያውኑ ግብፅን ሲለቁ ሂዱና ግቡባት የሚል አምላካዊ ትዕዛዝ ተሰጥቶአቸው ነበር ። ታላላቆችን መርጠው ለስለላ በሰደዱ ጊዜ ድል እንደሚ ያደርጉ ተስፋ ተሰጣቸው ። እነዚህ አስራ ሁለቱ ሰላዮች የምድርዋን ፍሬ ቀምሰው በተጨማሪ ወሬ ይዘውላቸው መጡ ፤ ሆኖም በእምነታቸው ተጠራጠሩ ።

ያዩዋቸው የምድርዋ ግዙፍ ሰዎች በአዕምሮአቸው ሰሌዳ ተስለው ስለ ነበረ ፈሩ ። እነዚህ ግዙፍ ሰዎች በሚወዘውዙን የራሳችን ውሳኔ ይመሰላሉ ። ከእንግዲህ ፈቃደኛነታችን እንጂ እግዚአብሔር አያስገድደንም ።

ምንም እንኳ እግዚአብሔር ወደ ምድሪቱ የመግባት ተስፋ ቢሰጣቸው የመጀመሪያው የመግባት ዕድል ከግዙ ፎቹ ሰዎች ፍርሃት የተነሳ ቀረባቸው ።

በክርስትና ሕይወት ልምምድ ግዙፎቹ ሰዎች በምን ይመሰላሉ ? ይህ አጥብቆ ሊመረመር የሚገባው ጥያቄ ነው ። ምክንያቱም ብዙዎቹ ክርስቲያኖች ወደ እውነተ ኛው ሰላምና ድል አድራጊነት እረፍት ፈጽሞ አልገ ቡም ። የብዙ ክርስቲያኖች ትዳር በነዚህ ግዙፎች ሰዎች ፈርሰዋል ። ብዙዎች ደግሞ የተስፋ ምድር እንዳለ ከማ መን ክደዋል ። ኑ ! ለነዚህ የክርስቲያኖች ኃጢአት ስም

እናውጣላቸው ። ምክንያቱም በእግዚአብሔር ፊት አም ነው ካልዳኑት ሰዎች ኃጢአት በሚበልጥ ኃጢአት ይበ ድላሉ ። እነዚህ ሁሉ ግዙፎች ሰዎች በእኔነት ዙሪያ ሰፍረዋል ።

አስራ ሁለቱም ባስራ ሁለቱ በዮርዳኖስ ጥልቅ በተ ሰወሩት ድንጋዮች ተመስለው ከዚህ በታች በዝርዝር ሰፍረዋል ።

፩ኛ ግዙፉ አለማመን ። ይህ ከውስጣችን የሚሰ ማን የጥርጥርና በእግዚአብሔር ላይ እንዳንተማመን የሚ ያውከን ድምጽ ነው ። ያዳመጥነው እንደሆን እምነታ ችን እየጨለመ ይሄድና መፍራት እንጀምራለን ። በዚ ህም ጊዜ እግዚአብሔርን እኔ በጣም ደካማ ነኝ እንለዋ ለን ። እገሌና እገሌ ተደናቂ ተሰጥኦ አላቸው ፤ ከዚህም በቀር ከኔ በመልክ በኃብትና በትምህርት በጣም ይበል ጣሉ ። ይህን ለማድረግ አልችልም ፤ ምክንያቱም ተፈጥ ሮዬ አይፈቅድልኝም ። ለሌሎች ይቻላቸው ይሆናል ፤ ነገር ግን ለኔ አይቻለኝም ።

እርሱ በማለት እኔ የሚለው ቃል የአማኞች ጣዖት ሆኖአል ። እኔነታችን ከክርስቶስ ጋር መሰቀል አለበት ። ይህን በይቅርታ ወደርሱ አምጥተን ስናስረክብ ግዙፉ አለማመን ይሞታል ።

ዘኊልቊ ፲፫ ፥ ፳፫ ፥ ፴፫ ።
ዘጸአት ፬ ፥ ፲ - ፲፬ ።
መሳፍንት ፮ ፥ ፲፭ ።
ማርቆስ ፯ ፥ ፳ ፥ ፮ ።
ዕብራውያን ፫ ፥ ፲፱ ።
ኤርምያስ ፩ ፥ ፮ - ፱ ።
አሞጽ ፯ ፥ ፲፬ ፥ ፲፭ ። (በእንደዚህ ባለ አለማ መን ላይ ድል ።)

፪ኛ ግዙፉ ቸልታ ወይም ሐተታ ። በዘመናዊው

የጉዞ ጥድፊያ ተይዘን አብረን እንድንሄድ ፈቀድንለት ማለት ነው ። እኔ ለዚህ ዓይነት ነገር ጊዜ የለኝም ፤ በጣም ሥራ ይበዛብኛል ፤ እስከማረጅ እጠብቃለሁ ፤ ፈተናዬን እስክጨርስ ድረስ ፣ ጡረታ እስክወጣ ፣ በሥራችን እንድንሰምጥ እንፈቅዳለን ። ቀጠሮን የማራዘም ግዙፍ በረከታችንን እያበረደ ያስወግደዋል ።

ዘፍጥረት ፳፬ ፥ ፶ - ፶፮ ።
ማቴዎስ ፲፫ ፥ ፳፪ ።
ዕብራውያን ፬ ፥ ፯ ።

፫ኛ ግዙፉ ግላዊ እራስን እንደ ጻድቅ መቁጠር ። የብዙዎች ክርስቲያኖች ፈቃደኛ አለመሆንና ጉድለታቸውን መረዳት አለመቻል በዚህ ግዙፍ ምክንያት ነው ። ወደ በረከት ከመግባትም ከልክሎአቸዋል ። ጀርባቸውን ወደ ተስፋይቱ ምድር አዙረው በአዋራማውና በንዳዱ በረሃ በመቀመጥ ለነሱ የተሻለ ነገር እንዳለ አያምኑም ። ክርስቶስ በኋላቸው እጁን ዘርግቶ እስከ መቼ ልጠብቅ እንደሚላቸው በቤተ መቅደስ ሆነው እረጅም ጸሎት የሚጸልዩትን ሰዎች ይመስላሉ ።

ሌሎች እንደሚያዩን እራሳችንን ብናይ ኖሮ ሊያሳውረን ከለው ጉድፍ በተጠነቀቅን ነበር ።

ኢሳይያስ ፷፭ ፥ ፪ - ፭ ።
ሉቃስ ፲፰ ፥ ፱ - ፲፬ ።
፩ኛ ዮሐንስ ፩ ፥ ፰ - ፲ ።
፩ኛ ቆሮንቶስ ፰ ፥ ፪ ፥ ፫ ።
ሮሜ ፲ ፥ ፫ ።
ራእይ ፫ ፥ ፲፯ ፥ ፲፰ ።

፬ኛ ግዙፉ ራስን ማታለል ። ይህም ግብዝነት ፣ እርግጠኛ አለመሆን ፣ አለመከባበርና ሌሎች የሚከተሉትንም የሚያጠቃልል ነው ። ማጋነንና እውሸት ፣ መስሎ መገኘት ፣ ደርሶ ኃላፊ መምሰልና ይህን የሚመስሰሉም

ናቸው ። እርሱ በብርሃን እንዳለ በብርሃን ካልተመላለስን አንድነት ሊኖረን አይችልም ። ባንድ በኩል ብዙ መስሎ መታየት የፍርሃት ውጤት ነው ። ከዚህ አርዕስት በታች በመከታተል ማጋነንና ውሸት ይወራል ።

እራሳችንን በመጀመሪያ ሳናርም ስለ ክርስቶስ ከማ ውራትና ሌሎቹንም ከመንቀፍ እንጠንቀቅ ።

፩ኛ ዮሐንስ ፩ ፣ ፲ ።
ዕብራውያን ፬ ፣ ፲፪ ፣ ፲፫ ።
፩ኛ ዮሐንስ ፬ ፣ ፲፰ ።

፭ኛ ግዙፉ እራስን ማስደሰት ። ልማድ በቀላሉ ሊቀሰም የሚቻል ነገር ሲሆን ፣ በቀልድ ፣ በመብል ፣ በመ ጠጥና በሥጋዊ ፍላጐት ውድቀት ይመጣል ።

በፍትወት በኩል የሚመጣ እርከስናና ብልግና ብዙ ጊዜ ብዙዎቹን ወደ በረሃ አዘቅት ይመራቸዋል ። ጳው ሎስ እንዲህ ሲል መፍትሄውን ይሰጠናል ። በሚከተለው ተስፋ እንድንቆም ቀላል በሆኑ ነገሮች ላይ እንኳ ቢሆን ጥብቅ እርምጃ መውሰድ እንዳለብን ይነግረናል ።

«ምንም ዓይነት ፈተና የለም ።»

፩ኛ ቆሮንቶስ ፱ ፣ ፳፬ - ፳፯ ፤ ፲ ፣ ፯ ፣ ፲፫ ፤
፮ ፣ ፲፱ ፣ ፳ ።
ማቴዎስ ፭ ፣ ፳፰ ።
ማርቆስ ፯ ፣ ፳ - ፳፫ ።

፯ኛ ግዙፉ እራስን መውደድ ። እነዚህ ለክርስቶስ ያላስረከብናቸው ነገሮች ናቸው ። እነዚህም ከጊዜ ብዛት የተነሣ ከሰውነታችን ጋር አንድ ሆነዋል ። በዘር መመ ካት ፣ ወይም በክብር መመካት ፣ ምስጋናንና ገንዘብን መውደድ ፣ የመጀመሪያ የመሆን ምኞት ፣ ምቀኝነት ፣ ግዴለሽነት ፣ የሌሎቹን መብት መንካት ፣ የራስን ክብር መፈለግ ፣ የሌሎችን ክብር ማዋረድ ናቸው ። እራስን መውደድ የብዙዎችን ክርስቲያኖች ሕይወት አጥፍቶ

አል። ምናልባት እንዲህ ያሉ ጉድለቶች ቢኖሩብን ጥፋታችንን ሳይደብቅ የሚመክር ወዳጅ ያስፈልገናል።

ምናልባት ይህ የራስን መውደድ ግዙፍ ክርስቲያኖችን እንዲበቀሉና እንዲጨክኑ ያደርጋቸው ይሆናል።

፩ኛ ጢሞቴዎስ ፮፥፮–፰።
ገላትያ ፭፥፳፮።
ሮሜ ፲፪፥፫፥፲።
፩ኛ ጴጥሮስ ፭፥፭።
ሉቃስ ፳፪፥፳፮፥፳፯።

፮ኛ ግዙፉ ለራስ ማዘን። አንዳንድ ክርስቲያኖች ወዲያውኑ በይቅርታ በማለፍ ፈንታ ነገርን በልባቸው በማልመዝመዝ፥ ቂም በልባቸው በማጠራቀምና እንዲሁም ደግሞ የተጠቁ በመምሰል እራሳቸውን በማስተዛዘን ይኖራሉ። ስለዚህ ይህ አድራጎታቸው ስሕተት ከመሆኑም በላይ ተስፋ ወደ መቁረጥ ያደርሳቸዋል። ሙሴ አንጐራጓሪዎቹን እስራኤላውያን ጠርቶ ማንጐራጐራችሁ በጌታ ላይ እንጂ በኛ ላይ እንዳልሆነ እወቁ አላቸው።

የሐዋርያት ሥራ ፭፥፵፥፵፩፤ ፲፮፥፳፪፥፳፭።
፪ኛ ቆሮንቶስ ፲፩፥፳፬–፴፤ ፲፪፥፲።
ዘጸአት ፲፮፥፰።
ሮሜ ፭፥፫።
፩ኛ ቆሮንቶስ ፲፥፲፥፲፩።
ፊልጵስዩስ ፬፥፲፪፥፲፫።

፰ኛ ግዙፉ ኵምጣጣ ወይን። ይህን ስንል እንደ ባደረግነው ውድቀት ለራሳችን የምናደርግለት ይቅርታ ነው። ለምሳሌ ከዚህ አሸናፊ ሕይወት ከተባለ ትምህርት ምንም ጥቅም አላገኘሁም ስንል ነው።

በጥንት ታሪክ ቀበሮ ወይን ለመብላት ፈልጋ ብትንጠራራ መድረስ ስላቃታት ያ ወይን ኵምጣጣ ነው አለች ይባላል። እራሳችንን የማይጐዳ ይቅርታ ለበደላ

ችን ማዘጋጀት ተገቢ ነውን ? የሌሎችን ትምህርት የምን ቃወመው እኛ የትምህርቱ ተከፋዮች በለመሆናችን ይሆን ? ሰውን የምናጥላላውና የምንነቅፈው በኑሮው ደረጃ አቋም መድረስ ስላቃተን ይሆን ?

ሉቃስ ፲፩ ፡ ፲፬ ። «የዲያብሎስ ነው ።»
የሐዋርያት ሥራ ፳፮ ፡ ፳፬ ፡ ፳፭ ። «አበድክ»
የሐዋርያት ሥራ ፪ ፡ ፲፫ ። «ሰከሩ»

፱ኛ ግዙፉ ግላዊ እምነት ። ብዙ ክርስቲያኖች ስለ ግል እምነታቸው ዝና በክርክር ደግመው መልሰው ሊነ ጋገሩ ይችላሉ ። ነገር ግን በፍጹም ወደ ውስጥ ሳይገቡ በአጥር ላይ ተንጠልጥለው ይቀራሉ ። የግል ኃይማኖታ ቸውና ማኅበራቸው ሎሌ በመሆን ሌሎችን እንደ እሾህና አሜከላ በመውጋት ይኖራሉ ። በልማድ በያዙት ኃይማ ኖት ላይ ተጣብቀው ምንም ዓይነት ልዩ መግለጫ ለመቀ በል እምቢ ብለዋል ። በማንኛውም ጊዜ ያለ ፍቅር ሌሎ ችን ለማረም ይሞክራሉ ። ይህ ግዙፍ የወል በመሆን ቢታወቅም የብዙዎቹን አሸናፊ ሕይወትና የወንድማማች ነት ፍቅር ሰርቆአል ።

ከዚያም መንፈሳዊ አንድነት ይጠፋል ። በነዚህ በሚከተሉት ከመጠን በላይ እንጻንሠራባቸው እንጠን ቀቅ ። እኒሁም መለያየት ፡ አለመፋቀር ፡ የራስን መን ገድ መውደድ ፡ ሌሎችን መናቅ ፡ ትዕቢትና ይህን የመሳ ሰሉ ነገሮች ናቸው ።

ሉቃስ ፱ ፡ ፵፱ ፡ ፶ ፤ ፳ ፡ ፩ ፡ ፪ ።
ዘኍልቁ ፲፩ ፡ ፳፬ - ፳፱ ።
ዮሐንስ ፫ ፡ ፴፱ ፡ ፵ ።

፲ኛ ግዙፉ የግል አስተሳሰብ ። ይህ ብዙውን በክር ስቶስ ያለንን ሰላምና በምስክርነታችን ያለንን ደስታ ይወ ስድብናል ። ይህም መሽኰርመምን ፡ ብቸኝነትን ፡ እፍረ ትን መመልከት እንዲህ ያሉት ሁሉ የኩራት ምንጮች

ስለ ሆኑ ከሰዎች ጋር በኅብረት እንዳንሠራ ይከለክሉናል ። ኅብረት በእግዚአብሔር የተወሰነ የክርስቲያኖች ስጦታ ነው ።

ይህም የክርስቲያኖች የሕይወት መነቃቃት ምልክት ነው ።

ሉቃስ ፲ ፡ ፭ ።
የሐዋርያት ሥራ ፩ ፡ ፲፬ ።
፩ኛ ቆሮንቶስ ፲፪ ፡ ፲፪ - ፳፯ ።

፲፩ኛ ግዙፉ ጭንቀት ። ክርስቶስ በማቴዎስ ፯ ፡ ፴፩ ላይ ስለ መብልና ስለ ልብስ እንዳንጨነቅ በማብራራት ገልጾልናል ።

በሚቻለን ሁሉ ሙሉ ጥንቃቄ ከወሰድን በኋላ በተረፈ ለሕይወታችን ለሚያስፈልገን ነገር ሁሉ በእግዚአብሔር እንታመን ። ጭንቀት ዘወትር ስሕተት የሆነ ማረፊያ የሌለው ልማድ ነው ። ይህ ግዙፍ ጭንቀት እንደ ቀሩት ሁሉ እርምጃ ተወስዶበት እንዲቀበር ወደ ክርስቶስ መምጣት ይገባዋል ።

ፊልጵስዩስ ፬ ፡ ፯ ፡ ፯ ።
፩ኛ ዮሐንስ ፫ ፡ ፳፩ ፡ ፳፪ ።

፲፪ኛ ግዙፉ ይቅር የማይል መንፈስ ። ክርስቶስ በግልጽ ልባችንን የሚያስጨንቅ ይቅርታ ያልተቀበልንበት ነገር ቢኖር በታዛዥነት ወደርሱ ብናቀርበው ወዲያውኑ በማስወገድ ሰላሙን ይሰጠናል ። «መስዋዕቱን በመሠዊያው ላይ ትተህ በመጀመሪያ ሂደህ ከወንድምህ ጋር ታረቅ ።» ይቅርታ መጠየቅ ትልቅ ትግል ያለበት ሲሆን ያለ እርሱ ሌላ ከጌታና ከሰው ጋር ሰላምና እረፍት የምናገኝበት መንገድ የለም ።

ይቅርታ የማያደርግ መንፈስ ወደ ጥርጣሬና አለማመን ይመራል ።

ማቴዎስ ፭ ፡ ፳፫ ፡ ፳፬ ፤ ፯ ፡ ፲፪ ።

ሮሜ ፲፪ ፥ ፲፱ ፡ ፳ ።

## የ፵ው ዓመታት መንከራተት ።

የአሥራ ሁለቱ ምርጥ መሪዎች ጥርጥር። ወዲያው የመግባታቸው ወሬ በናፍቆት ይጠባበቅ ለነበረው ሕዝብ ተወራለት ። ሆኖም ብዙ ከመወያየታቸውና የራሳቸውን ብርታት ከነዚያ ጋር በመዛዘኑ መጠን ተስፋ ቆርጠው በጠቅላላ ጀርባቸውን ወደ ተስፋይቱ ምድር አዞሩ ።

ከዚህም የተነሳ ጥርጣሪያቸው ስለ በዛ ቁጣቸውም እየበረታ በመሄዱ እግዚአብሔርን ይወቅሱትና ይረግሙት ጀመር ። የዚህ ውጤት የአርባ ዓመታትን በቅጣት መንከራተት አስከተለ ። ይህ ታሪክ እኛ እራሳችን የክርስቲያን የተስፋ ምድር ወደሆነው የመንፈስ ቅዱስ ሙላት ልንገባ እንዳለብን ያስተምረናል ። ይህ ዓይነት ልምምድ የጴንጠቆስጤ ስጦታ ሲሆን ለማንም አማኝ ሊሰጥ ተስፋ ተሰጥቶአል ።

ይህንን የሚመስል የበረሃ ውስጥ የመንከራተት ጉዞ በብዙ ክርስቲያኖች ሕይወት ይገኛል ። እርሱም እረጅም ሆነ ወይም አጭር ያለ እግዚአብሔር ፈቃድ በከንቱ የምናሳልፈው ጊዜ እንደ ሆነ የታወቀ ነው ።

ዘኁልቁ ፲፬ ፥ ፩ - ፫ ፡ ፳፪ ፡ ፳፫ ፡ ፴፫ ።
፩ኛ ቆሮንቶስ ፲ ፥ ፩ - ፲፩ ።
ዕብራውያን ፫ ፥ ፲፯ - ፲፱ ።

የመጨረሻው ትዕዛዝ። የአርባው ዓመታት መንከራተት ከለቀ በኋላ አትፍሩ ሄዳችሁ የተስፋይቱን ምድር ያዙና በመዘር ፈንታ እረፉ የሚል አምላካዊ ተስፋ ተሰጣቸው ።

ዘዳግም ፩ ፥ ፮ ፡ ፰ ፤ ፮ ፥ ፮ - ፱ ፡ ፳፩ ፤ ፴፩ ፥
፮ - ፰ ፤ ፴፫ - ፳፰ ፡ ፳፮ ።
፩ኛ ቆሮንቶስ ፲፮ ፥ ፲፫ ።

ወደ ተስፋይቱ ምድር መግባት ።

የዮርዳኖስን ወንዝ አሻጋገር ተአምራታዊ ነበር ። ይህ ለእስራኤላውያንና ለአሕዛብ የእግዚአብሔር ኃይል ማመሳከሪያ ነበር ። «ነገ እግዚአብሔር በመካከላችሁ ታምራት ያደርጋልና እራሳችሁን ቀድሱ የሚል ትዕዛዝ ለሕዝቡ ተሰጠ ።» እኔ አልተዋችሁም ጌታ እግዚአብሔርም አረፍት ሰጥቶአችኋል ። ስለዚህ በርቱ ጥሩም ይዞታ ይኑራችሁ ። ለክርስቲያኖች ዮርዳኖስን መሻገር ምን ማለት ነው ?

የፍርሃትና የእኔነት ስልጣን ወደኋላ ቀርተው መቀበር አለባቸው ። አሥራ ሁለቱ ድንጋዮች ክርስቲያኖችን ወደ ተስፋው ምድር እንዳይገቡ በሚከለክሉዋቸው ነገሮች ይመሰላሉ ። እነዚህ ሁሉ ከዮርዳኖስ ጥልቅ ተቀብረው መታሰቢያም ሊቆምላቸው ያስፈልጋል ። ድል አድራጊነታችንንና ሰላማችንን የሚያውክ ነገር ሁሉ መቀበር አለበት ። የኢያሱ ከነሙሉ ትጥቁ ከእግዚአብሔር ባለሥልጣን መልአክ እግር ስር መንበርከክ እኛ ከክርስቶስ ስር ያለንን የሥልጣን ይዞታ ይገልጻል ።

አዲሱ ምድር ከሁከት ያረፈበት ጊዜ በይኖር እንኳን ጠላታችን እኛን ለማጥቃት የሚጥርበት ብርታቱ በእግዚአብሔር ኃይል ስለ ተደመሰሰ ያለ ተስፋ በመሆኑ ሊያሸንፈን አይችልም ። ይህም ኃይል በታዛዥነት በምንቆይበት ወቅት ሁሉ በድል አድራጊነት ይከተለናል ። ሮሜ ፰ ፥ ፳ ይህም ሰማያዊ ስፍራ ነው ። ኤፌሶን ፩ ፥ ፫

በዚያም ይህን የመሰሰሉ የመንፈስ ፍሬዎች ይገኛሉ ። እነርሱም ፍቅር ፥ ደስታ ፥ ሰላም ፥ ትዕግሥት ፥ ቸርነት ፥ በጎነት ፥ እምነት ፥ የውሃት ፥ ራስን መግዛት ናቸው ። ገላትያ ፭ ፥ ፳፪ ፥ ፳፫ ሥጋችንን ከክርስቶስ ጋር ከከፉ ምኞቱና ከኃጢአቱ ብንሰቅለው ድል አድራጊ ከመሆናችን በላይ ክርስቶስን የሚመስል ሕይወት ይኖረ

ናል ። ይኸውም በመንፈስ እንጓለን በመንፈስ የተመላለ ስን እንደ ሆነ ነው ። ገላትያ ፭ ፣ ፳፭

ይህ በመንፈስ የተሞላ ድል አድራጊ ሕይወት ጳው ሎስ እንደገለጸው በታላቁ በመንፈስ ፍሬ በፍቅር የተያዘ ክርስቶስን የሚመስል ሕይወት ነው ።

፩ኛ ቆሮንቶስ ፲፫ ፣ ፩ - ፲፫ ።

የመንፈስ ቅዱስ ሙላት በጴንጤቆስጤ ዕለት የተ ሰጠ ተስፋ ሲሆን በጥቂቶቹ የገሊላ ድሆች ሕይወት ተገ ልጾ ዓለምን ቀይሮአል ። ይህ በየዕለቱ በምናደርገው የጸሎት ሕይወትና የቃሉ ማንበብ ፣ በምናደርገውም ታዛ ዥነት ይፈጸማል ። ስለዚህ እራሳችንን እራሴን አሳልፌ ሰጥቻለሁን ? ብለን እንጠይቅ ። አሁን እራሴን አስረክቤ አለሁን ? ይህ የድል አድራጊነት ሕይወት ነው ።

ዘዳግም ፴፫ ፣ ፳፭ ፣ ፳፯ ።
ኢያሱ ፩ ፣ ፱ ፣ ፭ ፣ ፰ ፣ ፱ ፤ ፫ ፣ ፩ ፣ ፭ ፣ ፲ ፣ ፲፯ ፤
፬ ፣ ፩ ፣ ፰ ፣ ፱ ፣ ፳፫ ፣ ፳፬ ፤ ፭ ፣ ፲፫ - ፲፭ ።
ሮሜ ፯ ፣ ፳፬ ፣ ፳፭ ።
ዕብራውያን ፫ ፣ ፲፰ ፤ ፲፪ ፣ ፪ ።
ዮሐንስ ፰ ፣ ፴፯ ።

## ፲፯ኛ ። መንፈስ ቅዱስ ።

መጽሐፍ ቅዱስ መንፈስ ቅዱስ ሌሎች እንደሚ ሉት መልካም ኃይል ሳይሆን እውነተኛ አምላክ እንደ ሆነ ይገልጻል ።

መጽሐፍ ቅዱስ ስለ እግዚአብሔር የሚናገረው ቃል ስለ መንፈስ ቅዱስ ደግሞ ይናገራል ። ስለዚህ ስለ እግዚአብሔር በምንናገርበት ጊዜ ሁሉ በአክብሮት እንደ መሆኑ መጠን ስለ መንፈስ ቅዱስም ስንናገር በአክብሮት መሆን አለበት ።

ስለዚህ ቅዱስ የሆነው የሚያሰራን ቅዱስ ነገር ነውና እርኩስ ነገር አሰራኝ ከማለት እንጠንቀቅ ። ማንኛውም በመጽሐፍ ቅዱስ ስለ መንፈስ ቅዱስ የተነገረው ቃል መለኮታዊ ምላተ አካል እንደ ሆነ ያስረዳናል ።

ማቴዎስ ፳፰ ፥ ፲፱ ።
፪ኛ ቆሮንቶስ ፲፫ ፥ ፲፬ ።
ሉቃስ ፩ ፥ ፴፭ ።
መዝሙር ፻፴፰ (፻፴፱) ፥ ፯ - ፲ ።
ማቴዎስ ፲፪ ፥ ፴፩ ።
ዮሐንስ ፲፬ ፥ ፳፮ ፤ ፲፭ ፥ ፳፮ ፤ ፲፮ ፥ ፲፫ ፥ ፲፬ ።
የሐዋርት ሥራ ፭ ፥ ፫ ።
ሮሜ ፰ ፥ ፳፮ ፥ ፳፯ ።
ገላትያ ፭ ፥ ፯ ።
ኤፌሶን ፬ ፥ ፴ ።
ዕብራውያን ፱ ፥ ፲፬ ።
፩ኛ ዮሐንስ ፬ ፥ ፩ - ፫ ።

በብሉይ ኪዳን ዘመን መንፈስ ቅዱስ ለተለየ ተግባር ለአንዳንድ ሰዎች ይሰጥ ነበር ። ነገር ግን በኋላ ከጴንጤቆስጤ ቀን ጀምሮ ለቅዱሳን ሁሉ መሰጠት ጀመረ ።

ዘፍጥረት ፩ ፥ ፪ ፤ ፮ ፥ ፫ ።
ዘጸአት ፳፰ ፥ ፫ ፤ ፴፩ ፥ ፫ ።
ዘኁልቍ ፲፩ ፥ ፳፭ - ፳፱ ፤ ፳፬ ፥ ፪ ፤ ፳፯ ፥ ፲፰ ።
መሳፍንት ፫ ፥ ፲ ፤ ፮ ፥ ፴፬ ፤ ፲፫ ፥ ፳፭ ፤
፲፭ ፥ ፲፬ ።
፩ኛ ሳሙኤል ፲ ፥ ፮ ፤ ፲፮ ፥ ፲፫ ።
፪ኛ ሳሙኤል ፳፫ ፥ ፪ ።
፩ኛ ዜና ፳፰ ፥ ፲፪ ።
፪ኛ ዜና ፳፬ ፥ ፳ ።
ነህምያ ፱ ፥ ፴ ።
ኢዮብ ፳፯ ፥ ፫ ፤ ፴፫ ፥ ፬ ።

ኢሳይያስ ፬ ፥ ፬ ፤ ፴፪ ፥ ፲፭ ፤ ፵፬ ፥ ፭ ፤ ፵፬ ፥
፫ ፤ ፷፩ ፥ ፩ ፤ ፷፫ ፥ ፲ ።

ሕዝቅኤል ፴፮ ፥ ፳፯ ።

ኢዩኤል ፪ ፥ ፳፰ ፥ ፳፱ ።

ዘካርያስ ፬ ፥ ፮ ፤ ፲፪ ፥ ፲ ።

ክርስቶስ በሥጋ በምድር በነበረበት ዘመን የነበረ የአዲስ ኪዳን ትምህርት አጽናኙ ይመጣ ዘንድ ክርስቶስ ሊሄድ እንደሚያስፈልግ ተናገረ ። በዚህ አኳኋን መንፈስ ቅዱስ ከሦስቱ አካል አንዱ እንደ ሆነ እናያለን ። ይኸውም ከአብና ከልጁ የተለየ በመሆን በአንዱ አጠቃላይ አምላክ ውስጥ ተለይቶ ይጠራል ።

ሀ) በሕዝቦቹ ልብ ውስጥ አምላክ ነው ።

ለ) እርሱ የክርስቶስ በመንፈስ በሕዝቦቹ ልብ ውስጥ መገኘት ነው ።

ማቴዎስ ፩ ፥ ፳ ፤ ፫ ፥ ፲፮ ፤ ፲ ፥ ፳ ።

ሉቃስ ፩ ፥ ፲፭ ፤ ፬ ፥ ፳፭ - ፴፭ ፤ ፫ ፥ ፲፮ ፥ ፳፪ ፤
፬ ፥ ፩ ፤ ፲፩ ፥ ፲፫ ።

ዮሐንስ ፫ ፥ ፭ ፥ ፮ ፥ ፰ ፤ ፮ ፥ ፷፫ ፤ ፲፬ ፥ ፲፮ ፤
፲፮ ፥ ፯ ፥ ፰ ፤ ፳ ፥ ፳፪ ፤ ፲፬ ፥ ፲፮ - ፲፰ ፥ ፳፮ ፤
፲፭ ፥ ፳፮ ።

የጴንጤቆስጤ ቀን አዲስ ዕለት እንደመሆኑ መጠን የነፃ ስጦታ የሆነው ጸጋና መንፈስ ቅዱስ ለሚያምኑት ሁሉ ተሰጠ ።

የሐዋርያት ሥራ ፩ ፥ ፬ ፥ ፰ ፤ ፪ ፥ ፩ - ፬ ፥ ፲፰ ፥
፴፰ ፤ ፬ ፥ ፴፩ ፤ ፭ ፥ ፴፪ ፤ ፰ ፥ ፲፭ - ፲፯ ፥
፲ ፥ ፵፬ ፥ ፵፭ ፤ ፲፫ ፥ ፪ ፥ ፬ ፤ ፲፱ ፥ ፮ ።

በጳውሎስና በቀሩት ጸሐፊዎች መልዕክት የመንፈስ ቅዱስ ትምህርት በጣም ተብራርቶ እንደተጻፈ እናያለን ። የመንፈስ ቅዱስ ፍሬዎች ፍቅር ፥ ደስታ ፥ ሰላምና ይህን የመሳሰሉት ናቸው ። ገላትያ ፭ ፥ ፳፪ ፥ ፳፫

መጽሐፍ ቅዱስ መንፈስ ቅዱስ እንዳለንና መንፈስ ቅዱስ በመሞላት መካከል ልዩነት እንዳለ ያስተምረናል ።

ዕብራውያን ፮ ፡ ፬ ፡ ፮ ።
መዝሙር ፶ (፶፩) ፡ ፲፩ ።
ሮሜ ፰ ፡ ፰ ፤ ፳ ፡ ፮ - ፳፯ ፤ ፲፬ ፡ ፲፯ ።
፩ኛ ቆሮንቶስ ፪ ፡ ፬ ፡ ፲ - ፲፬ ፤ ፫ ፡ ፲፮ ፤
፲፪ ፡ ፫ ።
፪ኛ ቆሮንቶስ ፫ ፡ ፫ ፡ ፮ ፡ ፲፯ ፤ ፲፫ ፡ ፲፬ ።
ገላትያ ፫ ፡ ፪ - ፭ ፡ ፲፬ ፤ ፬ ፡ ፳፱ ፤ ፭ ፡ ፲፯ ፡ ፳፭ ።
ኤፌሶን ፬ ፡ ፫ ፡ ፬ ፡ ፴ ፤ ፮ ፡ ፲፯ ፡ ፲፰ ።
ፊልጵስዩስ ፩ ፡ ፲፱ ፤ ፪ ፡ ፩ ፤ ፫ ፡ ፫ ።
፩ኛ ተሰሎንቄ ፭ ፡ ፲፱ ።
፪ኛ ተሰሎንቄ ፪ ፡ ፲፫ ።
፩ኛ ጢሞቴዎስ ፬ ፡ ፩ ።
፪ኛ ጢሞቴዎስ ፩ ፡ ፯ ፡ ፲፬ ።
ቲቶ ፫ ፡ ፭ ።
ዕብራውያን ፱ ፡ ፲፬ ።
፩ኛ ጴጥሮስ ፬ ፡ ፲፬ ።
፪ኛ ጴጥሮስ ፩ ፡ ፳፩ ።
፩ኛ ዮሐንስ ፫ ፡ ፳፬ ።
ይሁዳ ፳ ። ራእይ ፫ ፡ ፳፪ ።

የመጨረሻው ትዕዛዝ «መንፈስ ቅዱስ ይሙላባችሁ» የሚል ነው ።

## ፲፫ኛ ። እግዚአብሔር ።

ብሉይ ኪዳን ከሁሉ በላይ የሆነው ታላቁና ዘለዓለማዊው ፥ እኔ ፡ እኔነኝ ባይ ፤ የሕያዋን ሁሉ የሕይወት ምንጭ ብሎ ይገልጸዋል ። «ኤሎሂም» የሚለው ቃል የጥቅል ስሙ እንደመሆኑ መጠን ከእውነተኛው ሦስቱ ሥላሴዎች ጋር ይስማማል ። በብሉይ ኪዳን እግዚአብ

ሔር እንደየሰዉ ፍላጐት በስሙና በጠባዩ እራሱን ገል ጸአል ።

በአንዱ አጠቃላይ አምላክነቱ በሦስትነት አባት ልጅ መንፈስ ቅዱስ ተብሎ ይጠራል። ይኸውም ሥላ ሴዎች የምንለውን የጥሪ ስም ሲገልጽ ነው ። ኤሎሂም ኃያልነቱን የሚገልጽ የጥቅል ስሙ ነው ። ይህም ስም በብሉይ ኪዳን ፪ሺ፭፻ ጊዜ ተጠቅሶአል ።

ዘፍጥረት ፩ ፡ ፩ ።

ኤል — ነጠላ ፦ ብርቱ ወይም መጀመሪያ ።

ዘፍጥረት ፲፯ ፡ ፲፫ ፤ ፵፯ ፡ ፫ ።

ኤል — ኤልዮን ፦ ከሁሉ ከፍ ያለው እግዚአብሔር ።

ዘፍጥረት ፲፬ ፡ ፲፰ - ፳፪ ።

ኤል — ሻዳይ ፦ በቂው አምላክ ።

ዘፍጥረት ፲፯ ፡ ፩ ፤ ፵፱ ፡ ፳፭ ፤ ፳፰ ፡ ፫ ፡ ፬ ።

ኤል — ዖላም ፦ ዘለዓለማዊ እግዚአብሔር ።

ዘፍጥረት ፳፩ ፡ ፴፫ ።

ያህዌህ ፦ ያለና የነበረ የማይለወጥ እግዚአብሔር ።

ዘፍጥረት ፪ ፡ ፬ ፤ ዘጸአት ፫ ፡ ፲፬ ፤ ሚልክያስ ፫ ፡ ፯ ።

ያህዌህ — ኤሎሂም ፦ እግዚአብሔር አምላክ እንደ ፈጣሪ ። ዘፍጥረት ፪ ፡ ፬ ።

ያህዌህ — ይርኤ ፦ እግዚአብሔር ያስባል ወይም ይሰጣል ። ዘፍጥረት ፳፪ ፡ ፲፫ ፡ ፲፬ ።

ያህዌህ — ሮፌ ፦ የሚፈውስ እግዚአብሔር ።

ዘጸአት ፲፭ ፡ ፳፯ ።

ያህዌህ — ኒሲ ፦ እግዚአብሔር ዓላማዬ ።

ዘጸአት ፲፯ ፡ ፰ - ፲፭ ።

ያህዌህ — ሻሎም ፦ እግዚአብሔር ሰላማችን ።

መሳፍንት ፯ ፡ ፳፬ ።

ያህዌህ — ሮይ ፦ እግዚአብሔር እረኛዬ ።

መዝሙር ፳፪ (፳፫) ፡ ፩ ።

ያህዌህ — ጽድቀኑ ፡- እግዚአብሔር ጽድቃችን ።
ኤርምያስ ፳፫ ፥ ፮ ፤ ፴፫ ፥ ፲፮ ።

ያህዌህ — ሸማህ ፡- እግዚአብሔር አለ ።
ሕዝቅኤል ፵፰ ፥ ፴፭ ።

ያህዌህ — ጸባዖት ፡- የሠራዊት ጌታ በጦርነት ጊዜ የሚዋጋ ሰማያዊ ኃይል ። ይህ በመጀመሪያዎቹ በአምስቱ መጻሕፍቶች አልተገለጸም ነበር ። ግን እስራኤል እረዳት በስፈለጋት ጊዜ በ፩ኛ ሳሙኤል ፩ ፥ ፫ ላይ ይህ ስም ተገለጸ ። በኤርምያስ መጽሐፍ ፹ ጊዜ ሲጠቀስ በሐጌ መጽሐፍ ላይ ደግሞ በሁለት ምዕራፎች ላይ ፲፬ ጊዜ ተጠቅሶ እናገኛለን ።

፩ኛ ሳሙኤል ፩ ፥ ፫ ።
መዝሙር ፳፬ (፳፫) ፥ ፲ ፤ ፵፮ (፵፭) ፥ ፯ ፥ ፲፩ ።
ኢሳይያስ ፮ ፥ ፩ – ፭ ፤ ፵፬ ፥ ፮ ።
ሚልክያስ ፫ ፥ ፲፮ ፥ ፲፯ ።
ሉቃስ ፪ ፥ ፲፫ – ፲፭ ።
ያዕቆብ ፭ ፥ ፬ ።

ስለ እግዚአብሔር ባሕሪይ የሚገልጹ የመጽሐፍ ቅዱስ ጽሑፎች እነዚህ ናቸው ።

፩ኛ እግዚአብሔር በሁሉ ቦታ አለ ። ከእርሱ ማምለጥ አይቻልም ። መዝሙር ፻፴፱ (፻፴፰) ፥ ፯ - ፲ ከፊትህ ወዴት እሸሻለሁ ? ኤርምያስ ፳፫ ፥ ፳፬ ። ሰው በስውር ቢሸሸግ እኔ አላየውምን ? የሐዋርያት ሥራ ፲፯ ፥ ፳፯ - ፳፰ ቢሆንም ከእያንዳንዳችን የራቀ አይደለም ።

፪ኛ ያልተወሰነ ኃይል አለው ። አይሸነፍም ። ኢዮብ ፵፪ ፥ ፪ ሁሉን ታደርግ ዘንድ ቻይ እንደ ሆንህ ፥ አሳብህም ይከለከል ዘንድ ከቶ እንደማይቻል አወቅሁ ። ኤርምያስ ፴፪ ፥ ፲፯ የሚያቅትህ ነገር የለም ። መዝሙር ፻፫ (፻፪) ፳ – ፳፩ በእግዚአብሔር ቃል ሰማዮች ጸኑ ። ማቴዎስ ፲፱ ፥ ፳፮ በእግዚአብሔር ዘንድ ሁሉ ይቻላል ።

ናሆም ፩ ፡ ፫ እግዚአብሔር በወጀብና በአውሎ ነፋስ ውስጥ መንገድ አለው ፤ ደመናም የእግሩ ትቢያ ነው ።

፫ኛ ወሰን የሌለው ዕውቀት አለው ። ሊታለል አይ ችልም ። መዝሙር ፻፴፰ (፻፴፱) ፡ ፩ – ፮ አቤቱ ፡ መረ መርኸኝ አወቅኸኝም ። ፩ኛ ዮሐንስ ፫ ፡ ፳ ሁሉንም ያውቃል ። መዝሙር ፻፵፯ (፻፵፮) ፡ ፬ ፡ ፭ የከዋክብት ንም ብዛት ይቆጥራል ። ሁሉንም በየስማቸው ይጠራቸ ዋል ። የሐዋርያት ሥራ ፲፭ ፡ ፲፰ ከጥንት ጀምሮ ሥራው ሁሉ በእግዚአብሔር ዘንድ የታወቀ ነው ።

፬ኛ ከሁሉ የሚበልጥ ነው ። በፍጹም አይበለጥም ። ዘፍጥረት ፳፩ ፡ ፴፫ ። የዘላለሙ አምላክ ። ፪ኛ ዜና ፮ ፡ ፲፰ ሰማይ ከሰማያትም በላይ ያለ ሰማይ ይይዝህ ዘንድ አይችልም ። ፩ኛ ጢሞቴዎስ ፩ ፡ ፲፯ ብቻውን አም ላክ ለሚሆን ለማይጠፋው ለማይታየውም ለዘመናት ንጉሥ ምስጋናና ክብር እስከ ዘላለም ድረስ ይሁን አሜን ።

እግዚአብሔር ቅዱስ ነው ።
ኢሳይያስ ፵፫ ፡ ፲፭ ።
እግዚአብሔር ፍቅር ነው ።
፩ኛ ዮሐንስ ፬ ፡ ፰ ፡ ፲፮ ።
እግዚአብሔር መንፈስ ነው ።
ዮሐንስ ፬ ፡ ፳፬ ።

## ፲፱ኛ ። ክርስቶስ ።

የተቀባ የሚለው ቃል ለተባረከው አዳኛችን ለክር ስቶስ የተሰጠ የክብር ስም ነው ። የሰው ልጅ በኃጢአት ከወደቀበት ጊዜ ጀምሮ የእግዚአብሔር በሰው አምሳል ወደ ምድር የመምጣት ተስፋ ተሰጠ ። በዓለም ፈንታም እንዲሞት ተወሰነ ። በእብራይስጥ የክርስቶስ የተለየ ስሙ መሢሀ ይባላል ። በግሪክ ደግሞ ክርስቶስ ተብሎ

ይጠራል ። ይኸውም የተቀባ ማለት ነው ። በእብራይ ስጥ የሥጋዊ ስሙ ፪ሆሹዋ እንደሚባል ሁሉ በግሪክ ደግሞ ኢየሱስ ይባላል ፤ ይኸውም አዳኝ ማለት ነው ። ስለ ክርስቶስ የሚገልጹ የጥቅስ ሰንሰለቶች በብሉይ ኪዳን በመያያዝ ተጽፈው እናገኛለን ። በእርሱም የዓ ለም ሕዝብ ሁሉ ይበረከሉ ፤ እርሱም የንጉሦች ንጉሥ የጌቶች ጌታ ነው ። ስሙም ድንቅ መክር ኃያል አምላክ የሰላም አለቃ ተብሎ ይጠራል ።

ዘፍጥረት ፫ ፡ ፲፭ ፤ ፲፪ ፡ ፫ ፤ ፲፯ ፡ ፲፱ ፤ ፳፰ ፡ ፲፬ ፤ ፵፱ ፡ ፲ ።
ዘኁልቁ ፳፬ ፡ ፲፯ ።
መዝሙር ፻፱ (፻፲) ፡ ፬ ።
ኢሳይያስ ፱ ፡ ፮ ፡ ፯ ፤ ፶፫ ፡ ፲፪ ፤ ፷፩ ፡ ፩ - ፫ ።
ማቴዎስ ፲፪ ፡ ፲፰ - ፳፩ ።
ዳንኤል ፱ ፡ ፳፭ ።
ዘካርያስ ፪ ፡ ፲ - ፲፫ ።
ሚልክያስ ፫ ፡ ፩ ፡ ፪ ።

ከአይሁዶች ነቢያት ቄስና ንጉሥ ይቀበሉ ፡ ይህ ክርስቶስ ሦስቱንም እንደ ሆነ ያሳያል ። በዘይት ሳይሆን በመንፈስ ቅዱስ የተቀባ መሆን ነበረበት ። የእሾህም አክሊል (በኃጢአተኞች ሰዎች እጅ) በራሱ ላይ ተደፋ በት ።

ዘሌዋውያን ፰ ፡ ፲፪ ።
ዕብራውያን ፬ ፡ ፲፬ ።
ዘዳግም ፲፯ ፡ ፲፭ ፡ ፲፰ ፡ ፲፱ ።
የሐዋርያት ሥራ ፫ ፡ ፳፪ ፡ ፳፫ ።
፩ኛ ነገሥት ፲፱ ፡ ፲፮ ።
፩ኛ ሳሙኤል ፲፮ ፡ ፲፪ ፡ ፲፫ ።
፪ኛ ሳሙኤል ፯ ፡ ፲፮ ።
ሉቃስ ፩ ፡ ፴፪ ፡ ፴፫ ።

መዝሙር ፸፱ (፸፲) ፥ ፩ ።
ዕብራውያን ፫ ፥ ፯ ፥ ፲ ።
ዘካርያስ ፱ ፥ ፱ ።
ኢሳይያስ ፷፩ ፥ ፩ ፥ ፪ ።
ሉቃስ ፬ ፥ ፲፰ ፥ ፲፱ ።
ማቴዎስ ፭ ፥ ፭ ፥ ፳፫ ፤ ፫ ፥ ፲፯ ፤ ፪ ፥ ፭-፯ ፤
፳፩ ፥ ፭ ፤ ፳፯ ፥ ፳፱ ።

በተአምራታዊ ሁናቴ ከድንግል በቤተልሔም መወለድ ነበረበት ።

ኢሳይያስ ፯ ፥ ፲፫ ፥ ፲፬ ።
ሚክያስ ፭ ፥ ፪ ።
ማቴዎስ ፩ ፥ ፳፫ ።
ሉቃስ ፩ ፥ ፴፭ ።

ለዓለም መሰቃየትና መሞት ከዚያም መቀበር በሦስተኛም ቀን መነሳት ነበረበት ።

መዝሙር ፲፭ (፲፮) ፥ ፲ ፤ ፳፩ (፳፪) ፥ ፩-፲፰ ።
ኢሳይያስ ፶ ፥ ፮ - ፯ ፤ ፶፪ ፥ ፲፫ - ፲፭ ፤
፶፫ ፥ ፩ - ፲፪ ።
ዘካርያስ ፲፩ ፥ ፲ - ፲፫ ፤ ፲፫ ፥ ፯ ።
ማቴዎስ ፳፮ ፥ ፵፪ ፤ ፳፯ ፥ ፴፭ ፤ ፳፯ ፥ ፱ ፥ ፲ ፥
፳፱ ፥ ፴፬ - ፴፯ ፥ ፶ ።

ስቅለት ። ለስድስት ሰዓት በመስቀል በፈቃደኝነት ተሰቅሎ ስለ ሰው ልጅ በደል ሞተ ። የሰው ልጅ አእምሮ በሙላት ሊያስተውለው በማይችለው ሁናቴ በሥጋው የዓለምን ኃጢአት ተሸክሞ ከባድ በሆነ ስቃይ አንደበት ሊገልጸው በማይችለው መከራ ተጨነቀ ። (ማቴዎስ ፳፯ ፥ ፵፮ ፥ ፵፯ ።) ለሞት አሳልፋ ወደሰጠችው ከተማ አተኩሮ ሲመለከት ወታደሮች በልብሱ እጣ ይጣጣሉ ነበር ፤ ቀሳውስትም ድል አደረግን ብለው ይታበዩ ነበር ፤ ንስሐ የገባውም ወንበዴ ይጸልይ ነበር ፤ የበአ

ሉም ሠራዊት ወደ እርሱ ይመለከት ነበር። ስለ በደ ሏም የሞተላት ዓለም በፊቱ ሆና ትታይ ነበር።

ላለፉትና ለሚመጡት ተሰቅሎ ስለ አዳናቸው ጌታ፣ የሚያወሳ ታላቁ የዓለም የታሪክ ምዕራፍ ተከ ፈተ።

ዮሐንስ ፲፪፥ ፴፪፤ ፲፱፥ ፲፯ - ፲፱።
ማቴዎስ ፳፯፥ ፴፫ - ፵፬።
ማርቆስ ፲፭፥ ፳፪ - ፴፪።
ሉቃስ ፳፫፥ ፳፯ - ፵፫።

ትልቁ የማስተስሪያ ሥራ እንደዚህ ተፈጸመ። ሆኖም ጌታ ኢየሱስ ከመቃብር ተነሥቶ ወደ ሰማይ እን ዳረገ በተመሳሳይ መንገድ በንጉሥነት በኃይልና በክብር እንደሚመጣ በዚሁ መጠን መጽሐፍ ቅዱስ ይገልጽል ናል። ይህም ዳግመኛ ስለመምጣቱ ነው። የመምጣቱ ምልክቶች አሁንም እየታዩ ናቸው።

የሐዋርያት ሥራ ፩፥ ፱ - ፲፩።
ማቴዎስ ፳፬፥ ፳፯ - ፴፩፥ ፴፱፤ ፳፭፥ ፯፥ ፲፫፥ ፴፩፥ ፴፪።

በተጨማሪ በበለጠ የክርስቶስን ጠባይ የሚገልጹ ስሞች አሉ። (አማኑኤል) እግዚአብሔር ከኛ ጋር ነው።

ኢሳይያስ ፯፥ ፲፬።
ማቴዎስ ፩፥ ፳፫።

ቃል፣ ማለት የተገለጠ ነገር ወይም ሐሳብ ማለት ነው። ሎጐስ የተባለው ከግሪክ የተወረሰው ቃል በእብ ራይጥም ተመሳሳይ ትርጉም ይዞ እናገኘዋለን።

ዮሐንስ ፩፥ ፩ - ፬።
ራእይ ፲፱፥ ፲፫።
፩ኛ ቆሮንቶስ ፩፥ ፳፬።

የኛ ጌታ (ኩሪዮስ) ምሳሌው ጌታ ማለት ከሆነው የግሪክ ቃል በእብራይስጥ አዶናይ ተብሎ እንደሚጠራ

ሁሉ በተለይ ባንድ ስፍራ ያህዌህ ከሚለው ስም ጋር አመሳስሎ ይጠቅሰዋል ። (ፊልጵስዩስ ፪ ፥ ፲፩)

ሮሜ ፩ ፥ ፬ ።
ሉቃስ ፲ ፥ ፩ ።
፩ኛ ቆሮንቶስ ፲፭ ፥ ፶፯ ።

(የሰው ልጅ) የክርስቶስ የሥጋዊ ስሙ ነው ። በአዲስ ኪዳን ሰማንያ ጊዜ ተጠቅሶአል ።

ማቴዎስ ፰ ፥ ፳ ፤ ፳፬ ፥ ፴፯ ፥ ፵፬ ።
ሉቃስ ፲፱ ፥ ፲ ።
ዮሐንስ ፫ ፥ ፲፫ ።

(የእግዚአብሔር ልጅ) የክርስቶስ መለኮታዊ ስምና ያምላክነቱ ማረጋገጫ ።

ማቴዎስ ፬ ፥ ፫ ፤ ፳፯ ፥ ፵፫ ።
ማርቆስ ፲፭ ፥ ፴፱ ።
ሉቃስ ፩ ፥ ፴፭ ፤ ፳፪ ፥ ፸ ።
ዮሐንስ ፩ ፥ ፲፬ ፤ ፫ ፥ ፲፮ ።
ፊልጵስዩስ ፪ ፥ ፮ - ፲፩ ።
ቲቶ ፪ ፥ ፲፫ ።
ራእይ ፪ ፥ ፲፰ ።

መስቀሉ ። መስቀል በላቲን ቋንቋ ክሩክስ ይባላል ። በዚያን ጊዜ ሮማውያን ለመቀጮ አራት ዓይነት መስቀል ነበራቸው ። በየትኛው ዓይነት መስቀል ጌታ እንደተሰቀለ በእርግጥ አናውቅም ። ቆንስጠንጢኖስ የተባለው ሮማዊ ንጉሥ የክርስትናን ሃይማኖት በተቀበለ ጊዜ ስቅለት የተባለውን የወንጀለኛ መቅጫ ለወጠ ።



# ፳ኛ ። ጸሎት ።

ጸሎት ፈጣሪና ሰው ለውይይት የሚገናኙበት መንገድ ነው ። ይኸውም የሀሳብ መግለጽ ነው እንጂ የሥጋ ግንኙነት አይደለም ። የፍላጎት ዶጋግሞ መጠየቅ ሳይሆን የእምነት ሁናቴ ነው ። ይህም የሰዎች ወደ እግዚአብሔር መመለሻ ሚስጥራዊ መንገድ ሲሆን የእግዚአብሔርም የነፃ ማውጣት ምድራዊ በረከት ነው ። ይህም በከፊል ከእግዚአብሔር የተሰጠ የጸጋ መንገድ ነው ። እግዚአብሔርም በክርስቶስ ከመገለጹ በፊት የብሉይ ኪዳን ሰዎች ወደእርሱ ይጸልዩ ነበር ።

ሀ) ወደእርሱም እንደ ጸጋውና ይቅር ባይነቱ ይቀርባሉ ።

ለ) ከሕዝቡ ጋር ቃል ኪዳን እንደ መግባቱ ይቀርቡታል ።

ዘፍጥረት ፲፰ ፥ ፳፫ ፤ ፴፪ ፥ ፱ - ፲፩ ።
ዘጸአት ፴፪ ፥ ፲፩ - ፲፫ ፤ ፴፫ ፥ ፲፪ - ፲፯ ።
ዘኍልቍ ፲ ፥ ፴፭ ፤ ፲፬ ፥ ፲፯ – ፲፱ ።
መሳፍንት ፲፮ ፥ ፳፰ ።
፩ኛ ሳሙኤል ፩ ፥ ፲ ፥ ፲፩ ።
፩ኛ ነገሥት ፰ ፥ ፳፫ ።
ነህምያ ፩ ፥ ፭ ፥ ፯ ።
መዝሙር ፶፯ (፶፮) ።
ዮናስ ፪ ፥ ፪ ።

ክርስቶስ ሲመጣ አዲስ ዝምድና ተገለጸ ። ሐዋርያቶቹን በአዲስ አቋም ጸሎትን አስተማረ ። ይኸውም የአባትና የልጅ ግንኙነት ነው ። በዳግመኛ ልደት የእግዚአብሔር ልጆች በመሆናችን እግዚአብሔርንም በልጅነት እናናግረዋለን ። ክርስቶስ በመካከላቸው በኖረበት ወቅት ይህን አዲስ የግል ግንኙነት አስተማራቸው ። ልጅ ላባቱ እንደሚናገር በማንኛውም ስፍራና ሁናቴ

በቀንም ሆነ በማታ ዓይናቸውንና ልባቸውን በንድነት ወደ እግዚአብሔር እንዲያነሱ አስተማራቸው ። በዚህ አዲስ ግንኙነት ከንቱ መደጋገምና ለታይታ በሰው መኃል የሚደረግ ጸሎት ክብሩን የተገፈፈ ስለሆነ ልብን ወደሚያነብ አባታችን በስውር እንጸልያለን ።

ማቴዎስ ፮ ፡ ፯ - ፲፭ ፥ ፲፰ - ፴፪ ፤ ፲፬ ፡ ፳፫ ፡
፳፮ ፤ ፳፮ ፡ ፵፩ ።
ሉቃስ ፲፭ ፡ ፲፰ ።
ማርቆስ ፩ ፡ ፴፭ ።
ዮሐንስ ፫ ፡ ፫ ፤ ፲፬ ፡ ፲፫ ፤ ፲፮ ፡ ፳፫ ፡ ፳፬ ፤
፲፯ትን በሙሉ ።

ከጴንጤቆስጤ በኋላ የአዲሱ ግንኙነት ልምምድ እየጠለቀና እየሞላ ሄዷል ።

የእግዚአብሔር ወንዶችና ሴቶች ልጆች ወደ ሙሉ ሰውነት ደረጃ እያደጉ ደርሰዋል ። እንዲሁም ጸሎት በክርስቶስ ዘንድ በሰማያዊ ሥፍራ ይደርሳል ።

እንዲህ ያለው ጸሎት በመንፈስ ፍላጐትን አስረክበን የሱን መሪነት መጠየቅ ነው ። በእውነተኛ እምነት ቢያስፈልግ ለሙሉ ሌሊት እንኳን ቢሆን ለነፍሳት መዳን በውስጣችን በሚቃትተው መንፈሱ እንጸልያለን ።

ይህ ነው የችግርን ተራራ የሚያስወግድና ጠይቀን የምናገኘው ።

ዮሐንስ ፲፮ ፡ ፳፫ ።
ሉቃስ ፱ ፡ ፳፰ ፤ ፲፩ ፡ ፩ ፤ ፳፪ ፡ ፵፬ ።
የሐዋርያት ሥራ ፬ ፡ ፴፩ ፤ ፱ ፡ ፭ ፡ ፲፩ ፤ ፲ ፡
፱ ፤ ፲፪ ፡ ፭ ፡ ፲፩ ፡ ፲፪ ፤ ፲፮ ፡ ፲፫ ፤ ፳፩ ፡ ፭ ።
ኤፌሶን ፩ ፡ ፲፭ - ፲፱ ፤ ፫ ፡ ፲፬ - ፳፩ ፤ ፮ ፡ ፲፰ ።
ሮሜ ፰ ፡ ፲፮ ፡ ፲፯ ፡ ፳፮ ፡ ፳፯ ።
ፊልጵስዩስ ፩ ፡ ፱ - ፲፩ ።
፩ኛ ተሰሎንቄ ፫ ፡ ፲ ።

ቆላስይስ ፩ ፥ ፱ ፡ ፲ ፤ ፬ ፥ ፫ ።
፩ኛ ጢሞቴዎስ ፪ ፥ ፳ ።
ያዕቆብ ፭ ፥ ፲፮ ።
ይሁዳ ፳ ።
፩ኛ ዮሐንስ ፭ ፥ ፲፬ - ፲፮ ፤ ፫ ፥ ፳፪ ።
ራእይ ፳፪ ፥ ፳

### ማስገንዘቢያ ።

በክርስቶስ ስም መጸለይ ክርስቶስ ምን እንደ ሆነና በአባቱም ተቀባይነትን ለማግኘቱ እርግጠኛ በመሆን ነው ። ሊሰጠን ባላረጋገጠልን ነገር ሁሉ በስሙ አንዳች ነገር አንጠይቅም ።

## ፳፩ኛ ። ሕግ ።

ሕግ ማለት ከሙሴ ጀምሮ እስከ ክርስቶስ ሞት ድረስ በእግዚአብሔር የተሰጠ ትእዛዝ ነው ። ሕግ ከጸጋ ጋር ይቃረናል ። ሕግ ቅድስናን ይጠይቃል ፤ ጸጋ ግን ቅድስናን ይሰጣል ።

በብሉይ ኪዳን በእምነት በምናደርገው የሕግ ታዛዥነት ከእግዚአብሔር ቅድስናን እንቀበላለን ። ከዚህ የተነሣ ከሕግ በታች ያሉት በሕግ ቅድስናን ለማግኘት በመሞከራቸው ወደቁ ። ሕግም ከእምነት አይደለም ።

ሕግ ወደ ክርስቶስ የሚያመጣ ሞግዚታችን ሆኖአል ። በሕግ ሁሉ ከኃጢአት በታች ተዘግቶአል ።

ዮሐንስ ፯ ፥ ፲፱ ።
ሮሜ ፲ ፥ ፪ ፥ ፫ ።
ገላትያ ፫ ፥ ፲፩ ፡ ፲፪ ፥ ፳፪ ፥ ፳፬ ።
ዘጸአት ፳ ፥ ፩ - ፳፮ ፤ ፳፬ ፥ ፲፪ ፤ ፴፩ ፥ ፲፰ ።
ዘዳግም ፮ ፥ ፮ - ፱ ።
መዝሙር ፩ ፥ ፪ ፤ ፲፰ (፲፱) ፥ ፯ ፥ ፰ ፤ ፴፮ (፴፯) ፥ ፴፩ ፤ ፴፱ (፵) ፥ ፰ ፤ ፻፲፰ (፻፲፱) ፥ ፩ ።

ከሕግ በታች ያሉ ሰዎች ሁሉ ወድቀዋል ። ክርስ ቶስ መጥቶ የሕግን ሥራ ፈጽሞ አዲሱን የጸጋ መንገድ ሰጠ ።

ኢሳይያስ ፩ ፥ ፲፫ - ፲፰ ፤ ፭ ፥ ፷፬ ።
ኤርምያስ ፱ ፥ ፲፱ ፥ ፲፫ - ፲፯ ።
ሕዝቅኤል ፳፪ ፥ ፳፯ ።
ዳንኤል ፱ ፥ ፳ - ፲፫ ።
ማቴዎስ ፭ ፥ ፲፯ ፤ ፳፪ ፥ ፴፯ ፥ ፴፯ ፥ ፵ ።
ሉቃስ ፩ ፥ ፯ ።
ዮሐንስ ፩ ፥ ፲፯ ።
የሐዋርያት ሥራ ፲፫ ፥ ፴፱ ፤ ፲፭ ፥ ፭ ፥ ፲ ፥ ፲፩ ፥
፳፰ ።
ሮሜ ፪ ፥ ፲፪ - ፲፬ ፤ ፫ ፥ ፳ ፤ ፬ ፥ ፲፭ ፤ ፭ ፥ ፲፫ ፥
፲፬ ፤ ፯ ፥ ፫ ፥ ፬ ፤ ፲፫ ፥ ፰ - ፲ ።
ገላትያ ፫ ፥ ፳፬ ።
ፊልጵስዩስ ፫ ፥ ፱ ፥ ፯ ።
ዕብራውያን ፯ ፥ ፲፱ ።
ያዕቆብ ፪ ፥ ፲ ።

የጸጋ ነፃነት በክርስቶስ ደም ተገዛ ። ስለዚህ ማንም ክርስቲያን በምንም ዓይነት ሁናቴ ወደ ሕግ ቢመለስ ከእ ግዚአብሔር እርግማን በታች ይሆናል ።

የሐዋርያት ሥራ ፲፭ ፥ ፩ ፥ ፪ ፥ ፭ ፥ ፲፱ ።
ገላትያ ፫ ፥ ፲ ፤ ፭ ፥ ፫ ፥ ፬ ።

## ፳፱ኛ ። ጸጋ ።

ጸጋ ጥረታችን ያላስገኘልን የነፃ ስጦታ ማለት ነው ። የመድኃኒታችን ቸርነትና ሰውን መውደዱ ነው ። እኛ ስላደረግነው በጽድቅ ስለነበረው ሥራ አይደለም ። ጸጋ የሕግና የሥራ ተቃራኒ ነው ። ሕግ እግዚአብሔር ቅድስናን ከሰው የሚጠይቅበት መንገድ ሲሆን ጸጋ ግን

እግዚአብሔር ቅድስናን የሚሰጥበት መንገድ ነው ። የጸጋ ዘመን የተጀመረው በክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ ነው ።

ቲቶ ፫ ፡ ፭ ፡ ፯ ።
ዮሐንስ ፩ ፡ ፲፮ ፡ ፲፯ ፡ ፲፰ ፤ ፫ ፡ ፴፬ ።
ሮሜ ፫ ፡ ፳፬ - ፳፮ ፤ ፭ ፡ ፪ ፡ ፲፭ - ፳፩ ፤
፮ ፡ ፲፬ ።
፪ኛ ቆሮንቶስ ፰ ፡ ፩ - ፫ ፤ ፱ ፡ ፰ ።
ገላትያ ፩ ፡ ፫ - ፲፭ ፤ ፪ ፡ ፳፩ ፤ ፭ ፡ ፬ ።

ሕግ ያስገድዳል ጸጋ ግን ይሰጣል ። «እንዲህ እንድታደርግ ትጠየቃለህ...» «እንዲህ እንድታደርግ ኃይል ተሰጥቶሃል ትባላለህ...»

ዘዳግም ፭ ፡ ፲፰ - ፳ ።
፩ኛ ዮሐንስ ፬ ፡ ፲፱ ።
ዮሐንስ ፩ ፡ ፲፮ ፤ ፫ ፡ ፲፮ ።
ሮሜ ፫ ፡ ፳፩ - ፳፬ ፤ ፱ ፡ ፫ ፤ ፲ ፡ ፬ - ፲ ።
ፊልጵስዩስ ፫ ፡ ፱ ፤ ፬ ፡ ፲፫ ።
ዕብራውያን ፯ ፡ ፲፱ ።
መዝሙር ፶ (፶፩) ፡ ፲፩ ።
ኤፌሶን ፫ ፡ ፲፱ ።

ሕግ መልካሞችን ይባርካል ፤ ጸጋ ግን ክፉውን ያድናል ።

ዘጸአት ፲፱ ፡ ፫ ።
ኤፌሶን ፪ ፡ ፩ - ፱ ።

በሙሴ ዘመን የነበረው ዓለም ከሕግ በታች ስለ ወደቀ አወዳደቁ ክርስቶስን እስከ መስቀል አድርሶታል ። እንዲሁም በዚህ በጸጋ ዘመን ያለው ዓለም የጸጋን ደኅንነት ባለመቀበሉ ከክህደቱ የተነሳ እስከ ፍርድ ይደርሳል ።

የእግዚአብሔር የጸጋ እቅድ አይደለም የወደቀው ፤ የወደቀው ሰው ነው ።

፪ኛ ቆሮንቶስ ፬ ፡ ፫ ፡ ፬ ።
፪ኛ ጢሞቴዎስ ፫ ፡ ፩ - ፰ ።
፩ኛ ዮሐንስ ፬ ፡ ፩ – ፫ ።
፪ኛ ጴጥሮስ ፪ ፡ ፩ ።
ይሁዳ ፬ ፡ ፰ ፡ ፲፩ - ፲፫ ፡ ፲፯ ።
፪ኛ ተሰሎንቄ ፪ ፡ ፲፩ ፡ ፲፪ ።
ራእይ ፫ ፡ ፲፬ – ፲፯ ።

የጸጋ እርነት ቀላልነት እግዚአብሔር ለዓለም የመሰነላት የመጨረሻ የደኅንነት እቅድ ነው ። ከዚህ የተለየ ሌላ ወንጌል የሚያስተምር የተረገመ ይሁን ።

ገላትያ ፩ ፡ ፰ ፡ ፱ ።
ዮሐንስ ፲ ፡ ፩

## ማስገንዘቢያ ።

የጸጋ ማግኛ መንገዶች ። በዚህ እግዚአብሔር በረከት ወደ ነፍሳችን የሚመጣበትን መንገድ አዘጋጀ ። የጸጋ ብርኰት ዘወትር የማይለወጥ የእግዚአብሔር የነፃ ስጦታ ነው ። ከዚህ የተለየ ሌላ ዓይነት ጸጋ የለም ። የሚከተሉት ዋናዎቹ የጸጋ ማግኛ መንገዶች ናቸው ። በዚህ የተሰጠውን ቀደም ተከተል እንደ ትክክለኛው ቀደም ተከተል አንቆጥረውም ።

፩ኛ ጸሎት ። ይህ የየግላችን ከክርስቶስ ጋር የመገናኛ ቁልፍ ስለ ሆነ የቀሩት የጸጋ መስመሮች ሁሉ መሠረት ነው ።

፪ኛ የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ ። የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ እራሱ የእግዚአብሔርን ድምፅ የምንሰማበት ላቅ ያለው የጸጋ መንገድ ነው ። በእርሱም እግዚአብሔር ያስገነዝባል ፤ ያድናል ፤ ይቀድሳል ፤ እንዲሁም ደግሞ ይመራል ።

፫ኛ የምስክርነት አገልግሎት ። እግዚአብሔር ሌሎቹን ወደ ክርስቶስ ለማምጣት በልጆቹ የምስክርነት አገ

ልግሎት ማለት በሚናገሩት ቃል ፣ በመዝሙራቸው ወይም በሕይወታቸው ይጠቀማል ። ክርስቶስ ወንዶችና ሴቶች ክርስቲያኖችን ወደ ራሱ መጥራቱ በዚያም ሆነ በዚህ እንዲያገለግሉት ሲሆን ሙሉ ጊዜያቸውን በመስ ጠት ሊያገለግሉ የወጡ ጥቂት የተለዩ አገልጋዮች አሉት ።

፬ኛ ማምለክ ። በቤታችን ወይም በቃሉ እንዳለው ሁለትም ሦስትም በስሜ በሚሰበሰቡበት በዚያ እገኛለሁ እንዳለ ከአማኝ ክርስቲያኖች መኃል ሆነን ልናመልከው እንችላለን ። ስለዚህ ለአምልኮት አለመሰብሰብ ከላይ ከአንድ እስከ ሦስት የተዘረዘሩትን የጸጋ ማግኛ መንገ ዶች የመናቅ ውጤት ነው ።

፭ኛ ጥምቀት ። ጥምቀትና ቅዱስ ቁርባን (የጌታ እራት) ከላይ ከተጠቀሱት አራቱ የተለዩ ጠቃሚነት ያላ ቸው ውጫዊን የመንፈሳዊነት ስርዓት የሚያመለክቱ አድራጐቶች ናቸው ።

፮ኛ የጌታ እራት ። ስለ ጌታ እራት ተመልከት ። የቤተ ክርስቲያን ስርዓተ አምልኮ የጸጋ ስጦታ ምልክት ነው ። ይህም የውስጥ መንፈሳዊ ጸጋ በውጭ በግልጽ ሲታይ ነው ። የወንጌላውያን ክርስቲያኖች የቤተ ክርስ ቲያን ስርዓተ አምልኮ ሁለት ብቻ ናቸው ። እነርሱም ጥምቀትና ቅዱስ ቁርባን ይበላሉ ። ሉተር ከሚባለው አስተማሪ ዘመን ጀምሮ ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን በሁ ለቱ በጥምቀትና በቅዱስ ቁርባን ታምናለች ። እነዚህም በጌታ በተለይ የተሰጡ ናቸው ።

በመጨረሻ ፡- ግላዊ የሆነ በክርስቶስ ከሚኖረን እምነት ውጭ የሆነ የክርስቲያን ስርዓት ሁሉ ጥቅመቢስ ነው ።

የሐዋርያት ሥራ ፪ ፣ ፵፫ – ፵፮ ፤ ፰ ፣ ፴፮ ።
፩ኛ ቆሮንቶስ ፲፩ ፣ ፳፱ ፤ ዕብራውያን ፬ ፣ ፪ ።

## ፳፫ኛ ። ፈተና ።

የሰይጣን የማጥመጃና የማስጐምጃ ፈተና ። የሰውን ልጆች ወደ ኃጢአት በመምራት የሚያሰናክልበት መንገድ ነው ። አንዳንድ ጊዜ ግን መጽሐፍ ቅዱስ በችግር መመርመርን ፈተና ብሎ ይጠራዋል ። ሰይጣን ይፈትናል እግዚአብሔር ግን ይመረምራል ። ስለዚህ በነዚህ በሁለቱ መካከል ያለውን ልዩነት ማወቅ ይገባናል ። ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻው መጽሐፍ ቅዱስ ሰይጣንን እንደ ፈታኝ አድርጎ ይገልጸዋል ። ይህ አሳሳች የሰውን ልጆች እያታለለ ወደ ኃጢአት ይመራቸዋል ።

ዘፍጥረት ፫ ፥ ፲፫ ።
ማቴዎስ ፬ ፥ ፩ ፥ ፫ ፤ ፮ ፥ ፲፫ ።
፩ኛ ቆሮንቶስ ፯ ፥ ፭ ።
፪ኛ ቆሮንቶስ ፲፩ ፥ ፫ ።
ሉቃስ ፬ ፥ ፲፫ ፤ ፳ ፥ ፲፪ ፥ ፲፫ ።
፩ኛ ተሰሎንቄ ፫ ፥ ፭ ።

ፈተና በልዩ ልዩ መንገድ የሚመጣ ሲሆን ለዳኑትም ሆነ ላልዳኑት ከልጅነት ጀምሮ እስከ እርጅና የማይቀር የተወሰነ ነገር ነው ። ክርስቶስ እንኳን ኃጢአት ሳይኖርበት ተፈትኗል ።

ሉቃስ ፳፪ ፥ ፳፰ ።
መዝሙር ፺፬ (፺፭) ፥ ፰ ።
የሐዋርያት ሥራ ፳ ፥ ፲፱ ።
ገላትያ ፬ ፥ ፲፬ ፤ ፮ ፥ ፩ ።
፩ኛ ጢሞቴዎስ ፮ ፥ ፱ ።
፩ኛ ጴጥሮስ ፩ ፥ ፮ ።
ያዕቆብ ፩ ፥ ፪ ፥ ፲፪ - ፲፭ ።
ዕብራውያን ፪ ፥ ፲፰ ፤ ፬ ፥ ፲፭ ።

የዳኑት ብቻ ድል የማድረግን ሚስጢር ያውቃሉ ።

ማቴዎስ ፳፯ ፡ ፵፮ ፡፡
፩ኛ ቆሮንቶስ ፲ ፡ ፲፫ ፡፡
ያዕቆብ ፩ ፡ ፲፪ ፡፡
፪ኛ ጴጥሮስ ፪ ፡ ፱ ፡፡
ራእይ ፫ ፡ ፳፩ ፡፡

## ፳፬ኛ ፡፡ የመሰቃየት ችግር ፡፡

በዓለም የሚደርስብን ሥቃይና መከራ ኃጢአት የተባለው በሽታ ውጤት ነው ፡፡ የዚህ ዓለም አምላክ የሚባል ስም ከተሰጠው አጥፊ የተነሳ ዓለም በሞላ ከመስመር ውጭ ወጥቶአል ፡፡

ከሞት ጋር የመጣ ማንኛውም ዓይነት የመሰቃየት መከራ በኃጢአት የመውደቅ ውጤት እንደ ሆነ መጽሐፍ ቅዱስ ይገልጻል ፡፡

በመከራና በስቃይ ላይ ክርስቲያኖች ምን አስተያየት አላቸው ? ሞት የማናመልጠው ነገር ነው ፡፡ እንዲሁም ስቃይና ሕመም ይኸንኑ ይመስላሉ ፡፡ እነርሱን ፊት ለፊት መግጠም አለብን ፡፡ በእምነትና በድፍረት መታገስ አለብን ፡፡ ምክንያቱም እነርሱ ክርስቶስን ገጥመውት በነበረ ጊዜ አሸንፏቸዋል ፡፡ አንዳንድ ጊዜ እነዚህ ደግሞ በመንገዳችን ከእግዚአብሔር የተፈቀዱ ሊሆኑ ይችላሉ ፡፡

ከእግዚአብሔር ፈቃድ ውጭ ምንም ዓይነት ጉዳት እንደማይደርስብን እንወቅ ፡፡ አንዳንድ ጊዜ በእግዚአብሔር ማጥሪያ እሳት ውስጥ መፈተን አለብን ፡፡ ይኸውም እግዚአብሔር ቆሻሻውን አውጥቶ የቀረውን ንጹሕ ወርቅ ስለሚፈልግ ነው ፡፡

ዘፍጥረት ፫ ፡ ፲፯ - ፲፱ ፤ ፳፪ ፡ ፩ - ፲፰ ፡፡
ኢዮብ ፩ ፡ ፳፩ ፣ ፳፪ ፤ ፪ ፡ ፲፯ ፤ ፳፫ ፡ ፲ ፡፡
ኢሳይያስ ፶፫ ፡ ፫ - ፭ ፡፡

ማቴዎስ ፲ ፥ ፳፰ - ፴ ፤ ፲፫ ፥ ፳ - ፳፪ ፤
ፙ፮ ፥ ፴፰ ።
የሐዋርያት ሥራ ፲፬ ፥ ፳፪ ።
፩ኛ ተሰሎንቄ ፫ ፥ ፪ – ፬ ።
፪ኛ ጢሞቴዎስ ፫ ፥ ፲፩ ፥ ፲፪ ።
ዕብራውያን ፲፩ ፥ ፴፬ - ፴፱ ።
ያዕቆብ ፩ ፥ ፪ ፥ ፫ ።
፩ኛ ጴጥሮስ ፪ ፥ ፳ - ፳፬ ፤ ፩ ፥ ፮ ፥ ፯ ።
ሮሜ ፭ ፥ ፫ ።
፪ኛ ቆሮንቶስ ፯ ፥ ፲ ።
ዕብራውያን ፲፪ ፥ ፯ - ፲፫ ።
፩ኛ ጴጥሮስ ፫ ፥ ፲፬ - ፲፯ ፤ ፬ ፥ ፲፯ – ፲፱ ፤
፭ ፥ ፲ ።

ክርስቲያን የሆነ ሰው ማንኛውንም መከራ በእምነትና በድፍረት ሊገጥመው ይገባል ። ግላዊ ምቾትን መፈለግ እራሱ ኃጢአት ነውና ፥ ድል መሆንና ማጉረምረም አይገባም ። ክርስቶስ በድል አድራጊነት አሸንፎአል ። ጥርጥር በእርሱ ላይ ያለንን አስተያየት ያጨልምብናል ። በኛ ላይ የሚመጣውን ሕመም ለማስወገድ የሚቻለውና ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ የሚደረገውን ነገር ጠንቅቆ ስለሚያውቅ ችግራችንን ማውሳት እምብዛም የሚያስፈልግ አይደለም ። እራሳችንን በሙሉ ብናስረክበውና በእርሱ ላይ የጠበቀ እምነት ቢኖረን በፈቃዱ ከለብን ማንኛውም ዓይነት ሕመም ሊፈውሰን ይችላል ። ድል ላደረገ የሕይወት አክሊል ይጠብቀዋል ።

መዝሙር ፱ ፥ ፱ ፤ ፳፯ (፳፮) ፥ ፰ ፤
፻፳ (፻፳፩) ፥ ፩ - ፰ ።
ምሳሌ ፲፪ ፥ ፲፫ ፤ ፲፰ ፥ ፲፫ ።
ኢሳይያስ ፴፰ ፥ ፲ ።
ማቴዎስ ፰ ፥ ፲፮ ፥ ፲፯ ።

ዮሐንስ ፲፮ ፥ ፳ ፤ ፲፮ ፥ ፴፫ ።
፪ኛ ቆሮንቶስ ፬ ፥ ፲፯ ፤ ፲፪ ፥ ፯ - ፲ ።
፩ኛ ተሰሎንቄ ፬ ፥ ፲፫ ፥ ፲፬ ።
፪ኛ ተሰሎንቄ ፩ ፥ ፬ - ፱ ።
፩ኛ ጴጥሮስ ፬ ፥ ፲፪ ፥ ፲፫ ።
፪ኛ ጴጥሮስ ፪ ፥ ፱ ።
ያዕቆብ ፩ ፥ ፲፪ ።
ራእይ ፫ ፥ ፲፪ ፤ ፳፩ ፥ ፬ ።

## ፳፫ኛ ። ጥርጥርና እየቀዘቀዙ የመሄድ ምክንያት ።

ቀስ በቀስ ሥር እየሰደደ እንደሚሄድ በሽታ ዓይነት ጥርጥርን በክርስቲያን መንገድ ላይ የሚያኖር የሚደብት የክርስቲያኖች ኃጢአት ነው ። ይህም የመጨረሻ ቀኖች ጠባይ ነው ። እርሱም የመቀዝቀዝ ጠንቅና ኃይልን የመጣል ፥ ያለማመን ምክንያት ነው ።

ከአንዳንድ የመቀዝቀዝ ጠንቅ ከሆኑት መዘዞች እራሳችንን እንዴት ልንጠብቅ እንደምንችል ለመረዳት መጽሐፍ ቅዱስ የሚለውን እንመልከት ።

ሀ) መጥፎው አላማኝ ልብ ።
ማቴዎስ ፲፫ ፥ ፲፱ ፥ ፳ ።
ማርቆስ ፬ ፥ ፭ ፥ ፮ ።
ሉቃስ ፰ ፥ ፳ ፥ ፳፪ ፥ ፳፬ ።
ዕብራውያን ፫ ፥ ፲፪ ።
ለ) መራራ ሥሮች ።
ዕብራውያን ፲፪ ፥ ፲፭ ።
ሐ) ይቅር አለማለት ።
መዝሙር ፴፯ (፴፮) ፥ ፲፰ ።
ማቴዎስ ፭ ፥ ፳፫ ፥ ፳፬ ፤ ፮ ፥ ፲፪ ።
ሮሜ ፲፪ ፥ ፲፱ ፥ ፳ ።

መ) ሰይጣን ቃሉን ይወስዳል ።

ሉቃስ ፰ ፥ ፲፪ ።
ማቴዎስ ፬ ፥ ፫ ።

ሠ) ኩራትና ትዕቢት ።

ዮሐንስ ፰ ፥ ፵፬ ።
ሉቃስ ፲፰ ፥ ፱ - ፲፬ ።
ሮሜ ፲ ፥ ፫ ።
፩ኛ ዮሐንስ ፩ ፥ ፰ - ፲ ።
፩ኛ ቆሮንቶስ ፰ ፥ ፪ ፣ ፫ ።
ራእይ ፫ ፥ ፲፯ ፣ ፲፰ ።

ረ) ክርክርና ምክንያት ።

ማቴዎስ ፲፯ ፥ ፳ ።
ሮሜ ፲፬ ፥ ፩ ።
፪ኛ ጢሞቴዎስ ፪ ፥ ፲፬ ፣ ፲፯ ፣ ፳፫ ።

ሰ) መጨነቅ ።

ፊልጵስዩስ ፬ ፥ ፮ ፣ ፯ ።
ማቴዎስ ፮ ፥ ፴፩ ።

ሸ) ዕዳ ። እርስ በርሳችሁ ከመዋደድ በቀር ለማንም ዕዳ አይኑርባችሁ ።

ሮሜ ፲፫ ፥ ፰ ።

ቀ) ንጹሕ ያልሆነ ሕሊና ።

የሐዋርያት ሥራ ፳፬ ፥ ፲፮ ።
፩ኛ ጢሞቴዎስ ፩ ፥ ፲፱ ፤ ፫ ፥ ፱ ።
ቲቶ ፩ ፥ ፲፭ ።

በ) እርኩሰት ።

ማርቆስ ፯ ፥ ፳ - ፳፫ ።
፩ኛ ቆሮንቶስ ፱ ፥ ፳፬ - ፳፯ ፤ ፲ ፥ ፮ ፣ ፲፫ ።

ተ) ሐሜት መናገር ። «የሌሎችን ሰዎች ኃጢአት ማውራት ።»

ዘሌዋውያን ፲፱ ፥ ፲፮ ።

መዝሙር ፲ (፲፩) ፥ ፫ ።
ሮሜ ፩ ፥ ፳፱ ፥ ፴ ።
ያዕቆብ ፫ ፥ ፬ - ፮ ።

ቸ) ያለመጸለይ ።
ማቴዎስ ፳፯ ፥ ፵፩ ።
ሉቃስ ፳፫ ፥ ፴፭ ።

የነዚህ ሁሉ መፍትሄ አዘውትሮ መታዘዝና አስፈላጊም በሆነ ጊዜ እንደ በሚሆነው ንጽሕና ለመንጻት ወደ ክርስቶስ መምጣት ያሻል ።

ተጠራጣሪው ቶማስ እጁን ዘርግቶ እንዲህ ሲል ጮኸ ። «አምላኬና ጌታዬ»

ዮሐንስ ፳ ፥ ፳፰ ፥ ፳፯ - ፳፱ ።
ማቴዎስ ፲፰ ፥ ፳፱ ፥ ፴፩ ።
፩ኛ ቆሮንቶስ ፱ ፥ ፳፯ ፥ ፳፯ ።
፩ኛ ጢሞቴዎስ ፮ ፥ ፳ ፤ ፮ ፥ ፲፪ ።
ፊልጵስዩስ ፫ ፥ ፲፱ ።
ዕብራውያን ፲፪ ፥ ፩ ።

## ፳፯ኛ ፡፡ ሥጋ ፡፡

ሥጋ ስንል ሰው በተፈጥሮው ከአዳም «አምላካዊ አምሳል» ውድቀት በኋላ የወረሰው ወደ ኃጢአት የሚመራ ተፈጥሮ ነው ። ይህ አሮጌው መጥፎ ተፈጥሮ ክርስቲያኖችን እንኳ በመማረክ የሥጋቸውን ፈቃድ እንዲከተሉ አድርጎ ሥጋዊ ክርስቲያን ያደርጋቸዋል ። ሆኖም ድል አድራጊነት ለሁሉ ተዘጋጅቶአል ። ሥጋ በሰው ትከሻ ላይ እንዳለ ከባድ ሸክም ነው ። የሮማዊያን የወንጀለኛ አቀጣጥ በሕል ገዳዩን ወንጀለኛ ከሟቹ ጋር አብሮ ማሰር ነበር ። ማስገንዘቢያውን ተመልከት ።

መዝሙር ፶ (፶፩) ፥ ፭ ።
ዮሐንስ ፫ ፥ ፮ ፤ ፳ ፥ ፲፫ ።

ሮሜ ፯ ፥ ፲፬ - ፳፬ ።
ገላትያ ፬ ፥ ፳፱ ።
ኤፌሶን ፪ ፥ ፫ ።

ሥጋ እንዴት ይሸነፋል? ሰው መጀመሪያ አዲስ ሕይወት ተሰጥቶት አዲስ መወለድ ያስፈልገዋል ። ከዚህ በኋላ ሕይወቱን በሙሉ ያስረከበ ከሆነ የተጫነውን የኃጢአት ባርነት ቀንበር ወርውሮ ከላዩ እንዲጥል ኃይል ይሰጠዋል ።

መዝሙር ፶፬ (፶፩) ፥ ፳፪ ።
ዮሐንስ ፩ ፥ ፲፪ ፥ ፲፫ ፤ ፮ ፥ ፷፫ ።
ሮሜ ፮ ፥ ፬ ፥ ፮ - ፲፩ ፤ ፯ ፥ ፬ - ፮ ፤ ፲፫ ፥ ፲፬ ።
ኤፌሶን ፩ ፥ ፲፬ ።

አዲስ የተወለደ ሰው በመንፈስ ግዛት እንጂ በሥጋ ግዛት አይደለም ። ሆኖም ሥጋው ከእርሱ ጋር ስላለ የራሱን ምርጫ በመውሰድ እንደ ሥጋ ወይም እንደ መንፈስ ፍላጐት ሊመራ ይችላል ። በመጀመሪያ አቋም ያለ ሥጋዊ ሲባል በሁለተኛው አቋም ያለ ግን መንፈሳዊ ይባላል ። ስለዚህ በሥጋ ላይ ድልን የሚያገኘው በመንፈስ ምራቻ የሚመላለሰው እንደ ሆነ ግልጽ ነው ።

ሮሜ ፰ ፥ ፰ ።
፪ኛ ቆሮንቶስ ፯ ፥ ፩ ፤ ፲ ፥ ፬ ፥ ፭ ።
ሮሜ ፯ ፥ ፳፩ - ፳፭ ፤ ፰ ፥ ፩ - ፬ ፥ ፰ ፥ ፱ ።
ዘጸአት ፲፬ ፥ ፴ ።
፩ኛ ቆሮንቶስ ፫ ፥ ፩ - ፬ ።
ገላትያ ፫ ፥ ፫ ፤ ፭ ፥ ፩ ፥ ፲፮ ፥ ፲፯ ።
ኤፌሶን ፪ ፥ ፲፩ ፥ ፲፪ ።

ሥጋዊ ሕይወት በክርስቲያኖች ውስጥ እራሱን በእንደነዚህ ባለው ፍሬው ይገልጻል ። በራስን ወዳድነት ፥ በምቀኝነት ፥ ድልን በማጣት ፥ በመለያየት ፥ በወረዳ የኑሮ አቋም ።

፩ኛ ቆሮንቶስ ፩ ፣ ፲፩ ፣ ፲፪ ፤ ፫ ፣ ፩ – ፬ ።
ፊልጵስዩስ ፩ ፣ ፲፭ – ፲፯ ።
፪ኛ ቆሮንቶስ ፲፪ ፣ ፳ ፣ ፳፩ ።
፩ኛ ዮሐንስ ፪ ፣ ፲፯ ።
ይሁዳ ፳፪ ፣ ፳፫ ።
ራእይ ፫ ፣ ፲፭ ፣ ፲፱ ።

## ማስገንዘቢያ ።

በሮሜ ፯ ፣ ፳፬ ቅዱስ ጳውሎስ ስለ ሮማውያን የወንጀለኛ አቀጣጥ ዓይነት የተናገረውን በጽሑፉ የገለጸ ይመስላል ። ነፍሰ ገዳዩ ፍርዱን ከተቀበለ በኋላ ከሟቹ ሬሳ ጋር ታስሮ እስኪሞት ድረስ ይተዋል ። «ይህም በቁም መሞት ተብሎ ይጠራል ።»

# ፳፯ኛ ። ግብዝነት ።

ይህ ከግሪክ ሐይፓአክራሲስ ከሚለው ቃል የተወረሰ ነው ። ትርጉሙም ያልሆኑትን መምሰል ማለት ነው ። ይህም መንፈሳዊ ለመምሰል የመንፈሳዊ ልብስ ስለለበሱትና ልባቸው ግን ከእግዚአብሔር ስለራቀው ሰዎች ያመለክታል ።

በመንፈሳዊ አነጋገር ግብዝነት ማለት ተግደርዳሪ ያልሆነውን ነኝ ባይ የማይመስለውን አስመሳይ ማለት ነው ።

በአዲስ ኪዳን ክርስቶስ በማከታተል እንዲህ ያለውን ኃጢአት ያብራራል ። ይህም ከመምሰል ጋር እጅ ለእጅ ተያይዞ የሚሄድ የመንፈሳዊ እውረት በመጨረሻ ወደ ክህደት ያደርሳል ። እውነተኛ መንፈሳዊ ኃይል በማጣት ክርስቲያኖች በውጭ በሚሆነው ደንብ መጠበቅና የክርስቲያን ንግግርን እንደ ልብስ ለብሰው ይሄዳሉ ። ይህም በእግዚአብሔር ፊት አስጸያፊ ከሆኑት ኃጢአቶች አንዱ ነው ። ይህም ከአድራጎት ኃጢአት የላቀ

የአስተያየት ኃጢአት ሆኖ እናገኘዋለን ። በጌታችን ትም ህርት ይህ ወደ ገሃነም የሚያስገባ የተረጋገጠለት አንደ ኛው ኃጢአት ነው ።

ማቴዎስ ፭ ፥ ፪ ፥ ፳ ፥ ፲፮ ፤ ፭ ፥ ፳ ፥ ፲፰ ፤ ፲፰ ፥
፭ - ፱ ፤ ፲፮ ፥ ፫ ፤ ፳፫ ፥ ፳ - ፴፫ ፤ ፳፬ ፥ ፶፩ ።
ማርቆስ ፲፪ ፥ ፲፰ ፤ ፮ ፥ ፮ ።
ሉቃስ ፲፪ ፥ ፩ ፤ ፲፫ ፥ ፲፰ ።
ሮሜ ፲፪ ፥ ፱ ።
ያዕቆብ ፫ ፥ ፲፮ ።
፩ኛ ጴጥሮስ ፩ ፥ ፳፪ ፤ ፪ ፥ ፩ ።
የሐዋርያት ሥራ ፳ ፥ ፩ - ፲፩ ።
ኢሳሎ ፮ ፥ ፩ ፥ ፲ - ፲፪ ፥ ፲፱ ፥ ፳፪ ፥ ፳፮ ።

ግብዝነትና አለእውነተኛነት የክርስቲያንነት ማብ ቂያ ጠባዮች ይሆናሉ ።

፩ኛ ጢሞቴዎስ ፬ ፥ ፩ - ፫ ።
፪ኛ ጢሞቴዎስ ፫ ፥ ፳ ።

## ፳፫ኛ ። መስጠት ።

ይህ ጊዜን ዓለማዊ ንብረትንና ገንዘብን ለእግዚአብ ሔር መስጠት ማለት ነው ። ይህም የማይወድቅ የእው ነተኛ ክርስቲያን የፍቅር አድራጐት መግለጫ ነው ። ዳሩ ግን ታዛዥና ዝግጁ አዲስ ልብ ካልኖረ ይህ ሁሉ በእግ ዚአብሔር ፊት ጥቅመ ቢስ ነው ። በብሉይ ኪዳን ዘመን ሰዎች ከመቶ አሥር አስራት እንዲሰጡ በሕግ ታዘዋል ።

ዘፍጥረት ፲፬ ፥ ፳ ፤ ፳፰ ፥ ፳፪ ።
ዘሌዋውያን ፳፯ ፥ ፴ - ፴፪ ።
ነህምያ ፲ ፥ ፴፰ ፤ ፲፫ ፥ ፲ - ፲፪ ።
ሚልክያስ ፫ ፥ ፰ - ፲ ።
ዘኊልቊ ፲፰ ፥ ፳፩ ፥ ፳፬ ።
ዘዳግም ፲፪ ፥ ፮ ፤ ፲፬ ፥ ፳፪ - ፳፮ ፥ ፳፱ ።

ምሳሌ ፫ ፡ ፱ን ከዕብራውያን ፮ ፡ ፱ - ፲ ጋር
　　እመዛዝን ።

በአዲስ ኪዳን ክርስቶስ ፈሪሳውያን የሚያደርጉትን የታይታ ወግ በመዝለፍ ድሀና በለጸጋ ሳይለይ የሚሰጠውን የአዲስ ልብ ስጦታ በጠለቀ መንገድ ይገልጸው ነበር ።

አሥራት መስጠት የሚያዘልፍ ነገር አይደለም ። ነገር ግን ለክርስቲያኖች እንደ ሕግ ሆኖ የተደነገገ መሆን የለበትም ።

አሥራትን ለእግዚአብሔር በመስጠት ብዙ ክርስቲያኖች የብልጽግናን በረከት ተቀብለዋል ።

ማቴዎስ ፳፫ ፡ ፳፫ ።
ሉቃስ ፲፩ ፡ ፵፪ ፤ ፲፰ ፡ ፲፪ ።
ማቴዎስ ፲፱ ፡ ፳ - ፳፪ ።
ዮሐንስ ፫ ፡ ፩ - ፫ ።
ማቴዎስ ፮ ፡ ፩ - ፬ ።
፩ኛ ቆሮንቶስ ፲፫ ፡ ፫ ።
ማቴዎስ ፲ ፡ ፵፪ ።
ሉቃስ ፲ ፡ ፴፬ ፡ ፴፭ ።

በጴንጤቆስጤ ዕለት በግሩም አኳኋን አዲስ ኃይል ተገለጸ ። ሰዎች ለጸጋው መታዘዝንና በክርስቶስ ፍቅር ተገደው መስጠትን ጀመሩ ። ያውም አንዳንዶቹ ያላቸውን ሁሉ ሰጡ ።

ሆኖም ሐናንያ በዚህ መንገድ እንኳ እንደተቀሰፈ ተገልጾአል ።

የሐዋርያት ሥራ ፪ ፡ ፵፬ - ፵፭ ፤ ፬ ፡ ፴፪ ፡ ፴፬ ፡
　　፴፭ ፡ ፴፯ ፤ ፭ ፡ ፩ - ፲፩ ።

እውነተኛ መስጠት የመንፈስ ፍሬ ነው ።
በልብ ውስጥ በጸጋ የተፈጠረ ምኞት ነው ።
ለእግዚአብሔር ፍቅርና ለሰው ደግሞ በአስፈላ

ጊው የነፍስና የሥጋ ችግር መድረስ ነው ። የማይለወጥ የፍቅር ምልክት ነው ። ሰው ለእግዚአብሔር በደንብ እንዲሰጥ ጥንቃቄ ፣ ጸሎትና እራሱን መግዛት ያስፈልገዋል ። ዓለማዊ ዕቃችንንና ገንዘባችንን ለእርሱ በሙሉ ባናስረክብ እርሱ የፈለገውን ሊወስድ ይችላል ።

እኛ ደግሞ የእርሱ ባለአደራዎች እንደሆንን መገንዘብ አለብን ። እራሳችን ደግሞ አገልጋዮች እንደሆንን እናስብ ።

፪ኛ ቆሮንቶስ ፰ ፣ ፯ - ፲፬ ፤ ፱ ፣ ፩ ፣ ፫ - ፰ ።
፩ኛ ቆሮንቶስ ፲፮ ፣ ፩ ፣ ፪ ።
ፊልጵስዩስ ፬ ፣ ፲ ፣ ፲፬ - ፲፰ ።

## ፳፱ኛ ። መጽሐፍ ቅዱስ

## የእግዚአብሔር እስትንፋሳዊ ቃል ።

ባለፉት ዘመናት የመጽሐፍ ቅዱስ ጸሐፊዎች በመንፈስ ቅዱስ ቃለ አስተዋጽኦና የመሪነት ሐሳብ ተደግፈው ጻፉት ።

ስለዚህ በነሱ የተጻፈው ቃል ስሕተት የለበትም ። በእርግጥ ይህ የእግዚአብሔር ቃል ነው ።

ይህንንም ስንል ጸሐፊዎቹ እንደ ጽሑፍ መሣሪያ ሆኑ ማለታችን አይደለም ። ነገር ግን ስሕተት ከሆኑ ታሪኮችና ገለጻዎች በመንፈስ ቅዱስ ተጠበቁ ማለታችን ነው ። የእግዚአብሔር እስትንፋሳዊ የቃል ጽሑፍ በግሪክ ቴኦፒኒስቶስ የእግዚአብሔር እስትንፋስ በሚለው ተተክቶ ይገባል ። (፪ኛ ጢሞቴዎስ ፫ ፣ ፲፮)

መጽሐፍ ቅዱስ በእግዚአብሔር እስትንፋሳዊ ቃል ተጻፈ ብሎ መግለጽ አስቸጋሪ እንደ መሆኑ ሁሉ ፣ በዚሁ መጠን ጌታችን ከድንግል ማርያም በመንፈስ ተፀነሰ ብሎ ማስረዳቱም አስቸጋሪ ነው ።

ስለዚህ በመለኮታዊ አምላክነት ካመንን የመጽሐፉ በሙሉ በአምላክነቱ እስትንፋስ መሪነት መጻፍ አያጠራጥረንም ።

መጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ የእግዚአብሔር ቃል ለሰዎች እንደተነገረ ይገልጻል ። በመከታተል «የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል ።» «የእግዚአብሔር ቃል እንዲህ ሲል ወደኔ መጣ» ይላል ።

ኢሳይያስ ፩ ፡ ፪ ፤ ፳፰ ፡ ፲፬ ፡ ፳፪ ።
ኤርምያስ ፫ ፡ ፲፬ ።
፪ኛ ጴጥሮስ ፩ ፡ ፳ ፡ ፳፩ ።
፪ኛ ጢሞቴዎስ ፫ ፡ ፲፮ ።
ዘጸአት ፬ ፡ ፲፫ ፤ ፳፬ ፡ ፬ ፡ ፯ ፤ ፴፪ ፡ ፲፮ ።
ዘዳግም ፴፩ ፡ ፳፬ ።
መዝሙር ፳፪ (፳፫) ፡ ፲፩ ።
ሕዝቅኤል ፪ ፡ ፯ ፤ ፫ ፡ ፫ ።
ዘካሪያስ ፯ ፡ ፯ ።
፩ኛ ተሰሎንቄ ፪ ፡ ፲፫ ።

የሚቀጥለው የሚያስረዳው ባንድ በተወሰነ ወቅት ቀጥተኛ አምላካዊ ትእዛዝ ለቃሉ መጻፍ መተላለፉን ያስረዳል ።

ጳውሎስ በቃል ሆነ በጽሑፍ የገለጸው መልዕክቱ በቀጥታ ከእግዚአብሔር ዘንድ እንደመጣ ያስረዳል ።

ሙሴ ፡— ዘጸአት ፲፯ ፡ ፲፬ ።
ኢሳይያስ ፡— ኢሳይያስ ፰ ፡ ፩ ፤ ፴ ፡ ፰ ።
ኤርምያስ ፡— ኤርምያስ ፴ ፡ ፩ ፡ ፪ ፤ ፴፮ ፡ ፩ - ፴፪ ።
እንባቆም ፡— እንባቆም ፪ ፡ ፪ ።
ቅዱስ ዮሐንስ ፡— ራእይ ፩ ፡ ፩ - ፫ ፡ ፲፱ ፤ ፳፩ ፡ ፭ ።
ቅዱስ ጳውሎስ ፡— ሮሜ ፲፮ ፡ ፳፪ ፡ ፳፮ ።
፩ኛ ቆሮንቶስ ፲፬ ፡ ፴፯ ፤ ፲፩ ፡ ፳፫ ።
ገላትያ ፩ ፡ ፲፩ ፡ ፲፪ ።

፩ኛ ጢሞቴዎስ ፪ ፡ ፩ ።
፩ኛ ተሰሎንቄ ፪ ፡ ፲፫ ፤ ፬ ፡ ፲፭ ።
ኤፌሶን ፫ ፡ ፫ ፡ ፬ ።
፩ኛ ቆሮንቶስ ፪ ፡ ፯ - ፲፫ ።

ክርስቶስ ብሉይ ኪዳን በእግዚአብሔር መሪነት እንደተጻፈ ያስረዳል ። በተጨማሪ ከራሱ ሞት በኋላ መንፈስ ቅዱስ በበለጠ የእግዚአብሔርን ቃል እንደሚገልጽ ተስፋ ሰጥቶአል ። ከዚህ በቀር ኢየሱስ የሚናገረው ቃል ሁሉ ባባቱ ሥልጣን እንደ ሆነ ተናግሮአል ።

ማቴዎስ ፬ ፡ ፬ ፡ ፯ ፡ ፲ ፤ ፭ ፡ ፲፰ ፤ ፲፱ ፡ ፬ ፡ ፭ ፤
፳፪ ፡ ፴፩ ፡ ፴፪ ፡ ፵፫ - ፵፭ ፤ ፳፮ ፡ ፶፬ ።
ሉቃስ ፬ ፡ ፳፩ ፤ ፳፬ ፡ ፳፭ ፡ ፳፯ ፡ ፵፬ ፡ ፵፭ ።
ዮሐንስ ፭ ፡ ፵፮ ፡ ፵፯ ፤ ፰ ፡ ፵፯ ፤ ፲፪ ፡ ፵፰ ፤
፲፯ ፡ ፲፬ ፡ ፲፫ ፤ ፲፯ ፡ ፰ ።

መጽሐፍ ቅዱስ በሥልጣን እየተናገረ የሰውን ስሕተት ያሳያል ። እርሱም የመንፈስ ሰይፍ ነው ። የመጽሐፍ ቅዱስን ሰብአዊና መለኰታዊ ልዩነት መግለጽ አስቸጋሪ እንደመሆኑ ሁሉ ፤ የጌታችንንም ሰብአዊና መለኰታዊ ሕይወት ለይቶ ማስረዳት አስቸጋሪ ነው ።

መጽሐፍ ቅዱስ በማንኛውም ዘመንና ሁኔታ እግዚአብሔር ሊያውቁት የሚወደውን ነገር ለመግለጽ ሁል ጊዜ ዝግጁ ሲሆን ለመረዳት አራሳቸውን ላዘጋጁ ሁሉ በመንፈስ ቅዱስ መሪነት ያስረዳል ።

እግዚአብሔር መጽሐፍ ቅዱስ እንዲነበብና ሊማሩት እንዲገባ ያዛል ።

ኤፌሶን ፩ ፡ ፲፯ ።
ቆላስይስ ፬ ፡ ፲፮ ።
፩ኛ ተሰሎንቄ ፭ ፡ ፳፯ ።
ሮሜ ፲፭ ፡ ፬ ።
፩ኛ ቆሮንቶስ ፪ ፡ ፲፬ ፡ ፲፭ ።

፪ኛ ጢሞቴዎስ ፫ ፥ ፲፮ ፤ ፬ ፥ ፪ ።
ያዕቆብ ፩ ፥ ፳፩ ፥ ፳፪ ።
፩ኛ ጢሞቴዎስ ፬ ፥ ፲፫ ።
ኢያሱ ፩ ፥ ፰ ።
፪ኛ ነገሥት ፳፫ ፥ ፪ ፥ ፳፬ ።
መዝሙር ፩ ፥ ፩ ፥ ፪ ።
የሐዋርያት ሥራ ፲፯ ፥ ፲፩ ።
መዝሙር ፻፲፰ (፻፲፱) ፥ ፺፯ ።

በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ለሚጨምሩ ወይም ለሚቀንሱ ጥብቅ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶአቸዋል ።

ዘዳግም ፬ ፥ ፪ ።
ማርቆስ ፯ ፥ ፲፫ ።
ራእይ ፳፪ ፥ ፲፰ ፥ ፲፱ ።

## ፴ኛ ። ሰይጣን ።

ሰይጣን ማን ነው ? መጽሐፍ ቅዱስ ብቻ ስለእርሱ ማስረጃ ይሰጣል ። ይህንንም ፍጡር የከበበት ማንኛውም ዓይነት በደልና የሰው ልጅ የመውደቅ ምክንያቶች ናቸው ። እርሱም ከዘመን በፊት በመንግሥት ሰማያት በከፍተኛ ሥልጣን ተቀምጦ የነበረ መልአክ ነበር ። በአንድ ዓይነት መንገድ ማለት የተፈጥሮ አእምሮአችን በማይገምተው መንገድ ኃጢአትን በመሥራት ከዕለታት አንድ ቀን ፍጹምና ያለ ኃጢአት የነበሩትን የሰው ልጆች ከኃጢአት በታች ለመውደቃቸው ምክንያት ሆነ ።

ኢሳይያስ ፲፬ ፥ ፲፪ – ፲፬ ፤
ዘፍጥረት ፫ ፥ ፩ ፥ ፲፬ ፥ ፲፭ ።
ሕዝቅኤል ፳፰ ፥ ፲፪ – ፲፬ ።
ሉቃስ ፲ ፥ ፲፰ ።

ሰይጣን አሁን የት ነው ያለው ? ጊዜያዊ ሥራውስ ምንድርነው ? እርሱ በአየር ላይ ሥልጣን እንዳለው

አለቃ የዚህ ዓለም ገዢ (እምላክ) ነው ።

ዓለምን ትክክል ወዳልሆነው መንገድ ለመምራትና ለማታለል ኃይል አለው። እነዚህም ስስት ፥ በመዓረግ ከፍ ለማለት መመኘትና ፥ በኃጢአት የተሞላ ደስታ ናቸው ። በነዚህም ላይ በተጨማሪ የነፍስ በደነት ፥ ሐዘ ንና ሞትን ይሰጣል ። ሰዎችን ለማሳወር ኃይል አለው ። ክርስቲያኖችን ዓይኖቻቸውን ሸፍኖ እንደዚህ በመሰሉ ስሜቶች ያታልላቸዋል ። እነዚህም እንደሚከተሉት የመ ሳሰሉ ናቸው ።

፩ኛ. መልኩን እንደ ብርሃን መልአክ በማስመሰል ።

፪ኛ. በእርኩስ መንፈስ ምትኃትና በአስማት ፥ ክርስ ቲያን እንደሆኑ አድርጎ በማስመከት ።

፫ኛ. በከፊል እውነት የሆነውን ነገር አግንኖ ያልሆ ነውን በመግለጽ በሚመጣ የክርስቲያኖች መለያየት ።

፬ኛ. ለማጥላላትና እውነት በማስመሰል ክፋትን በማመንጨት ።

ማቴዎስ ፬ ፥ ፰ ፥ ፱ ።
ሉቃስ ፳፪ ፥ ፴፩ ፥ ፴፪ ።
ዮሐንስ ፰ ፥ ፵፬ ፤ ፲፪ ፥ ፴፩ ፤ ፲፬ ፥ ፴ ።
ሮሜ ፭ ፥ ፲፪ - ፲፬ ፤ ፰ ፥ ፳፪ ።
፩ኛ ቆሮንቶስ ፭ ፥ ፭ ።
፪ኛ ቆሮንቶስ ፪ ፥ ፲፩ ፤ ፬ ፥ ፬ ።
ኤፌሶን ፪ ፥ ፪ ፤ ፮ ፥ ፲፪ ።
፩ኛ ጢሞቴዎስ ፩ ፥ ፳ ።
ዕብራውያን ፪ ፥ ፲፬ ።
፩ኛ ጴጥሮስ ፭ ፥ ፰ ።
፩ኛ ዮሐንስ ፪ ፥ ፲፫ ፥ ፲፬ ፤ ፭ ፥ ፲፱ ።
መክብብ ፩ ፥ ፲፬ ።

ለሰይጣን የተወሰነለት ፍጻሜ ምንድር ነው ? የኛ ድል ማድረጊያና ማምለጫ መንገድ ምንድር ነው ? በተ

ፈጥሮ ሥጋችን አማካኝነት ከሚያጠቃን ምህረት ከሌለው ጠላታችን በአንድ መንገድ ብቻ እናመልጣለን ። ሁሉን ነገር ከሚያስችል በየሱስ ክርስቶስ ደም በኩል ከሚገኘው አዲስ ልደት መወለድ ያስፈልጋል ። ምንም በኃጢአተኞች የሾህ አክሊል ቢደፋበት አክሊሉ ተለውጦ የክብር አክሊል ሆኖአል ። ድሉን ተቀዳጅቶአል ። ስለዚህ በደንብ የነቃችሁ ሁኑ ፤ እኔ ዓለምን አሸንፌዋለሁ ። የዚህንም ዓለም አምላክ ሰይጣንን ተቃወሙት ከናንተም ይሸሻል ።

ይህ ድል የዘለዓለም ስለሆነ ሰይጣን እራሱና እርከሰት ሁሉ ለዘለዓለም በእሳት ባሕር ይጣላሉ ። ይህም የሚፈጸመው ትልቁ ጠላታችን ሞት ሲደመሰስ ነው ።

ዮሐንስ ፲፮ ፡ ፲፩ ፡ ፴፫ ።
ሮሜ ፲፮ ፡ ፳ ።
፩ኛ ቆሮንቶስ ፲፭ ፡ ፳፮ ።
ገላትያ ፮ ፡ ፲፬ ።
፩ኛ ዮሐንስ ፪ ፡ ፲፯ ፤ ፫ ፡ ፰ ፤ ፬ ፡ ፬ ፡ ፲፯ ።
፪ኛ ጴጥሮስ ፩ ፡ ፬ ።
ራእይ ፲፩ ፡ ፲፭ ፤ ፳ ፡ ፪ ፡ ፯ ፡ ፲ ።

## ፴፩ኛ ። ሥጋዊ ሞት ።

ሥጋዊ ሞት በዓለም ሁሉ አለ ። ሁሉ ይሞታሉ ፤ ኃጢአት ያልሠሩ ሕፃኖች ፡ ሃይማኖት ያላቸው ሰዎች ፡ በክፉት የተሞሉ ሁሉ አንድ ዓይነት ሞት ይሞታሉ ። ከሁለተኛው ሞት ጋር አንድ አይደለም ። ሁለተኛ ሞት የተባለው የመንፈስ ሞት ሲሆን ከእግዚአብሔር ለዘላለም መለየት ነው ። የሥጋ ሞት ግን ነፍስና ሥጋ ሲለያዩ ብቻ ነው ። ነፍስ ግን አትሞትም ።

ሮሜ ፭ ፡ ፲፪ ፡ ፲፬ ።

ሞት በዓለም ሁሉ የተገኘው ፣ የሞት መነሾ የሆ ነው ኃጢአት በዓለም ሁሉ ስላለ ነው ። መጽሐፍ ቅዱስ ሞት በሰው ምክንያት እንደመጣ ይናገራል ። ሆኖም ይህ ሞት ለእንስሳት እንኳን ደርሶአል ።

ዘፍጥረት ፩ ፤ ፳፬ ፡ ፳፭ ፡ ፴፩ ፤ ፫ ፡ ፲፯ ፡ ፲፱ ።
ሮሜ ፭ ፡ ፲፪ ፡ ፲፰ ፡ ፲፱ ፤ ፰ ፡ ፳፪ ።
ኢሳይያስ ፲፩ ፡ ፮ – ፱ ።

ሥጋዊ መከራና ሞት በመጀመሪያ በእግዚአብሔር ዘንድ የታቀደ አይመስልም ።

የቀድሞ ሰዎች የሕይወት ዘመን ረጅም ነበር ። ሆኖም ይህ በተወርሶ የመጣ የቆየ የሥጋ እርጅናና በሽታ ወደ ሥጋ ሞት ማድረሱ የማይቀር ነው ።

ዓለማዊ ሞት ከዓለም እርክሰት ጋር ጐን ለጐን ይሄዳሉ ።

ዘፍጥረት ፩ ፤ ፳፩ ፡ ፳፫ ፤ ምዕራፍ ፫ን በሙሉ ።
፩ኛ ነገሥት ፲፫ ፡ ፳፬ ።
መዝሙር ፲፫ (፲፬) ፡ ፩ – ፫ ።
ኤርምያስ ፲፯ ፡ ፱ ።
ማርቆስ ፱ ፡ ፵፩ – ፵፫ ።
ገላትያ ፭ ፡ ፲፱ ፡ ፳፩ ።
፩ኛ ቆሮንቶስ ፲፭ ፡ ፳፪ ።
፪ኛ ቆሮንቶስ ፭ ፡ ፲ ።
፩ኛ ጴጥሮስ ፩ ፡ ፳፬ ።

ክርስቶስ ለኛ ሲል እራሱን ለሥጋዊ ሞት አሳልፎ በመስጠት ድል አድርጐ መቃብሩ ባዶውን ተገኘ ። ምድራዊው ሰውነቱ በመቃብር አልተገኘም ። ድል በመንሳት በሦስተኛው ቀን ተነሣ ። የጻነ ሰው በዚህ መመራት ተገቢው ሥነ ሥርዓት ሲሆን በዚህም ላይ ሞትን መፍራት የለበትም ። እንደ ቅዱስ ጳውሎስ ጌታውን ለማየት መና

ፈቅ አለበት ። ነገር ግን ክርስቶስን አልቀበልም የሚለ ውን ሰው የጨለማው ፍርሃት አይለቀውም ።
(ዮሐንስ ፫ ፣ ፴፮ ።)

ዮሐንስ ፳ ፣ ፫ - ፱ ።
የሐዋርያት ሥራ ፪ ፣ ፳፬ ።
ፊልጵስዩስ ፩ ፣ ፳፩ ፣ ፳፫ ።
፩ኛ ተሰሎንቄ ፬ ፣ ፲፫ ፣ ፲፰ ።

እግዚአብሔር የሕያዋን አምላክ ነው ። በክርስቶስ ለመንግሥቱ የተለዩት ወደ እግዚአብሔር በዓይነ ቅዱ በት ይቀርባሉ ። ከክርስቶስ ጋር ያርፋሉ ። ይኸውም ከዓለም ጉዞአቸውን ጨርሰው በሰላምና በእረፍት ይቀመ ጣሉ ። (ፊልጵስዩስ ፩ ፣ ፳፫ ።)

ዕብራውያን ፱ ፣ ፳፯ ።
ራእይ ፳፩ ፣ ፯ ፣ ፯ ።
ዮሐንስ ፭ ፣ ፳፬ ።
ሉቃስ ፲፯ ፣ ፳፫ ፣ ፳፯ ፤ ፳ ፣ ፴፯ ፣ ፴፰ ።
፩ኛ ዮሐንስ ፩ ፣ ፯ ።

## ፴፱ኛ ። መንፈሳዊ ሞት ።

መንፈሳዊ ሞት ማለት ፍጡራዊ ሰው በኃጢአት ከእግዚአብሔር ተለይቶ የቆመበትን አቋም የሚያሳይ ሲሆን ይኸው ሰው ተመልሶ ዳግመኛ መወለድ እንደሚ ገባው የሚያሳስብ ነው ።

መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚነግረን ከእግዚአብሔር ለዘለዓለም የተለየ ነውና ሳይለወጥ ወደ መንግሥተ ሰማ ያት ለመግባት አይችልም ይለናል ።

ሰው በምድር በሚያሳልፈው ዘመኑ ክርስቶስን ሊክድ ወይም ሊያምን ይችላል ፤ ዳሩ ግን በዚህ እቅዱ የመጨረሻ ውጤቱ ይጠብቀዋል ።

ዘፍጥረት ፪ ፥ ፲፯ ።
ሕዝቅኤል ፲፰ ፥ ፬ ።
ሮሜ ፭ ፥ ፲፪ ፤ ፮ ፥ ፲፮ ፥ ፳፫ ፤ ፰ ፥ ፮ ፥ ፲፫ ።
፩ኛ ቆሮንቶስ ፲፭ ፥ ፳፩ ፥ ፳፪ ።
ማቴዎስ ፰ ፥ ፳፪ ።
ሉቃስ ፲፭ ፥ ፳፬ ።
ዮሐንስ ፭ ፥ ፳፬ ፥ ፳፭ ።
ኤፌሶን ፪ ፥ ፩ - ፫ ፤ ፬ ፥ ፲፯ ፥ ፲፰ ።
ቆላስይስ ፪ ፥ ፲፫ ።
፩ኛ ዮሐንስ ፭ ፥ ፲፪ ።

የሰው ነፍስ ለዘለዓለም ነዋሪ ነው ። አሁን በዓለም ሳለ የእግዚአብሔርን ይቅርታ ካልተቀበለ ነፍሱ ለዘለዓለም ከእግዚአብሔር የተለየች ትሆናለች ። ይህም ከሥጋዊ ሞት ጋር የሚመዛዘን አይደለም ።

ሉቃስ ፲፫ ፥ ፳፬ - ፳፯ ።
፪ኛ ቆሮንቶስ ፮ ፥ ፪ ።
ማቴዎስ ፳፭ ፥ ፵፮ ።

ይህ ዘለዓለማዊ ሞት በመጽሐፍ ቅዱስ ሁለተኛ ሞት ተብሎ ተሰይሟል ።

መጽሐፍ ቅዱስም እየደጋገመ ይህ ሁለተኛ ሞት ከእግዚአብሔር ተለይቶ ኀዘን በማይለቅበት ቦታ መኖር መሆኑን ይናገራል ። ነገር ግን ሰይጣን ፥ ኃጢአትና ሞት በመስቀሉ ተሸነፉ ። ሆኖም ይህ ነፍሳዊ ሞት በአማኝ ላይ ምንም ሥልጣን የለውም ። ስለዚህ በዚህ ይዞታ ላሉት ዳግመኛ ሞት ሥልጣን እንደሌለው እንረዳለን ።

ማቴዎስ ፲፫ ፥ ፵፪ ፥ ፵፱ ፥ ፶ ።
ራእይ ፪ ፥ ፲፩ ፤ ፳ ፥ ፮ ፥ ፲ ፥ ፲፬ ፥ ፲፭ ፤ ፳፩ ፥ ፰ ።

## ፴፫ኛ ። ሥጋዊና መንፈሳዊ ፈውስ ።

የሥጋና የነፍስ ፈውስ ጥያቄ ኃጢአት ከስገኘው ችግር ጋር ተሳስሮአል ። ኃጢአትና ሥቃይ የማይለያዩ ፣ ከመጀመሪያ በአዳምና በሔዋን ውድቀት የተጀመሩ ናቸው ። የሥቃይ መድኃኒት የሚገኘው ከእጅ ጥበብ ሕክምና እንደ አፕራሲዮን ሌላም ይህን የመሳሰሉና ከእ ምነትም የሚደረግ ፈውስ ነው ። ነገር ግን ከነዚህ ሁሉ አንዱ ብቻ በቂ ነው ብሎ ማሰብ ስሕተት ነው ።

ለአንዳንድ ፈውሶች መጣሪያዎች ያስፈልጋሉ ። ለአንዳንዶች መድኃኒት ያስፈልጋል ። ነገር ግን አንዳን ዶች የአንጎል ሐሳብ ብቻ ይበቃቸዋል ። ከነዚህ ከላይ ከተዘረዘሩት በቀር ከእግዚአብሔር ደኅንነትን ያገኘ ሰው የእግዚአብሔር መንፈስ እንደመራው ለመፈወስ ሰብአ ዊና መለኮታዊ የእምነት ኃይል አለው ።

በብሉይ ኪዳን ዘመን እግዚአብሔር አንዳንድ ጊዜ በተአምራት ይፈውሳ ነበር ።

> ዘጻግም ፲፪ ፣ ፲፫ ።
> ፩ኛ ነገሥት ፲፯ ፣ ፳፩ ፣ ፳፪ ።
> ፪ኛ ነገሥት ፬ ፣ ፴፬ ፣ ፴፭ ፤ ፭ ፣ ፲ - ፲፬ ።
> ኢሳይያስ ፴፰ ፣ ፭ ።

ክርስቶስ ልቡ የተሰበረውን ለመፈወስ እንደመጣ ተናገረ ፤ ለተማረኩትም ነፃነት ለመስበክ ፣ ለታወሩት ብር ሃን ለመስጠት ፣ የቆሰሉትን ለመፈወስ ፣ ለድሆች ወንጌ ልን ለመስበክ መጣ ። እየሰበከ እየፈወሰ ሲመላለስ ደቀ መዛሙርቱም የእግሩን ዱካ እንዲከተሉ አዘዛቸው ። በመድኃኒት ወይም በመጣሪያ አልሠራም ። ነገር ግን በመንፈሳዊ ሥልጣን ይሠራ ነበር ። ክርስቲያኖች በመ ከራ ሁሉ ፣ ምን ዓይነት ጠባይ ሊኖረን እንደሚገባ የመ ልከሙ ሰምራዊ ምሳሌ ተሰጥቶናል ።

ሉቃስ ፬ ፥ ፲፯-፳ ።
ኢሳይያስ ፷፩ ፥ ፩ ፣ ፪ ።
ማቴዎስ ፬ ፥ ፳፫ ፤ ፰ ፥ ፯ ፣ ፲፬-፲፯ ፤ ፲ ፥ ፩ ፣
፯ ፣ ፰ ፤ ፲፪ ፥ ፲፭ ፤ ፲፬ ፥ ፲፬ ።
ሉቃስ ፲ ፥ ፲፯-፳ ፥ ፳፭-፴፯ ።
መዝሙር ፻፫ (፻፪) ፥ ፫ ።
የሐዋርያት ሥራ ፬ ፥ ፳፱ ፣ ፴ ።

ክርስቶስ ሙቶ ከተነሣ በኋላ ለተከታዮቹ የተሰበረን ልብ የሚፈውስና ሌላም ይህን ዓይነት የሚያደርግላቸውን መንፈስ ሰደደላቸው ። እንዲህም ያለ መጽናናት የክርስቲያንን ፍቅር የሚገልጽ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ ነው ።

ስለዚህ እያንዳንዱ ሐኪም በሚያደርገው ሕክምና ከመቅጽበት እንደ እግዚአብሔር የመፈወስ ችሎታ የለውም ። የመርዳትና የማፍቀር ሥራ የጥንቁቅ ክርስቲያን ጠባይ መሆን አለበት ።

ከላይ እንደጠቀስነው ማንኛውም ለሥጋ ፈውስ የሚሰጥ የመድኃኒት እርዳታ ለነፍስ ከሚደረግላት ያዲስ መወለድ እርዳታ ጋር ሲመዛዘን ጥቅመ ቢስ ሆኖ እናገኘዋለን ።

እንደዚሁም በመድኃኒትና በኦፕራስዮን ወይም ደግሞ በልዩ ልዩ የሕክምና ሥራዎች አለማመን ሞኝነት ነው ። ይህም ራዲዮና ማተሚያ ለእግዚአብሔር አገልግሎት ክብር አይጠቀሙም ብለው ከሚገምቱ ጋር ይመሳሰላል ። ክርስቲያኖች በፍጹም ያለኃጢአት ነኝ ለማለት እንደማይችሉ ሁሉ ፥ እንዲሁም ደግሞ በሺታ አይመጣብኝም ለማለት አይችሉም ።

ዮሐንስ ፲፬ ፥ ፲፮-፲፰ ።
ፊልጵስዩስ ፪ ፥ ፳፯ ።
ገላትያ ፬ ፥ ፲፬ን ከ፩ኛ ቆሮንቶስ ፲፫ ፥ ፫ ጋር

አመዛዝን ።

ቆላስይስ ፩ ፡ ፲፩ ።

፪ኛ ቆሮንቶስ ፲፪ ፡ ፯ - ፱ ።

በተለይ አስደናቂ የሆኑት የበሽታ ማስወገጃ ስጦታዎች ለሐዋርያትና ለደቀ መዛሙርቱ ተሰጥተዋል ። ምናልባትም እስከ ዛሬ ድረስ እነዚህ ስጦታዎች ለአንዳንድ ሰው ተሰጥተው ይሆናል ። ሆኖም የእግዚአብሔር ስጦታ ከዘመናዊ የሕክምና መድኃኒት የተለየ ነው ።

የሐዋርያት ሥራ ፫ ፡ ፯-፰ ፤ ፭ ፡ ፲፭ ፤ ፰ ፡ ፲፯ ፤ ፳፰ ፡ ፰ ።

፩ኛ ቆሮንቶስ ፲፪ ፡ ፱ ፡ ፳፰ ።

ያዕቆብ ፭ ፡ ፲፭ ።

በመጨረሻ ፣ ከሥቃይ ለመዳን በዘመናዊ የመድኃኒት መሣሪያዎች መጠቀም አለብን ።

እግዚአብሔር እነዚህ መሣሪያዎች እንዲኖሩን ፈቅዷል ። ነገር ግን እነዚህ መሣሪያዎች አንዳንድ ጊዜ አይረዱም ። ሆኖም የእግዚአብሔር ሰው በእምነት ጸሎት ሊጸልይ ይችላል ። እግዚአብሔር ሁሉን ቻይ እንደ ሆነ ሁልጊዜ ማስታወስ አለብን ።

እርሱ ቢፈቅድ ይፈውሳል ። ሁሉን የሚያስብ እርሱ ብቻ ነው ። (ከእናንተ የታመመ ማንም ቢኖር የቤተ ክርስቲያንን ሽማግሌዎች ወደ እርሱ ይጥራ ፤ በጌታም ስም እርሱን ዘይት ቀብተው ይጸልዩለት ። ያዕቆብ ፭ ፡ ፲፬)

፪ኛ ዜና ፲፮ ፡ ፲፪ ።

ሉቃስ ፰ ፡ ፵፫ ።

፪ኛ ቆሮንቶስ ፲፪ ፡ ፯ ።

# ፴፬ኛ ። እውነተኛይቱ ቤተ ክርስቲያን ።

በግሪክ ቋንቋ ኤክሊሲያ ማለት አሁን ቤተ ክርስቲያን ብለን የምንጠራው ነው ። ይኸውም የተጠሩ ወይም የተመረጡ ስብሰባ ማለት ነው ። (የሐዋርያት ሥራ ፯ ፣ ፴፰)

ካቶሊክ የተባለው ቃል ዓለም ሁሉ ማለት ነው ። እውነተኛይቱ ቤተ ክርስቲያን ማለት ከሰይጣን ባርነት የተጠሩና ሁለተኛ የተወለዱ እውነተኛ አማኞች ናቸው ። ይኸውም ከጴንጤቆስጤ ጊዜ ጀምሮ ነው ። እነዚህ ክርስቲያኖች ያልናቸው በሕይወት ያሉና ለእረፍት ያንቀላፉት ናቸው ።

ማቴዎስ ፲፯ ፣ ፲፰ ።
የሐዋርያት ሥራ ፪ ፣ ፲፬ ፣ ፴፰ ።
፩ኛ ቆሮንቶስ ፲፪ ፣ ፲፪ ፣ ፲፫ ።
ኤፌሶን ፩ ፣ ፳፪ ፣ ፳፫ ።
ዕብራውያን ፲፪ ፣ ፳፫ ።

ይህን የተመረጠ ስብሰባ ለመግለጽ መጽሐፍ ቅዱስ አያሌ ምሳሌዎችን ይሰጣል ።

ሀ) በእስራኤላውያን ከግብጽ መውጣት ትመሰላለች ። የተመረጡት ሕዝቦች ከመስዋዕት ደም በታች የሆኑት ነበሩ ።

ዘጸአት ፲፱ ፣ ፯ ።
ዘዳግም ፲ ፣ ፲፭ ።
፩ኛ ጴጥሮስ ፪ ፣ ፱ ።
የሐዋርያት ሥራ ፯ ፣ ፴፰ ።

ለ) በሰው አካል ትመሰላለች ። ይኸውም ስለ ልዩ ልዩ አሠራሩ ነው ።

፩ኛ ቆሮንቶስ ፲፪ ፥ ፲፪ - ፳፯ ።

ኤፌሶን ፭ ፥ ፳፱ ፡ ፴ ።

ሐ) በድንጋይ በመሠራት የተቀረጸችና በቀለማት ያጌጠች ክርስቶስ በሚኖርባት ቅድስት መቅደስ ትመሰላለች ።

፩ኛ ቆሮንቶስ ፫ ፥ ፲፮ ፡ ፲፯ ።

ኤፌሶን ፪ ፥ ፳፩ ፡ ፳፪ ።

፩ኛ ጴጥሮስ ፪ ፥ ፭ ።

መ) ክርስቶስ እራሱ የርሷ ሙሽራ እንደ ሆነ በእውነተኛ የፍቅር ጋብቻ ትመሰላለች ።

ኤፌሶን ፭ ፥ ፳፫ ፡ ፳፱ ፡ ፴፪ ።

ራእይ ፳፩ ፥ ፪ ፡ ፱ ።

ሠ) ታማኝነትና ፍጹም ፍቅር ባላት ለክርስቶስ በታጨች ንጽህት ድንግል ትመሰላለች ። (የእርሷንና የአመንዝራዋን ነገር አስተያይ ። ራእይ ፲፯ ፥ ፲፰)

ማቴዎስ ፳፭ ፥ ፩ - ፲፫ ።

፩ኛ ቆሮንቶስ ፲ ፥ ፳፩ ፡ ፳፪ ።

ከዘጸአት ፳ ፥ ፭ ጋር አመዛዝን ።

፪ኛ ቆሮንቶስ ፲፩ ፥ ፪ ፡ ፫ ።

ዘጸአት ፴፬ ፥ ፲፬ ።

ራእይ ፲፱ ፥ ፯ ።

በዚህ ዘመን በዓለም ከሁለት መቶ የሚበልጡ በክርስቲያን ስም የሚጠሩ ክፍሎች አሉ ። እውነተኞች ክርስቲያኖች ግን ለእግዚአብሔር ያልተሰወሩ የማትታየው ቤተክርስቲያን አባል የሆኑ አንድ አካል ያላቸው የእውነተኞች አማኞች ጉባኤ ነው ።

ኤፌሶን ፬ ፥ ፬ ።

ዮሐንስ ፲፯ ፥ ፳፩ ።

የሐዋርያት ሥራ ፱ ፥ ፴፩ ።

፩ኛ ቆሮንቶስ ፲ ፥ ፴፪ ፤ ፲፪ ፥ ፳፰ ፤ ፲፭ ፥ ፱ ።

፪ኛ ቆሮንቶስ ፮፡ ፲፬ - ፲፰ ።
ኤፌሶን ፭፡ ፳፪፡ ፳፫ ፤ ፪፡ ፲፱ ።
ማርቆስ ፲፮፡ ፲፰ ።
የሐዋርያት ሥራ ፪፡ ፵፪ ።
ኢሳይያስ ፩፡ ፱ ።
ሮሜ ፲፩፡ ፪ - ፭ ።
ማቴዎስ ፲፫፡ ፵፯፡ ፵፰ ፤ ፳፰፡ ፲፱፡ ፳ ።
፪ኛ ጢሞቴዎስ ፪፡ ፲፱፡ ፳ ከ፩ኛ ነገሥት ፲፱፡ ፲፰ ጋር አስተያይ ።
፩ኛ ዮሐንስ ፪፡ ፲፱ ።

ይህች የምትታየው ከእውነተኛዋ ቤተ ክርስቲያን ጋር አንድ አይደለችም ።

እውነተኛይቱ ግን በክርስቶስ ስም ሁለትም ሆነ ሦስትም ሆነው በአንድነት የተሰበሰቡባት ቤተ ክርስቲያን ናት ። እውነተኛዎቹም ክርስቲያኖች በበጉ የሕይወት መጽሐፍ ስማቸው የተጻፈ ሰዎች ናቸው ። ይህ ደግሞ በምትታየው ቤተ ክርስቲያን መዝገብ ውስጥ መጻፍ ማለት አይደለም ። (የይሁዳንና የሰማርያን ቤተ ክርስቲያን ከንድዋ እውነተኛ ቤተ ክርስቲያን ጋር አመዛዝን ። የሐዋርያት ሥራ ፱፡ ፴፩) እነዚህ ደግሞ የሚታዩ ቤተ ክርስቲያኖች ናቸው ። (ገላትያ ፩፡ ፳፪)

የሚታየው ቤተ ክርስቲያን በክርስቶስ አማኝ ስብሰቦች ናቸው ።

የሚሰበሰቡትም ለጸሎት ፣ ለምስጋና ፣ እንጀራን ለመቁረስ ፣ ወንጌልን ለማስፋፋትና ምክር ለመቀበል ነው ። እንደዚህ ባለው ስብሰባ የሚሰበሰቡት በደንብ እንዲከሄዱ አንድ መሪ ያስፈልጋቸዋል ። ይህ ደግሞ መንፈሳዊ ሥራ ነው ።

በመጀመሪያ ጊዜ የነበሩ መሪዎች ሽማግሌዎችና ዲያቆናት ተብለው ይጠሩ ነበር ።

## ማስገንዘቢያ ።

ሽማግሌ የተባለው ቃል ከአይሁዳውያን ሃይማኖታዊ ስብሰባ የተወሰደ ቃል ነው ።

ኤጲስ ቆጶስ የተባለው ቃል የተወሰደው ከግሪኮች ተራ ሰው ስብሰባ ነው ።

በሚታየው ቤተ ክርስቲያን የስንዴና የእንክርዳድ ጠባይ ያላቸው ክርስቲያኖች ስላሉ እስከ ክርስቶስ ምጽአት እንዲሁ ይቆያሉ ። ከዚህ የተነሣ በዚህ በሚታይ ቤተ ክርስቲያን አብዛኛውን እውነተኛ አንድነት የለም ። ነገር ግን በክርስቶስ አንድ በሆኑት እርግጠኛ አንድነት አለ ። ሆኖም አንዱን የክርስቲያን ሥርዓተ ክፍል ብንይዝ ከክርስቶስ ጋር ላለን መንፈሳዊ አንድነት ዋስትና ሊሆነን አይችልም ።

ማቴዎስ ፲፰ ፥ ፲፭ - ፲፯ ፣ ፳ ፤ ፲፫ ፥ ፳፬ - ፴ ።
ፊልጵስዩስ ፩ ፥ ፩ ፤ ፬ ፥ ፫ ፣ ፲፬ - ፲፰ ።
ራእይ ፫ ፥ ፭ ፤ ፳ ፥ ፲፪ ፣ ፲፭ ፤ ፳፩ ፥ ፳፯ ፤
ፃ፪ ፥ ፲፬ ።
የሐዋርያት ሥራ ፪ ፥ ፵፪ - ፵፯ ፤ ፳ ፥ ፯ ፤ ፳ ፥
፩ - ፫ ፤ ፲፫ ፥ ፩ - ፬ ።
ሮሜ ፲፮ ፥ ፭ ።
፩ኛ ቆሮንቶስ ፭ ፥ ፫ - ፭ ፤ ፲፬ ፥ ፳፮ ፤ ፲፮ ፥ ፲፱ ።
ቆላስይስ ፬ ፥ ፲፭ ፣ ፲፮ ።
ዕብራውያን ፲ ፥ ፳፭ ።
፩ኛ ጢሞቴዎስ ፫ ፥ ፲፭ ።
ዘጸአት ፲፪ ፥ ፴፰ ።
ዘኁልቁ ፲፩ ፥ ፬ ።

# ፱ኛ ። ቅስና ።

ከአዳም ውድቀት በኋላ እግዚአብሔር ለሰው ልጅ የይቅርታንና የደኅንነትን መንገድ በመስቀሉ በኩል አዘ ጋጀ ። አቤል ፥ ኖኅ ፥ አብርሃም ደግሞ ሌሎች እግዚአብ ሔርን የሚፈሩ ሰዎች በደል የሌለውን ጥበት እያረዱ የበደላቸውን ይቅርታ በመቀበል ሕሊናቸውን ያድሱ ነበር ። (ዕብራውያን ፲፩ ፥ ፬)

በላቲን ሳከርዶስ ማለት የሚሰዋ ቄስ ማለት ነው ። በዚህ ዓይነት አንድ የቤተሰብ ሐላፊ ለቤተሰቡ መሥዋ ዕት ይሰዋል ። ከዚህም በቀር እንደመልከጼዴቅ ያሉ ንጉሦችና መኳንንቶች ለሕዝቦቻቸው መሥዋዕት ይሰው ነበር ። ስለዚህ አሁንም የወትሮው ሳይለወጥ የኃጢአት ይቅርታ የሚገኘው በእምነትና በደም በኩል ነው ።

ዘፍጥረት ፬ ፥ ፬ ፤ ፰ ፥ ፳ ፥ ፳፩ ፤ ፲፪ ፥ ፯ ፤ ፲፫ ፥
፲፰ ፤ ፲፬ ፥ ፲፰ ፤ ፳፮ ፥ ፳፭ ፤ ፴፩ ፥ ፶፬ ።
ኢዮብ ፩ ፥ ፭ ።

ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ሰው አመጸኛ ሆኖ እግዚአብ ሔር የሰጠውን መንገድ ንቆ ሕገወጥን መሥዋዕት በቀረ በው በቃየን መንገድ ተከተለ ። የሰዶምና የአረማውያን ሃይማኖቶች ሁሉ እግዚአብሔር ከሰጠው አምልኰ የተ ለዩ ናቸው ።

ስለዚህ እግዚአብሔር ዝቅተኛ የሆነውን የአይሁድ ዘር ለክህንነት በንጽሕና በማስቀመጥ ለእምቢተኛው ዓለም ምሳሌ እንዲሆን መረጠው ። በአንድ ሐሳብ አማኞ ችን ሁሉ ቀሳውስት ለማለት ይቻላል ።

ዘጸአት ፲፱ ፥ ፭ ፥ ፮ ፤ ፴፪ ፥ ፮ ፥ ፳፭ ።
ዘዳግም ፯ ፥ ፮ ።
ዘኍልቁ ፳፭ ፥ ፩ ፥ ፪ ።

ከተመረጠው ዘር (አይሁድ) ለመሥዋዕትነት የአገልግሎት ሥራ እንዲሠሩ የሌዋውያን ነገድ በእግዚአብሔር ትዕዛዝ ተመረጡ። ነገር ግን ይህ የተመረጠው ዘር ወደቀ። የተለየ ጠባያቸውን ጥለው እንደ ሌሎች አሕዛብ ንጉሥ እንዲነግሥላቸው ፈለጉ። ከዚህም በቀር የሕዝቡ አመጽ እየበረታ በመሄዱ ጣዖቶችን ተከተሉ። በኋላም ወደ ኋላ የተንሸራተቱት ቀሳውስት ክርስቶስን ሰቀሉት። ክርስቶስም ለዓለም ሁሉ የእግዚአብሔር በግ ሆኖ በመሞት መጽሐፍ ቅዱስ የተናገረውን ፈጸመ።

ዮሐንስ ፩ ፥ ፳፱ ፤ ፲፱ ፥ ፴ ።
ዘጸአት ፳፰ ፥ ፩ ።
ዘኁልቁ ፫ ፥ ፭ - ፲፱ ።
ዘዳግም ፴፪ ፥ ፲፭ - ፲፯ ።
መሳፍንት ፪ ፥ ፲፯ - ፲፱ ።
፩ኛ ሳሙኤል ፰ ፥ ፭ - ፱ ፥ ፲፱ ፥ ፳ ።
፪ኛ ነገሥት ፲፯ ፥ ፲፭ - ፲፰ ።
፪ኛ ዜና ፴፮ ፥ ፲፬ - ፲፯ ።
ኢሳይያስ ፳፰ ፥ ፯ ።
ኤርምያስ ፭ ፥ ፴፩ ።
ሆሴዕ ፯ ፥ ፱ ።

የሚታየው የመሥዋዕት ጊዜ እንደዚህ ባለ አኳኋን እንዳለቀ ክርስቶስ መጥቶ ሞተ። ለዓለም ደሙን አፈሰሰ። ከዚህ ቀደም ሲደረግ የነበረው መሥዋዕት የዚህ ምሳሌ ብቻ ነበር። ይህ ደግሞ ከእግዚአብሔር ለሰው የተሰጠ መጨረሻው የመዳኛ መንገድ ነው።

ከጸጋ ዘመን ጀምሮ አዲስ ነዋሪ መንገድ ተከፈተ። በቅድስተ ቅዱሳት የነበረው መጋረጃ ተቀደደ። እንደገና የሰው ልጅ ከእግዚአብሔር ጋር ለመገናኘት ቻለ። ስለዚህ አማኞች ቀሳውስት ናቸው። በዚህም ምክንያት አማኞች እንደዚህ ያሉትን መንፈሳዊ መሥዋ

ዕቶች ለእግዚአብሔር ያቀርባሉ። እንግዲህ፣ ወንድሞች ሆይ፥ ሰውነታችሁን እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝና ሕያው ቅዱስም መሥዋዕት አድርጋችሁ ታቀርቡ ዘንድ በእግዚአብሔር ርኅራኄ እለምናችኋለሁ፤ እርሱም ለአእምሮ የሚመች አገልግሎታችሁ ነው። ሮሜ ፲፪፥፩ እግዚአብሔር አሁን አዲስ የተመረጡ ሰዎችን ለእውነተኛዋ ቤተ ክርስቲያን ከዓለም ሰዎች ሁሉ ይጠራል። (በግሪክ) ኢክሊዚያ ይባላል። ይኸውም ጠርቶ ማውጣት ማለት ነው።

ሮሜ ፲፪፥፩።
ዕብራውያን ፲፥፲፱-፳፪፤ ፲፫፥፲፭።
፩ኛ ጴጥሮስ ፪፥፱።
ራእይ ፩፥፮፤ ፭፥፱፣፲።

እውነተኛዋ ቤተ ክርስቲያን የማትታይ ብትሆንም እንኳ የሚታዩ ስብሰባዎች አላት። ክርስቶስና ቅዱስ ጳውሎስ እንዳቆሙት ለጸሎት፣ ለምስጋናና፣ እንጀራን ለመቁረስ መሰብሰብ አለባት። የቤተ ክርስቲያን ሐላፊዎች ያስፈልጋሉ። (እውነተኛዋ ቤተ ክርስቲያን የሚሉትን የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች ተመልከቱ።) ነገር ግን እነዚህ መንፈሳዊያን በእግዚአብሔርና በሰው መካከል አስታራቂ ሆነው የሚቆሙ አይደሉም። ክርስቶስ ሁለትም ሆነ ወይም ሦስት ሆነው በስሜ በተሰበሰቡበት ስፍራ እገኛለሁ ብሎአል።

የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌ ወይም መሪ በእግዚአብሔር የተጠራ፣ በምዕመናን የተመረጠና በመንፈስ የተሞላ፣ መሆን አለበት።

እርሱም ትሑትና እረኝነቱን በሥነ ሥርዓት የሚመራ የድርጅቱ አቋቋሚ ነው። ለተሰበሰቡት ሰባኪ ነው። ሌሎችም የሚያስተምራቸው ሥርዓቶች አሉ። እነርሱም ቅዱስ ቁርባንና የስብከቱ ሥርዓቶች ናቸው።

የተመረጠው ሰው በጎቹን የመጠበቅ ሐላፊነት አለው ። ነገር ግን ጌታ ለመሆን ከመቀናጣት ይጠንቀቅ ። (፩ኛ ጴጥሮስ ፭ ፥ ፪ ፥ ፫)

ማቴዎስ ፲፰ ፥ ፳ ።
የሐዋርያት ሥራ ፮ ፥ ፫-፮ ፤ ፲፫ ፥ ፩ ፥ ፪ ፤ ፲፬ ፥ ፳፫ ፤ ፳ ፥ ፯ ።
፩ኛ ቆሮንቶስ ፲፬ ፥ ፳፮-፴ ፤ ፬ ፥ ፩ ።
ኤፌሶን ፩ ፥ ፳፪ ፥ ፳፫ ።
፩ኛ ጢሞቴዎስ ፫ ፥ ፩ ፤ ፭ ፥ ፲፯ ።
ቲቶ ፩ ፥ ፭ ፥ ፯ ።
፩ኛ ጴጥሮስ ፪ ፥ ፭ ፥ ፱ ፤ ፭ ፥ ፩-፫ ።
ያዕቆብ ፭ ፥ ፲፬ ።

## ማስገንዘቢያ ።

፩ኛ ካህን የተባለው ቃል ሁለት ትርጉም አለው ። እንደ መጽሐፍ ቅዱስ አገላለጽ ይህ ስም በመጀመሪያ ጊዜ መሥዋዕት ለሚያቀርብ ቄስ የተሰጠ ስም ነው ። በዕብራይስጥ ኮኸን ፥ በግሪክ ሄራስ ይባላል ።

በክርስቲያን ሰባኪዎች መጽሐፍ ውስጥ በግሪክኛ ፕረስቡተርስ የሚል ጽሑፍ እናገኛለን ። ትርጉሙም ሽማግሌ ማለት ነው ።

እያንዳንዱ በላቲን ቋንቋ የታተመ መጽሐፍ ይህን ቃል ይጠቅሳል ። የብሉይ ኪዳን ካህንና የአዲስ ኪዳን ሽማግሌ በሐሳብም ሆነ በሥራ በመጠኑ ይለያያሉ ።

፪ኛ አዲስ ኪዳን ማንም ከቄስ ትውልድ የሆነ ሥልጣን እንዲሰጠው አላዘዘም ። ከማቴዎስ ጀምሮ እስከ ራእይ ቄስ የተባለው ቃል ከሚከተሉት አርዕስቶች በታች ይገኛል ።

ሀ) የአይሁድ ካህናት ።

ለ) ኢየሱስ ክርስቶስ የኛ የካህናት አለቃ እንደ ሆነ ።

ሐ) ተራ ክርስቲያን ።

ቅዱስ ጴጥሮስ በጻፈው መልእክት ስለ መሪዎች እንዲህ ይላል ፤ እንግዲህ እኔ ፣ ከእነርሱ ጋር ሽማግሌ የክርስቶስም መከራ ምስክር ደግሞም ሊገለጥ ካለው ክብር ተካፋይ የሆንሁ ፣ በመካከላችሁ ያሉትን ሽማግሌዎች እመክራቸዋለሁ ፤ በእናንተ ዘንድ ያለውን የእግዚአብሔርን መንጋ ጠብቁ ፤ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ በውድ እንጂ በግድ ሳይሆን ፣ በበጐ ፈቃድ እንጂ መጥፎውን ረብ በመመኘት ሳይሆን ጐብኙት ፤ ለመንጋው ምሳሌ ሁኑ እንጂ ማኅበሮቻችሁን በኃይል አትግዙ ። የእረኞችም አለቃ በሚገለጥበት ጊዜ የማያልፈውን የክብርን አክሊል ትቀበላላችሁ ። ፩ኛ ጴጥሮስ ፭ ፣ ፩ - ፬

በተጨማሪም እንዲህ ይላል ፡- እላንተ ደግሞ እንደ ሕያው ድንጋዮች ሆናችሁ ፣ በኢየሱስ ክርስቶስ ለእግዚአብሔር ደስ የሚያሰኝ መንፈሳዊ መሥዋዕትን ታቀርቡ ዘንድ ቅዱሳን ክህናት እንድትሆኑ መንፈሳዊ ቤት ለመሆን ተሠሩ ። ፩ኛ ጴጥሮስ ፪ ፣ ፭

## ፴፺ኛ ። ለውድቀት የሚያደርሱ መንገዶች ።

ወደ ክህደት የሚመራ መንገድ በግሪክ ቋንቋ አፓስታስያ ይባላል ። ትርጓሜውም መውጣት ወይም መውደቅ ማለት ነው ። (፪ኛ ተሰሎንቄ ፪ ፣ ፫)

የመውደቅን ምልክት በምሳሌ የሚያስረዱ መንገዶች አሉ ። በቤተ ክርስቲያን ታሪክ እንደምናገኘው ይህ መውጣት ወይም ክህደት የሚባል እርምጃ ባንድ ጊዜ የሚሆን ሳይሆን ቀስ በቀስ በመሄድ የሚጨምር ነው ።

መጽሐፍ ቅዱስ ስለሚገልጻቸው ሦስት የመውደቅ መንገዶች እናጠናለን ። ከጥንት ጊዜ ጀምሮ ሦስት የስሕ

ተት መንገዶች በእግዚአብሔር ሰዎች ላይ ነበሩ ።

ሀ) ይህ መጀመሪያ በቃየል እንደተጀመረ መስሎ ተገልጸአል ። (ይሁዳ ፲፩) ይኸውም ደም የሌለው መሥዋዕት ነው ። ይህም በአንድ መንገድ መጽሐፍ ቅዱስ ስለ መስቀል የሚሰብከውን ትምህርት አለመቀበል ነው ።

ለ) ሁለተኛው የበለዓም ስሕተት ነው ። ይኸውም ከዓለም ጋር መስማማትን ይገልጻል ።

ሐ) ሦስተኛ የቀሳውስት በቤተ ክርስቲያን የገዥነት ሥልጣን ወደ ኒቆላውያን የሚያመለክት ነው ። (ራእይ ፪ ፥ ፮ ፥ ፲፭)

ሀ) ከእያንዳንዱ የክርስቲያን ሕይወት ጋር አመዛዝነን ስንናገር በቃየል መንገድ ስንል ምን ማለታችን ነው ? ከመጀመሪያ እንመልከት ። ይህ ማለት አንድ ክርስቲያን ከክርስቶስ ደም ሌላ ለኃጢአቱ የይቅርታ መንገድ ሲፈልግ ነው ። በዚህ አድራጎቱ የራሱን የተፈጥሮ አስተዋይነት በመንተራስ ክርስቶስን በምሳሌ የተከተለ በመምሰል ፍላጐቱን ይከተላል ። ይህ የደሙን መንገድ አክፉፍቶ በማኳሰስ የሚያወሳ የአዲሱ የዘመናዊነት ሐተታዊ ገለጻ ነው ።

ስለዚህ እግዚአብሔርን ያወቀ እየመሰለው የልቡ ኃጢአት ስርየትን ሳታገኝ ትኖራለች ። የቃየልን ታሪክ በደንብ እስኪገባን ብናጠና ቃየል ከእግዚአብሔር ሰላም እንዳላገኘ እንረዳለን ። ቃየል እግዚአብሔር መሥዋዕቱን ወደተቀበለለት ወንድሙ ተመልክቶ ቅንአትና ቁጣ በልቡ ሞላ ። የማያቋርጥ ቁጣ ከኃጢአት ያለመንጻት ምልክት ነው ። አንዳንድ ክርስቲያኖች የቃየል መንገድ ወዳልነው የውድቀት መንገድ ያመራሉ ። (ብዙ ዘመናዊ ቤተ ክርስቲያኖች በዚህ መንገድ በመሄዳቸው ልብን የሚያረካ መልእክት የላቸውም ።)

ዘፍጥረት ፬ ፥ ፩-፲፮ን ከዕብራውያን ፲፩ ፥ ፬ ጋር አመዛዝን ።

ይሁዳ ፩ ፥ ፲፩ ።

ገላትያ ፩ ፥ ፮-፱ ፤ ፪ ፥ ፲፩-፲፮ ፤ ፫ ፥ ፩-፬ ፤ ፮ ፥ ፲፪-፲፬ ።

የሐዋርያት ሥራ ፲፭ ፥ ፩ ፥ ፪ ፥ ፲፱ ፥ ፳፬ ፤ ፳ ፥ ፴ ።

ቆላስይስ ፪ ፥ ፲፮ ፥ ፲፯ ፥ ፳-፳፫ ።

ፊልጵስዩስ ፫ ፥ ፲፰ ፥ ፲፱ ።

፪ኛ ቆሮንቶስ ፲፩ ፥ ፫ ።

፪ኛ ጢሞቴዎስ ፬ ፥ ፫ ፣ ፬ ።

፪ኛ ጴጥሮስ ፪ ፥ ፩ ፥ ፪ ፥ ፲፬ ፥ ፲፭ ።

፪ኛ ዮሐንስ ፯ ።

ለ) የበለዓም መንገድ ባልነው በሁለተኛው የውድቀት መንገድ ምን እናገኛለን ? (፪ኛ ጴጥሮስ ፪ ፥ ፲፭) በጠቅላላው አነጋገር የክርስቲያን ከዓለም ጋር መወዳጀት ማለት ነው ። ይህ ነቢይ በሁለት መንገዶች እንደወደቀ ታሪክ በግልጽ ያስረዳል ።

ሀ) በመንፈሳዊ ስጦታው ለመነገድ ፈለገ ። (ዘኁልቁ ፳፪ ፥ ፲፪ ፥ ፲፰ ፥ ፲፱)

ለ) እስራኤላውያን በጣዖት ራሳቸውን እንዲያረክሱ አስተማራቸው ። (ዘሁልቁ ፳፭ ፥ ፩-፫ ፤ ፴፩ ፥ ፲፮) ክርስቲያን ለሆነ ሰው የሚጠቅሙ የእነዚህ ስሕተቶች ትርጓሜ ከዚህ ይቀጥላል ።

## ክርስቲያን ለሆነ ሰው ።

ሀ) ማንኛውም ክርስቲያን በእግዚአብሔር ሥራ የማይገባ የገንዘብ ወይም የዓለማዊ ጥቅም መፈለግ እንደሌለበት ያስገነዝባል ።

ለ) በዓለማዊነት ይመስላል ። በአንዳች ምክንያት

ነፍሲቱ ክርስቶስ በቂ አይደለም ብላ ታስብና ከዓለም ዓለ
ማዊ ደስታና ማኅበርተኝነትን ትፈልጋለች። በዚህ መን
ፈስ ያለች ቤተ ክርስቲያን በዓለማዊ መንገዶች ገንዘብ
ለማትረፍ ትዋራለች፤ በሥጋዊ እጅ ወይም በሌላ ነገሮች
ትተማመናለች። እነዚህ መንገዶች በመጀመሪያ በጣም
የሚረዱ ይመስላሉ። ዳሩ ግን በመጨረሻው ለመንፈ
ሳዊ ቅዝቃዜና ኃይል ማጣት ምክንያት ይሆናሉ።

ይሁዳ ፲፩፡፲፯።
ማቴዎስ ፯፡፲፭።
ሉቃስ ፲፯፡፲፫።
፪ኛ ቆሮንቶስ ፲፩፡፲፫ - ፲፭።
፩ኛ ጢሞቴዎስ ፯፡፭፡፲።
፪ኛ ጢሞቴዎስ ፫፡፭።
፪ኛ ጴጥሮስ ፪፡፲፯፡፳፡፳፩።

ከሦስተኛው የኒቆላውያንን አድራጐት ከሚያመለክ
ተው ውድቀት ምን እንረዳለን? (ራእይ ፪፡፯፡፲፭)
(ይህን ቃል የሚገልጸውን ማስገንዘቢያ ተመልከት።)
በአሁኑ የክርስቲያኖች የክርስትና ዘመን ውስጥ ክርስቶስ
ሊቀካህን በመሆን የቅድስተ ቅዱሳትን መጋረጃ ቀዶ በከ
ፈተው የቅስና ስርዓት ላይ የተደረበ ሰው ሠራሽ የክህ
ነት ስርዓት አለ። ይህም በቀሳውስትና በሕዝቦች መካ
ከል የተደረገውን የወንድማማች ወዳጅነት የሚለያይ
ነው። ከዚህም በቀር ቀሳውስት በእግዚአብሔርና በሰው
መካከል እንደ አማላጅ ሆነው መቆማቸው ነው። እን
ዲህ ያለው አድራጐት የቄሱና የተቀበዩ ሕዝብ ስሕተት
ነው። ምክንያቱም በክርስቶስ በኩል ያለውን ንጹሕ
እምነት ትተው በዚህ በሚታየው መንገድ ስለሄዱ ነው።
በመጨረሻው ጊዜ በሐሣዊ መሲሕ አጠቃላይነት የሚ
መሩ ኃያል የሆኑ በኋለኛው ዘመን የሚነሡ ከሐዲያን
ክርስቲያኖች እንደሚመጡ መጽሐፍ ቅዱስ በብዙ ቦታ

ይገልጻል ። (ምጽአት የተባሉትን የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች ተመልከት ።) በቀሳውስት መመራትና መገዛት አብዛኛውን ጊዜ ወደ ሃይማኖታዊ ስደት ያደርሳል ።

ኢሳይያስ ፩ ፥ ፬ - ፯ ፥ ፲፫ - ፲፰ ፤ ፰ ፥ ፮ - ፯ ።
ሕዝቅኤል ፰ ፥ ፱ - ፲፯ ።
ቆላስይስ ፪ ፥ ፳ ፥ ፳፫ ።
፩ኛ ጢሞቴዎስ ፮ ፥ ፳ ፤ ፬ ፥ ፩ - ፫ ።
የሐዋርያት ሥራ ፳ ፥ ፳፱ ።
፪ኛ ተሰሎንቄ ፪ ፥ ፫ ፥ ፰ - ፲፪ ።
፪ኛ ጴጥሮስ ፪ ፥ ፩ ፥ ፪ ፥ ፲፫ ፥ ፲፯ ፥ ፲፱ ፥ ፳፪ ።
ራእይ ፫ ፥ ፲፬ - ፲፯ ፤ ፲፫ ፥ ፲፩ - ፲፯ ።

## ማስገንዘቢያ ።

ይቅርታ የሌለው ኃጢአት ። ይህ ይቅርታ የሌለው ኃጢአት በወንጌል የተነገረውን የመጨረሻ ውድቀት የሚያወሳ ይመስላል ። (ማቴዎስ ፲፪ ፥ ፴፩ ፥ ፴፪)

ይህም የሚመጣው በእግዚአብሔር ነገሮች ሐሳቡ በግብዝነት የደነዘዘ እንደሆንና ክርስቶስን ላለመቀበል በልብ የደነደነ እንደሆን ነው ። የመንፈስ ድክመት ከመጣ በኋላ ኃይል የለም ። ምክንያቱም የንስሐ ፍላጐት ከሰው ልብ ይጠፋል ። (፩ኛ ጢሞቴዎስ ፬ ፥ ፪)

የኒቆላውያንና የቆሬ ክህደት ። የዮሐንስ ራእይ ብዙ ምሳሌ ያለው መጽሐፍ ነው ። ይህ ቃል ሚስጢራዊን ምሳሌ ያዘለ እንደመሆኑ መጠን ከሐዲነት ወዳለው ወደ ኒቆላውያን ይዘታ ያመለክታል ።

ትርጉሙን ለማወቅ የቃሉን ግሚስ ትርጉም እንመረምራለን ። ኒቆላውያን የሚለው ቃል ከሁለት ታላላቅ ቃላቶች የተቀዳ ነው ። አንዱ ኒቆዋ የሚለው ክፍል ቃል ማሸነፍ ማለት ነው ። ሁለተኛው የመጀመሪያው ግሚስ ላኑስ የሚለው ቃል ሕዝብ ማለት ነው ። ተጠ

ቃሉ ሲነበብ የሕዝብ የአለአግባብ ማሸነፍ ተብሎ ይጠራል ። ቆሬ በመለኰታዊ ትእዛዝ በታዘዙ ካህናት ላይ እንዳመጸ የአሁኑም ክህነት በመለኰታዊ ትእዛዝ አንዱ ሊቀካህን በሆነው በክርስቶስ ላይ እንደ ማመጽ ሆኖ በብዙዎች ዘንድ ይገመታል ።

## ፴፯ኛ ። መጠጥ የሚያስከትለው ችግር ።

ይህን ትምህርት በትሕትናና በሚያስተውል ሐሳብ እንመልከተው ። የአሳባችንም መጨረሻ በአንድ ጥቅስ ብቻ አይወሰንም ። ከዚህም በቀር መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ዚሁ ነገር ያለውን አስተያየት እንመለከታለን ።

እስቲ ወደ መጽሐፍ ቅዱስ እንሂድና እንደነጸጋ የተባሉትን ታላቅ ነገሮች ተመልክተን መሠረት በሌለው ነገር አሳባችንን ከመምራት እንጠንቀቅ ። (፩ኛ ቆሮንቶስ ፲ ፥ ፱ ፥ ፫) አልኮል ከእርሾ የመጣ ነው ። በጣፋጭ ፍራፍሬ ጭማቂ ውስጥ ይገኛል ። በእርሾ ውስጥ የሚታዩት ጥቃቅን ጀርሞች ቤትም ስፍራ በለ አየር ውስጥ ይገኛሉ ። እነዚህም ጀርሞች በአየር ላይ ባሉ ነገሮች ላይ ተጣብቀው እናገኛቸዋለን ። በአየር ላይ ተንሳፎ የተቀመጠ ጣፋጭነት ያለው ነገር ቢኖር በዚያ ላይ አርፈው በቀላሉ አልኮልን ይሠራሉ ። ሰዎች አልኮልን ከጥንት ጀምሮ እንደሚጠጡ እናውቃለን ። ወይን ምሳሌ በመሆን የአንድ አገርን ለምነት ያሳያል ። ለዚህም ነገር አጠቃላይ ምልክት በመሆን በመጽሐፍ ቅዱስ ብዙ ጊዜ ተጠቅሶ እናገኛለን ። ያም ሆነ ይህ የስካር ኃጢአት መምጫ ነው ። ከግብጽ የወይን ግንድ አወጣህ ።
(መዝሙር ፻፬ (፻፫) ፥ ፲)

ኤርምያስ ፪ ፥ ፳፩ ።
ዘፍጥረት ፱ ፣ ፳ ፣ ፳፩ ፤ ፳፯ ፣ ፴፯ ።
ዘዳግም ፯ ፣ ፲፫ ፤ ፳፩ ፣ ፳ ፣ ፳፩ ።
ምሳሌ ፳፫ ፣ ፳፩ ፣ ፳፱ - ፴፭ ።
ኢሳይያስ ፭ ፣ ፲፩ ፣ ፲፪ ።
ዕንባቆም ፪ ፣ ፲፭ ።

በመጽሐፍ ቅዱስ ዘመን በእስራኤላውያን አገር ከአንድ ዓይነት የበለጠ የተለያየ ዓይነት ወይን ነበር ። በብሉይ ኪዳንም ስለ ወይንና ስለ ሌሎችም ዓይነት መጠጦች ይናገራል ። ኢሳይያስ ፳፯ ፣ ፪ (በዕብራይስጥ ቸመር የሚለው ቃል ትርጉም የሚጣፍጥ ወይን ማለት ነው ።) ፪ኛ ዜና ፪ ፥ ፲ ያይን ፣ (የወይኖቹ ሁሉ ስም ።) ሩት ፪ ፣ ፲፬ (ከምጣጤ) ኢሳይያስ ፳፭ ፣ ፮ (ሽማሪም ፣ ወይኖች) ኢሳይያስ ፵፱ ፣ ፳፮ (ኤሶስ ፣ ወይን)

ወይንን እንደ መድኃኒት አድርገው ይጠቀሙበት ነበር ። ይኸውም በሽታን ከቁስል ላይ ለማስወገድና እንዲደነዝዘውም ለማድረግ ተጠቅመውበታል ። ማርቆስ ፲፭ ፣ ፳፫ (ሕመምን ለማስወገድ ይሰጥ ነበር ።) ሉቃስ ፲ ፣ ፴፬ ፤ ፩ኛ ጢሞቴዎስ ፭ ፣ ፳፫ አንዳንዴም በውኃ ደባልቀው ይጠጡታል ። ምሳሌ ፱ ፣ ፪ ፣ ፭

በዚያን ጊዜ ወይን በብዙ ካልጠጡ በስተቀር የማያሰክር እንደነበር ለማመን በቂ ምክንያት አለ ። ምሳሌ ፳፫ ፣ ፴ ፤ ኢሳይያስ ፭ ፣ ፲፩ ። ከጥንት ጀምሮ ከመጠጥ መለየት የተለመደ ነው ።

አንዳንድ ሰው ለእግዚአብሔር ሲመረጥ በመሐላ የማይጠጣ መሆን ነበረበት ። የናዝራዊያን ሕግ ምን እንደነበረና ቀሳውስቱ በቤተ መቅደስ ውስጥ ከመግባታቸው በፊት እንዳይጠጡ እንደተከለከሉ ለመረዳት የሚከተለውን ተመልከት ።

ዘኍልቁ ፮ ፥ ፩ – ፬ ።
ዘሌዋውያን ፲ ፥ ፰ ፥ ፱ ።
መሳፍንት ፲፫ ፥ ፫ ፥ ፬ ፥ ፲፬ ።
ኤርምያስ ፴፭ ፥ ፮ - ፲፱ ።
ዳንኤል ፩ ፥ ፰ ፥ ፲፪
ሉቃስ ፩ ፥ ፲፭ ፤ ፯ ፥ ፴፫ - ፴፭

ክርስቶስ የደኅንነት መንገድ ወደጠፋበትና በሥራና በሕግ ወደተማረከው የዓለም ሕዝብ መጣ ። ስለዚህ የግ ብዝነትና የአጉል ልማድን ሥርዓት መተው ያስፈልጋል ።

በዚህም ምትክ አዲሱን ነዋሪ የጸጋ የነፃነት ሕይወ ትን ተቀብሎ መኖር ተገቢ ነው ። ለደቀ መዛሙርቱ በሰው የተሠራው ሕግ ሳይሆን እውነተኛው መሪያቸው መንፈስ ቅዱስ እንደሆነ ተነገራቸው ። (በክርስቶስ ደቀ መዛሙርትና በዮሐንስ መጥምቁ ደቀ መዛሙርት መኃል የነበረውን የመለያየት ክርክር ተመልከት ።)

ማቴዎስ ፱ ፥ ፲፫ - ፲፯ ፤ ፲፭ ፥ ፫ ፥ ፮ ፥ ፱ ።
ገላትያ ፭ ፥ ፲፰ ፥ ፳፪ ፥ ፳፫ ፤ ፮ ፥ ፲፭ ።

ከመጠጥ መለየት ወይም መጾም ከሰዎች ምስጋናን ሊያሰጠንና ከሚመጣውም ቀጣት ሊያስመልጠን እንደማ ይችል ክርስቶስ አመልክቶናል ። ነገር ግን ስለ እርሱ ስንል እርሱ የሚፈልገውን እናደርጋለን ። ክርስቶስ አንድ ነገር እንዳናደርግ ቢፈልግና እኛም በፍጹም በፈ ቃዱ ብንማረክ በዚያ በምንፈልገው ነገር ላይ ድልን እና ገኛለን ። ከዚህም በቀር ያን የፍላጐት ምኞት ፈጽሞ ከኛ ሊያስወግደው ይችላል ።

ማቴዎስ ፮ ፥ ፲፮ – ፲፰ ።
፩ኛ ቆሮንቶስ ፲ ፥ ፲፫ ።

ክርስቶስ ያን የፓለስቲን አገር መጠጥ እምቢ ቢል ኖሮ ተከታዮቹ ምናልባት መጠጥ አለመጠጣት ለደኅን ነት ይጠቅማል ብለው ያምኑ ነበር ።

ቆላስይስ ፪ ፣ ፲፯ - ፳፫ ።
ገላትያ ፪ ፣ ፳፩ ።
የሐዋርያት ሥራ ፲፭ ፣ ፩ ፣ ፪ ፣ ፲፩ ፣ ፲፱ ።

ለመጨረሻ ። ያላንዳች ጥያቄ ባሁኑ ዘመን አልኮል ከዓለም መርገምቶች አንዱ ሆኖአል ። የአሁኑ የመጠጥ አጠማመቅ ከድሮው የተለየ ስለሆነ ለጊዜው ክርስቲያኖች አስቸጋሪ ሆኖ ተገኝቶአል ። ስካር ከዋናዎቹ ኃጢአቶች አንዱ ሲሆን የሰው ልጆችም ከእርሱ በለመለየት ተጣምረው ይጓዛሉ ።

ስካር እንደልማድ በተቆጠረበት አገር ከልክ ያለፈ አሳዛኝ የሆነ ነገርና ክፉት ይደረግበታል ። የክርስቲያን ጠባይ ደንብ በአዲስ ኪዳን በግልጽ ተጽፏል ። ቅዱስ ጳውሎስ እንዲህ ይላል ፡-

እላንት ግን እዩ ይህ ችሎታችሁ የደካሞች እንቅፋት እንዳይሆን ። ክርስቶስ እራሱ በግልጽ ያስጠነቅቀናል ፤ የሚያሰናክልም በአንገቱ መጅ ታስሮ ወደ ባሕር ቢጣል እንደሚሻለው ተናግሮአል ። ይህም ክርስቲያን ወንድሙ የሚሰናከልበትን ነገር ማድረግ እንደሌለበት ይገልጻል ።

የአንድ ክርስቲያን የትንሽ መጠጣት እርምጃ ለሌሎች መጥፎ ምሳሌ ነው ። እርሱ እንኳ ባይሰክር ደካማው ወንድሙ የእርሱን ምሳሌ በመከተል ይሰክርና በኃጢአት ይወድቃል ። ስለዚህ አንድ ሰው ወንድሙን በእውነት የሚወድ ከሆነ መጠጥ በፍጹም ይተዋል ። መጠጥ የማያስፈልግበት ሌላው ምክንያት ጠቃሚ በሆነው በእግዚአብሔር ሥራ ላይ ሊውል የሚገባው ገንዘብ በመባከን እንዳይጠፋ ነው ።

ሉቃስ ፲፯ ፣ ፴፩ ።
ሮሜ ፲፫ ፣ ፲፫ ፣ ፲፬ ።
፩ኛ ቆሮንቶስ ፰ ፣ ፲፩ ።

ገላትያ ፫ ፥ ፳፯ ።
ኤፌሶን ፭ ፥ ፲፰ ።
፩ኛ ተሰሎንቄ ፭ ፥ ፯ - ፰ ።
ማቴዎስ ፲፰ ፥ ፯ ።
ሮሜ ፲፬ ፥ ፫ ፥ ፳፩ ።
፩ኛ ቆሮንቶስ ፰ ፥ ፲፩ - ፲፫ ፤ ፯ ፥ ፱ ፥ ፲ ።

## ማስገንዘቢያ ።

በዕብራይስጥ በተጻፈው መጽሐፍ ቅዱስ ወይን በተለያየ ዓይነት ቃላት ተጠቅሶ እናገኛለን ። ወይንን ወይም ሌላውን መጠጥ የሚገልጹ ስድስት የተለያዩ ቃላቶች አሉ ።

ቲሮሽ የሚለው ቃል ገና ትኩስ የሆነ የወይን ጭማቂ ማለት ነው ። ሆኖም ይህ ቃል የፈላውን ወይም የደረቀውን መጠጥ ያመለክታል ። (ሆሴዕ ፬ ፥ ፲፩ ተመልከት ።) ይህ የደረቀ አዲስ ወይን ነው ። ሆኖም አስካሪነቱን ይገልጻል ።

## ፴፰ኛ ። ጥምቀት ።

በጥምቀት ሥነ ሥርዓት ምክንያት ብዙ ያለማስተዋል ክርክር ተደርጎአል ። እስቲ እውነተኛውን ትርጉም ለመረዳት እንሞክር ። በግሪክ ባፕቲዘ ማለት በውኃ ውስጥ ማጥለቅ ወይም በውኃ ማንጻት ማለት ነው ። በግሪክኛው በአዲስ ኪዳን አበባል ይህ ቃል ለዕቃ ማንጻትና ለሰው ማጥመቅ አንድ ዓይነት ትርጉም ይሰጣል ።

(በማርቆስ ፯ ፥ ፬) እንደተገለጸው ከሆነ በቀድሞዎቹ ሰዎች ማለት በክርስቲያኖች ዘመን መርጨትና ማጥለቅ የተፈቀደ ነበር ። ከዚህም የተነሣ በልብ ውስጥ የተደረገው የኃጢአት መንጻትና እምነት በሰዎች ፊት ይታያል ። በእግዚአብሔርም ፊት ትእዛዙ እንደተፈጸመ ይረጋገጣል ።

የጥምቀት ጥንተ አጀማመር ። በውኃ መንጻት በጥንት ሰዎች የተለመደ ነበር ። ይህ ልማድም በብሉይ ኪዳን ጊዜም ነበር ። (ዘጻግም ፳፱ ፥ ፬) በሞላ ሰውነት በወራጅ (በተገደበ) ውኃ መጥለቅ ሥነ ሥርዓታዊ መንጻት ነበር ። (ዘሌዋውያን ፲፬ ፥ ፰ ፥ ፱ ፤ ዘኍልቁ ፲፱ ፥ ፲፫) በሙሴ በተጻፉት የብሉይ ኪዳን የመንጻት ሥነ ሥርዓቶች ላይና በአዲስ ኪዳን የመንጻት ሥነ ሥርዓቶች ላይ አይሁድ በሕላዊ ሥነ ሥርዓታቸውን ጨምረውበታል ።

ክርስቶስ በሥጋ በዚህ ዓለም በነበረበት ጊዜ አሕዛብ ሃይማኖታቸውን ወደ አይሁድነት ሲለውጡ ሥነ ሥርዓቱ በውኃ መንጻት ወይም ጥምቀት ከግዝረት ጋር በኩልነት ደረጃ ይፈጸም ነበር ።

ዘጻግም ፲፱ ፥ ፲ ፤ ፳፱ ፥ ፬ ።
ዘኍልቁ ፰ ፥ ፯ ።
፪ኛ ዜና ፬ ፥ ፪ ፥ ፯ ።
፪ኛ ነገሥት ፫ ፥ ፲ ።
መዝሙር ፶ (፶፩) ፥ ፪ ፥ ፯ ።
ኢሳይያስ ፩ ፥ ፲፯ ።
ዮሐንስ ፪ ፥ ፯ ፤ ፲፩ ፥ ፶፭ ።
ዕብራውያን ፱ ፥ ፲ ።

የዮሐንስ ጥምቀት ። ዮሐንስ መጥምቁ በመጣ ጊዜ በእግዚአብሔር ፈቃድና ትእዛዝ አጠመቀ ። (ዮሐንስ ፩ ፥ ፴፫) ዮሐንስ አዲስ ልማድ አላመጣም ። ነገር ግን ወደኋላ የወደቀው ሕዝብ እንዲመለስና ንስሐ ገብቶ ከእርሱ በኋላ በሚመጣው መሲህ እንዲያምን ነበር ። አዲስ ንስሐ መግባታቸውን በዮርዳኖስ ውኃ በመጠመቅ ገለጹ ። ይህም አድራጐታቸው ከኃጢአት መንጻታቸውን የሚያሳይ ምልክት ነው ። (ማርቆስ ፩ ፥ ፬)

ማቴዎስ ፫ ፥ ፩ - ፯ ።
ማርቆስ ፩ ፥ ፬ ፥ ፭ ።

ሉቃስ ፯፡ ፳፱፤ ፲፮፡ ፲፮ ።

ዮሐንስ ፩፡ ፳፰፡ ፴፱፤ ፫፡ ፳፪-፳፮ ።

**የክርስቲያን ጥምቀት ።** ክርስቶስ ራሱ ወደዚህ ዓለም በመጣ ጊዜ የአይሁድን የጥምቀት ልማድ መረጠ። ተከታዮቹንም ይህን ነገር በአዲስ ሥርዓት እንዲከተሉ አዘዘ። ከክርስቶስ የመስዋዕትነት ሞት በኋላ ቅዱስ ጳውሎስ ጥልቅና ሠፊ ትርጉም በመስጠት ጥምቀትን አብራርቷል ። ከክርስቶስ ወዲህ የጥምቀት ሥነ ሥርዓት በስመ አብ በስመ ወልድ በስመ መንፈስ ቅዱስ እየተከሄደ ነው ። የክርስቲያን ጥምቀት አያሌ አስተያየት አለው ።

ሀ) ክርስቶስን ከልብ እንደተቀበልነው በአሕዛብ መካከል በግልጽ ስንመሰክር የምናሳየው አድራጐት ነው ።

ለ) ወደሚታየው ቤተ ክርስቲያን በአባልነት የመግባታችን ምልክት ነው ።

ሐ) ከኃጢአት የመታጠብ ምሳሌና ለአሮጌው ሕይወት ከክርስቶስ ጋር ተቀብሮ ለአዲስ ሕይወት መነሣትን የሚገልጽ ነው ። (ሮሜ ፮፡ ፬) ይህ ዓይነቱ ተግባር በላቲን ቋንቋ ሳክራሜንት ይባላል ። በውስጥ ያለን ጸጋ የአዲሱ ሕይወት ውስጣዊ ምሳሌ ነው ።

ዮሐንስ ፩፡ ፳፮፡ ፳፱፡ ፴፫፤ ፬፡ ፩፡ ፪ ።
ማቴዎስ ፳፰፡ ፲፱፡ ፳ ።
ማርቆስ ፲፮፡ ፲፮ ።
ሉቃስ ፫፡ ፲፮ ።
የሐዋርያት ሥራ ፩፡ ፭፤ ፪፡ ፴፰፤ ፰፡ ፴፮-
፴፰፤ ፲፡ ፴፯፡ ፵፯፡ ፵፰፤ ፲፩፡ ፲፮፤ ፲፫፡
፳፬፡ ፳፭፤ ፲፰፡ ፳፭፤ ፲፱፡ ፬-፭፤
፳፪፡ ፲፮ ።
ሮሜ ፮፡ ፬-፭ ።

፩ኛ ቆሮንቶስ ፲፪ ፥ ፲፫ ።
ኤፌሶን ፬ ፥ ፬ ፣ ፭ ፤ ፭ ፥ ፳፮ ።
ቆላስይስ ፪ ፥ ፲፪ ፥ ፲፫ ።
፩ኛ ጴጥሮስ ፫ ፥ ፳፩ ።

ለመጨረሻ ። ከእውነተኛ ኑዛዜ ጋር በተቀናጀ መንገድ ሰዎች በክርስቶስ ደም በማመን እንደዳኑ በግልጽ ተረድተዋል ። በዚህ ዓይነት በመጠመቅ የክርስቲያንነትን የቃል ኪዳን ምልክት ምስክርነት ያሳያሉ ።

የጥምቀቱ ሥነ ሥርዓት በማን ሊከሄድ ይገባል ? በመንፈሳዊ አስተያየት ከወሰድነው ማንም ሊያጠምቅ ይችላል ። ሆኖም የግድ የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች ሊያጠምቁ ይገባል ። ይሁንና እግዚአብሔር የሚመለከተው ትልቁ ነገር የጥምቀቱን አቅድ ሳይሆን አዲሱን ልብ ነው ። እንደምንገነዘበው ከሆነ ክርስቶስ በጭራሽ አላጠመቀም ። ቅዱስ ጳውሎስም ቢሆን ጥቂት ሰዎች ብቻ አጥምቋል ።

ዮሐንስ ፬ ፡ ፩ ፡ ፪ ።
፩ኛ ቆሮንቶስ ፩ ፡ ፲፬ ፣ ፲፯ ።

የጥምቀት አቅድና ጠቃሚነቱ ። እንደ ምሳሌው አገላለጽ በማጥለቅ ማጥመቅ የተሻለ መንገድ ነው ። ነገር ግን የመጠመቅ ሁኔታ በውኃ ብዛት ሊሆን እንደሚገባ አድርጎ መታሰብ የለበትም ። እንደዚህ መሆን የሚገባ ቢሆን ኖሮ እግዚአብሔር በግልጽ ይነግረን ነበር ። አማኞች በእምነት ብቻ ስለዳኑ ውጫዊ ድርጊት በሆነው የማጥመቅ ዘዴ መፌፌነቅ የለባቸውም ። ክርስቶስ ራሱ ጥምቀትን የክርስቲያን ኪዳን ምልክት አድርጎ እንደ መረጣት የሚያምኑ ሰዎች የርሷን ቅድስናና አስፈላጊነት ይገነዘባሉ ። አንዳንዶቹ ደግሞ የጌታችንና የቅዱስ ጳውሎስን ትምህርት ከዚህ በተለየ መንገድ ይመለከቱታል ። ይኸውም የጥምቀት ሥነ ሥርዓት ደንብ ተዘርዝሮ አልታዘዘ

ምና ነው ። ስለዚህ የጥምቀት ሥነ ሥርዓት ከእምነትና ከልብ ኑዛዜ ውጭ እምብዛም አስፈላጊ አለመሆኑን ለማ ስረዳት ሳይጠመቅ በእምነት የዳነውን ወንበዴ እንደም ሳሌ አድርገው ያቀርባሉ ። (ሮሜ ፱ ፡ ፳፫ ፡ ፳፱)

ኤርምያስ ፪ ፡ ፳፩ ፡ ፳፪ ። ገላትያ ፩ ፡ ፮ ፡ ፯ ፤
፯ ፡ ፲፩ ። ሮሜ ፲ ፡ ፱ ፡ ፲ ።

የሕፃናት ጥምቀት ። በማያጠራጥር መንገድ በግ ልጽ ስለ ሕፃናት ጥምቀት የሚያስረዳ ከመጽሐፍ ቅዱስ ማግኘት አይቻልም ። ሆኖም የሐዋርያት ሥራ ፪ ፡ ፴፰ ፡ ፴፱ ፤ ፲፮ ፡ ፲፩ ፡ ፴፫ ።

ከቀሩት ጥቅሶች የቀረበ ሐሳብ ይሰጣል ። ይህንን የሚያደርጉ ፕሮቴስታንቶች ኢየሱስ ክርስቶስ ሕፃናትን ወደ እርሱ እንዲያመጡ እንዳዘዘ ሁሉ በዚሁ ዓይነት አሁንም ሕፃናት ወደ እርሱ ከሚመጡት የመጀመሪያዎቹ ሊሆኑ እንደሚገባ አድርገው ስለሚያምኑ ነው ።

ሕፃናት እንዲጠመቁ የሚያደርጉበት ምክንያት በሕፃንነታቸው የጥምቀትን ሥርዓት ከፈጸሙ ይህ አድ ራጐታቸው በደጉ ጊዜ ጌታ ኢየሱስን እንደግል መድኃ ኒታቸው አድርገው ለመቀበል ያደፋፍራቸዋል የሚል እምነት ስላላቸው ነው ። እንዲህ ያለው አድራጐት የሚ ፈጸመው በሕፃናት ብቻ ሳይሆን ኋላ ጌታን እቀበላለሁ አሁን ግን ልጠመቅ ለሚሉ ሁሉ እንደሚደረግላቸው ተረጋግጦአል ። ይህም የሚደረገው ጥምቀቱ ይቅደም እምነቱም ይከተላል የሚል ድንጋጌ ስለኖራቸው ነው ።

ሰው በግል ሐሳቡ ክርስቶስን እንደግል መድኃኒቱ ካልተቀበለ በስተቀር ሁለተኛ መወለድ አይችልም ። በሕ ፃንነታቸው ለሞቱት የተለየ ሐሳብ አለ ። እነዚህ የእግዚ አብሔርን ፍቅር ያልካዱ ስለሆኑ በርሱ ያርፋሉ ።

ሕፃን በመቀደስ ወይም በሌላ ሥራ ሁለተኛ ይወለ ዳል ከማለት እንጠንቀቅ ።

# ፴፱ኛ ። የጌታ እራት ።

ይህ አድራጐት እንጀራ መቁረስ ወይም ቅዱስ ቁርባን ይባላል ። ይህም ሥርዓት ለመጀመሪያ ጊዜ በሰው ቤት ውስጥ ተጀመረ ። ጌታን ለሚወዱ እውነተኛ የተወደደ የፍቅር ግብዣ ነው ። ነገር ግን ለተከታዮቹ አሳፋሪ የጦር ሜዳ ውጊያ ሆኖባቸዋል ። በዚህ በተቀደሰ ሥነ ሥርዓት እንኳን ፣ ክርስቲያንነት የተከፋፈለ ድንጋጌን ይዟል ። ዳሩ ግን ትክክለኛውን ለመረዳት የቀድሞ አመጣጡንና ትርጉሙን ማወቅ ይጠቅማል ። ይህ የተጀመረው የቀድሞውን የአይሁድ የፋሲካ የሌሊት በአልለውጦ ክርስቲያኖች እርሱን ለማስታወሽ ሕብስቱን በመብላትና ወይኑን በመጠጣት እንዲያስቡት ባደረገበት ሌሊት ነው ።

እራሱ ለእርድ የተዘጋጀ የፋሲካ በግ ሳለ በፋሲካ ሌሊት የተበሉትን ሕብስትና ጽዋ እንሥቶ የራሱ አካል ምሳሌ አደረጋቸው ። በተጨማሪም ሥጋው እንደ ሕብስቱ እንደሚቆረስና ደሙም እንደ ወይኑ እንደሚፈስ አስረዳቸው ። እንደምሳሌ የተጠቀመበት ሕብስት እንጂ ሥጋ እንዳልሆነ በምልክት አስረድቶአል ።

እውነተኛው መስዋዕት እስኪሟላ ድረስ እንደ ጥላ ወይም እንደ ሥዕል በመሆን የቆሙትን የብሉይ ኪዳን ሥርዓቶች ፈጽሞ እራሱ እውነተኛው መስዋዕት ሆነ ።

ከዚህ የተነሣ የፋሲካው በዓል ወደ ጌታ እራት ተለወጠ ። ይህንኑ ለማብራራት ቅዱስ ጳውሎስ በ፩ኛ ቆሮንቶስ ፲፩ ፣ ፳፫ ላይ መግለጫ ሰጥቶአል ።

(በግሪክ ኡካሪስቲአ የሚለው ቃል ምስጋና መስጠት ማለት ነው ።) ከዚህ የተሻለ መልካም ትርጉም ስላለው ፕሮቴስታንቶች ይህን አተረጓጐም አይቀበሉም ። ምክንያቱም ይህ ትርጉም ከራሱ ምንም ጉድፈት የሌ

ሰው ከሮማዊ ካቶሊካውያንና ከመሰሎቻቸው የተወረሰ ስለሆነ ነው ። እንደ ብሉይ ኪዳን አወሳሰን የአይሁዶች ፋሲካ በአይሁዶች በመጀመሪያ የአዲስ ዘመን መለወጫ ሳምንት እንዲውል ተደንግጐአል ። ይህም ሳምንት ለእግዚአብሔር የሚታደሱበትና የሚደሰቱበት ሳምንት ነው ። ከዚህም በቀር እግዚአብሔር ከግብጽ እንዳወጣቸውና ሌሎችንም በጐ ነገር እንዳደረገላቸው መለስ ብለው የሚያስቡበት ጊዜ ነበር ። በመሠረቱ መልከምና ነቀፋ የሌለበት ሥነ ሥርዓት ነበር ። ዳሩ ግን ያቀርቡት የነበረው መስዋዕት ኃጢአትን ለዘለዓለም ሊያስወግድ አይችልም ። ይህ የምሳሌ ሥርዓት ከአባት ወደ ልጅ ሲተላለፍ የቆየ ነው ።

ዘጸአት ፲፪ ፥ ፫ - ፲፫ ፥ ፳፩ - ፴፮ ፤ ፲፫ ፥ ፰ ።
ሕዝቅኤል ፵፭ ፥ ፳፩ ።
ዘዳግም ፲፮ ፥ ፩ - ፰ ።
ኢያሱ ፭ ፥ ፲ ።
፩ኛ ሳሙኤል ፳ ፥ ፮ ።
፪ኛ ዜና ፴ ፥ ፲፭ - ፲፮ ።
ኢሳይያስ ፴ ፥ ፳፱ ።

የጌታ እራት አጀማመር ። ያለ ጥርጣሬ የፋሲካ በዓል የተጀመረው ለክርስቶስ መስዋዕትነት ምሳሌ ለመሆን ነበር ።

እርሱ እራሱ በመስቀል ላይ በመሰቀል በእግዚአብሔር ፊት ከዓለም መጀመሪያ እንደተሰቀለ ተቆጠረ ። በሞተም ጊዜ ተፈጸመ ብሎ ጮኸ ። እርሱ የሞተበት ጊዜ የበዓል መጨረሻ ወቅት ነበር ። በዚህ መጨረሻ ጊዜ ለደቀ መዛሙርቶቹ አዲስ ዓይነት የፋሲካ በዓል ሰጣቸው ።

፩ኛ ቆሮንቶስ ፭ ፥ ፯ ፥ ፮ ።
ዮሐንስ ፩ ፥ ፳፱ ፥ ፴፮ ።

ዕብራውያን ፲ ፣ ፲ ፣ ፲፬ ።
፩ኛ ጴጥሮስ ፩ ፣ ፲፰ ፣ ፲፱ ።
ራእይ ፮ ፣ ፺ ፲፫ ፣ ፰ ።

የጌታ እራት ትርጉም ። በመንፈስ ሆኖ የጌታን ሥጋ መብላትና ደሙን መጠጣት ማለት ምንድነው ? በዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ ፮ ጌታ ስለ ሕይወት እንጀራ ሲናገር ሥጋውን ስለ መብላትና ደሙን ስለ መጠጣት በማብራራት ገልጸአል ። በቁጥር ፶፫ ላይ ሐሳቡን በማጠቃለል ሥጋዬን ያልበላ ደሜን ያልጠጣ የዘላለም ሕይወት የለውም በማለት ተናግሮአል ። ይህ መግለጫ የተሰጠው የጌታ እራት ከመሰጠቱ አስቀድሞ ነው ። ስለዚህ ከጌታ እራት ጋር አጣምረን አናስበውም ።

ይህ መንፈሳዊ አድራጐት ነው ። ዳሩ ግን የጌታ እራት የሚታይ ምልክት ነው ። መንፈሳዊ ሥራ ታዲያ ምንድነው ? ለኛ የተቆረሰውን ሥጋ የምንበላውና ለኛ የፈሰሰውን ደም የምንጠጣበት ምክንያት ጌታ ለኛ በመስቀል ላይ ያደረገልንን እያስታወስን በምስጋና የምናደርገው ሥርዓት ነው ። እራሳችን በመስቀሉ ይቅርታ እንደዳን መናገርና መደሰት ከጌታችን ጋር የቀረበ አንድነት ማድረግ ነው ። አንድ ዓይነት ለክርስቶስ የማይስማማ የሥጋ ፍትወት ቢኖርብን ከጌታ እራት ልንሳተፍ አንችልም ። በሌላ መንገድ ደግሞ የልብ ሥራ እንጂ የሰውነት ሥራ ስላልሆነ በማንኛውም በታና ጊዜ ሊደረግ ይቻላል ።

ይህም በጸሎት ፣ በመዝሙርና በሐሳብ ቢሆን መልካም ነው ።

የጌታ እራት እንዴት መንፈሳዊ ምግብ ይሆናል ? መንፈሳዊን ምግብ የምንመገበው በዚህ ብቻ አይደለም ። ይህ በጌታችን የተመረጠ ልዩ ምሳሌያዊ መንገድ ነው ። ለተከታዮቹም ያዘዘው ይህንኑ ነው ። ክርስቶስ ለሐዋር

ያቶቹ ስሙን በምሳሌ ይነግራቸው ነበር። ለእነርሱም መልክም አረኛና የሕይወት ውኃ ነበር። አዲሱ የክርስ ቶስ ማስታወሻ፥ የእንጀራና የወይን እራት ለተሰበረው ሥጋውና ለፈሰሰው ደሙ ምሳሌ እንዲሆን ተነገረ። የውጭ የእንጀራ መብላትና ወይን መጠጣት በውስጥ በሕይወታችን ለሚሠራው የክርስቶስ ሥጋና ደም ምሳሌ ነው።

ጸሎታዊ ሐሳብን በያዘ በመጽሐፍ ቅዱስ ጽሑፍ ደግሞ እንዲህ ተጽፎአል። ውሰድና ብላ፥ (ውጫዊ ሥራ)

ክርስቶስ ስለአንተ እንደሞተ በማስታወስና በልብህ እምነት በምስጋና ተመገበው፥ (ውስጣዊ ሥራ) የክርስ ቶስ ሥጋ በእንጀራው ውስጥ አለ የሚለው የሳክራሜ ንት አባባል ትርጉሙን ፈጽሞ አጥፍቶታል። ከዚህ ሕብስትና ጽዋ የሚመገበው ልብ እንጂ አፍ አይደለም። የውስጣዊው መብል ለልብ ካልታወቀ የውጫዊ አፍ መብላት ብቻ ጥቅም የለውም።

በጌታ በኢየሱስ ባለማመን የጌታ እራት ተካፋይ የሆነ ሰው ሳያምን የሞተ ስለሆነ ምንም አይጠቅመውም። ሬሳን መመገብ አይቻልም። የአንድ ክርስቲያን በልቡ የተሰወረውን በደል ያለመናዘዝ፥ ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ሰዎች እንደገለጸው ከኃጢአት የሚያነጻውን የክርስቶስን ደም እንቢ እንደማለት ያህል ነው። (፩ኛ ቆሮንቶስ ፲፩፥ ፳፰) የጌታን ሥጋ ስለማይለይ ለራሱ ፍርድ ይበላልና፥ ይጠጣልምና። ስለዚህ ከላንት ብዙ ድውያን ደካሞችና ያንቀላፉ አሉ።

የፍቅር መታሰቢያ። የጌታ እራት ለእውነተኛ ተከ ታዮቹ የተሰጠ የፍቅር መታሰቢያ መሆን አለበት። (፩ኛ ዮሐንስ ፩፥ ፫ - ፯ ተመልከት ።) በማቴዎስ ፲፫፥ ፳፬፡ ፴ እንደተጠቀሰው ይህ አሳብ ሁልጊዜ በሙሉ አይ

ሳከም ። የሰው የኃጢአት ተፈጥሮ እንደዚህ ስለሆነ ነው ።)

ዮሐንስ ፮ ፡ ፵፩ - ፶፰ ፤ ፯ ፡ ፴፯ ፤ ፲ ፡ ፯ - ፱ ።
ማርቆስ ፲፬ ፡ ፲፬ - ፲፮ ፡ ፳፪ ።
ማቴዎስ ፳፮ ፡ ፳፮ - ፳፰ ።
ሉቃስ ፳፪ ፡ ፲፱ ፡ ፳ ።
የሐዋርያት ሥራ ፪ ፡ ፵፪ ፡ ፵፮ ፤ ፳ ፡ ፯ ፡ ፲፩ ።
፩ኛ ቆሮንቶስ ፲ ፡ ፲፮ - ፳፩ ፤ ፲፩ ፡ ፳ - ፴፬ ።

## ማስገንዘቢያ ።

የእርሱ እውነተኛ መኖር ። ክርስቶስ ሁለትም ሦስ ትም ሆናችሁ በስሜ በተሰበሰባችሁ ጊዜ እኔ በመኃላ ችሁ አለሁ ብሎ ተስፋ ሰጥቶናል ። የእርሱ መኖር እር ግጠኛ ነገር ነው ። በዚህ አስተሳሰብ ቅዱስ ቁርባንን ስንሳተፍ የእርሱን ከመሐከላችን መገኘት እንረዳለን ።

### ቅዱስ ቁርባንን መቀበል ።

የእንጀራ መቁረስ (የድሮ ስሙ የጌታ እራት ይባ ላል ።) ይህ ዓይነት ሥርዓት እኛ እንደምናደርገው በቤተ ክርስቲያን ብቻ ሳይሆን በማንኛውም ስብሰባ ይደረግ ነበር ። አዲስ ኪዳንም በየትና በምን ዓይነት በታ መደ ረግ እንዳለበት መግለጫ አይሰጠንም ። በመጀመሪያ ጊዜ እንጀራውንና ወይኑን በምሽት ተመገቡ ። ከዚያ ቆይ ተው የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች እንደአስፈለጋቸው በቤተ ክርስቲያን ሕግ ደነገጉ ።

ሉቃስ ፳፬ ፡ ፩ ፡ ፲፫ ፡ ፴ ፡ ፴፩ ፡ ፴፮ ።
ዮሐንስ ፳ ፡ ፲፱ ፡ ፳፮ ።
የሐዋርያት ሥራ ፳ ፡ ፯ ።
፩ኛ ቆሮንቶስ ፲፮ ፡ ፪ ።

የጌታ መመለስ ። በፋሲካ እራት ጊዜ አይሁዶች የደነገጉት ልማድ አለ ። ይኸውም የፋሲካ እራት በሚበ

ሉበት ጊዜ ጠረጴዛ አጠገብ ባዶ ወንበር ያስቀምጣሉ ፤ ምክንያቱም መሲህ በፋሲካ ጊዜ ተመልሶ ይመጣል የሚል ሐሳብ ስላላቸው ነው ።

## ፵ኛ ። ፍቅር ።

መጽሐፍ ቅዱስ ፍቅር ከፍተኛው የእግዚአብሔር ባሕርይ ነው ይላል ። ኃጢአት የዓለም በሽታ የሆነ የፍቅር ተቃዋሚ ነው ። ፍቅር ክርስቶስ ካለው ሕይወት የመጀመሪያውና ታላቁ ነው ። ኃጢአት የሰይጣን ክፍል ነው ። እውነተኛ ፍቅር ለፍጥረታዊ ሰው አይታወቅም ። ለምሳሌ ለጠላቶቻችን እንኳን እስከመጸለይ የሚያደርሰን የፍቅር ባሕርይ ነው ። (ማቴዎስ ፭ ፥ ፵፬)

ፍጹም ፍቅር በመጽሐፍ ቅዱስ ተገልጾአል ። እንዲህ ያለውም ፍቅር ክርስቶስን በመምሰል በክርስቶስ አዲስ ሕይወትን ባገኙ ሰዎች ውስጥ ይኖራል ።

ይህንን ባሕርይ መጽሐፍ ቅዱስ በሚከተለው ዓይነት ሁኔታ ይገልጸዋል ።

| | |
|---|---|
| ፍቅር ታጋሽ ናት ። | ፩ኛ ቆሮ. ፲፫ ፥ ፬ ። |
| ፍቅር የዋህ ናት ። | ፩ኛ ቆሮ. ፲፫ ፥ ፬ ። |
| ፍቅር አትታበይም ። | ፩ኛ ቆሮ. ፲፫ ፥ ፬ ። |
| ፍቅር አትለግምም ። | ፩ኛ ቆሮ. ፲፫ ፥ ፬ ። |
| ፍቅር አትመካም ። | ፩ኛ ቆሮ. ፲፫ ፥ ፬ ። |
| ፍቅር አትቀናም ። | ፩ኛ ቆሮ. ፲፫ ፥ ፬ ። |
| ፍቅር አትሰስትም ። | ፩ኛ ቆሮ. ፲፫ ፥ ፭ ። |
| ፍቅር አትበሳጭም ። ቂም አትይዝም ። | ፩ኛ ቆሮ. ፲፫ ፥ ፭ ። |

ፍቅር በሌሎች ስሕተት አትደሰትም ።
፩ኛ ቆሮ. ፲፫ ፥ ፮ ።

ፍቅር ትንንሽ ስሕተቶችን አትመለከትም ።
    ፩ኛ ቆሮ. ፲፫ ፥ ፯ ።
ፍቅር እውነትን ለማወቅ ትጓጓለች ።
    ፩ኛ ቆሮ. ፲፫ ፥ ፯ ።
    ታምናለች ።
ፍቅር ሁልጊዜ ተስፋ አላት ።
    ፩ኛ ቆሮ. ፲፫ ፥ ፯ ።
    አትጨነቅም አታጉረመርምም ።
ፍቅር በፍጹም አትወድቅም ።
    ፩ኛ ቆሮ. ፲፫ ፥ ፰ ።
ፍቅር ሁሉን ትሰጣለች ። ዮሐ. ፲፭ ፥ ፲፫ ።
ፍቅር ፍርሃትን ታስወግዳለች ።
    ፩ኛ ዮሐ. ፬ ፥ ፲፰ ።
ፍቅር ጐረቤትን ከመጉዳት ትጠነቀቃለች ።
    ሮሜ ፲፫ ፥ ፲ ።
ፍቅር ያልከፈለችው ዕዳ ይቅርታም ያልተቀበለ
    ችበት በደል የላትም ። ሮሜ ፲፫ ፥ ፰ ።
ፍቅር ታገለግላለች ። ገላትያ ፭ ፥ ፲፫ ።
ፍቅር ዓለማዊ አይደለችም ።
    ፩ኛ ዮሐ. ፪ ፥ ፲፭ - ፲፯ ።
ፍቅር ከእግዚአብሔር ናት ። ፩ኛ ዮሐ. ፬ ፥ ፯ ።
ፍቅር በእውነት ክርስቶስን መሳይ ናት ።
    ኤፌሶን ፫ ፥ ፲፱ ።

## ፍቅር እንዴት ይገኛል ?

በቃላትና በስብከት ብቻ የሚገኝ አይደለም ።
    ፩ኛ ቆሮንቶስ ፲፫ ፥ ፩ ።
ከቃልህ ይልቅ ሥራህ የበለጠ እየጮኸ ይናገ
    ራል ። ፩ኛ ቆሮንቶስ ፲፫ ፥ ፩ ።
በማሰብና በትምህርት አናገኛትም ።
    ፩ኛ ቆሮንቶስ ፲፫ ፥ ፪ ።

የጠበቀ የሃይማኖት እምነት አይጠቅምም ።

፩ኛ ቆሮንቶስ ፲፫ ፣ ፫ ።

ገንዘብን ሁሉ መስጠት ፍቅርን አይገዛትም ።

፩ኛ ቆሮንቶስ ፲፫ ፣ ፫ ።

በእሳት መቃጠል ፍቅርን አይገዛትም ።

፩ኛ ቆሮንቶስ ፲፫ ፣ ፪ ።

ልብ በክርስቶስ ካልተገደደ ጥሩ ሥራና እስኪያ ልብም መድከም ጥቅም የለውም ። ቲቶ ፫ ፣ ፭ ። ሰው ዳግመኛ ካልተወለደ ይህችን ፍቅር ለማ ወቅ አይችልም ። ይኸንንም ሕይወት ለመኖር አይችልም ።

፩ኛ ዮሐንስ ፬ ፣ ፯-፲ ፤ ዮሐንስ ፫ ፣ ፫ ።

ይህ አዲስ በሕርይ ለእያንዳንዱ አማኝ በጸጋ ይታ ደለዋል ። እያንዳንዱም አማኝ በመንፈስ ቅዱስ በየጊ ዜው ያድጋል ። አንድ ፍሬ ሳትታወቅ በዛፍ ቅርንጫፍ እንደምታድግ ፣ እንዲሁም አማኝ በሆነ ሰው ሕይወት ውስጥ ከመንፈስ ፍሬዎች ዋና የሆነች ፍቅር ሳትታወቅ በልቡ ታድጋለች ።

አንድ ፍሬ በቅርንጫፍ ላይ ብትታሰር ትደርቃ ለች ። እንደዚሁም ሁሉ ይህ ክርስቲያን መሳይ ሕይወት በገዛ ራሱ የሚሠራ አይደለም ። ጳውሎስ በመልእክቱ ፍቅርን ለመፈለግ ተሽቀዳደሙ ይላል ። (፩ኛ ቆሮንቶስ ፲፬ ፣ ፩)

፩ኛ ዮሐንስ ፬ ፣ ፳ ፣ ፲፮ ።

ዮሐንስ ፫ ፣ ፲፮ ።

ሮሜ ፰ ፣ ፴፭ ፣ ፴፰ ፣ ፴፱ ፤ ፭ ፣ ፭ ።

፪ኛ ጢሞቴዎስ ፩ ፣ ፲፫ ።

ኤፌሶን ፪ ፣ ፬-፯ ፤ ፭ ፣ ፪ ።

፪ኛ ቆሮንቶስ ፲፪ ፣ ፩ ፣ ፴፩ ፤ ፲፫ ፣ ፲፫ ።

ዮሐንስ ፲፫ ፣ ፴፭ ።

## ፵፩ኛ ። የወንጌላውያን ጥሪ ።

ወንጌላዊ ለመሆን መጠራት ፥ በተለወጠው ሕይወት የሚመጣ ነው ። አባቴ እንደላከኝ እኔም ደግሞ እናንተን እልካችኋለሁ የሚለውን ዓላማ ሳይለውጥ ነው ።

በእውነተኛ ራእይ የዓለምን ጥፋት ተመልክቶ ወደ ዚህ ምድር በመምጣት የሰላም ወንጌልን እንዳስተማረ ሁሉ እኛም በእርሱ እግር ዱካ ተከትለን ለመሄድ ፈቃደኛ መሆን ነው ። እርሻው ይህ ዓለም ነው ።

ለወንጌላዊነት አገልግሎት ወደ ውጭ አገር የመሄድ እድል የሚያጋጥማቸው ጥቂቶች ናቸው ። ጥሪው ለሁሉ ክርስቲያን ስለሆነ ለሄዱትና ለቀሩት አስፈላጊነቱ እኩል ነው ። እውነተኛውን ጥሪ መጽሐፍ ቅዱስ ይገልጻል ። የዓለም ጣዕም የማይበግራቸው በወንጌላዊነት አገልግሎት ላይ ያሉ ብዙ ምስክሮች አሉ ።

የሰውን ልብ የሚሞላው አዲሱ በክርስቶስ የተገኘ ተፈጥሮ ነው ። እነዚህ የሄዱት እግዚአብሔር ማን ይሄድልኛል ሲል የሰሙ ናቸው ። እነርሱም አምላክ ሆይ ፥ ባርያህ ይሰማልና ወደፈቀድክበት ላከኝ ያሉት ናቸው ።

ኢሳይያስ ፮ ፥ ፩ ፣ ፭ ፣ ፰ ።
ዘጸአት ፪ ፥ ፲፩ ፤ ፬ ፥ ፲፪ ።
ፊልጵስዩስ ፪ ፥ ፭ ፣ ፮ ።
ዮሐንስ ፫ ፥ ፲፮ ፣ ፲፯ ፤ ፬ ፥ ፴፬ ፣ ፴፭ ።
ምሳሌ ፳፬ ፥ ፲፩ ።
ገላትያ ፩ ፥ ፲፭ ፣ ፲፮ ።
፩ኛ ቆሮንቶስ ፱ ፥ ፲፮ ።
አሞጽ ፯ ፥ ፲፬ ፣ ፲፭ ።
ማቴዎስ ፬ ፥ ፲፰ ፣ ፲፱ ፤ ፱ ፥ ፱ ።
ዘጸአት ፴፪ ፥ ፴፪ ፤ ሙሴ ስለ ወንድሞቹ ከሕይወት መጽሐፍ እንዲፋቅ ወደደ ።

ሮሜ ፱ ፣ ፫ ። ጳውሎስ ለሥጋ ዘመዶቹ እን
ዲረገም ፈቀደ ።
ኤርምያስ ፩ ፣ ፯ ፣ ፰ ።
፩ኛ ቆሮንቶስ ፪ ፥ ፩ - ፱ ።
ሉቃስ ፬ ፣ ፲፰ ።
ዮሐንስ ፳ ፣ ፳፩ ።

የወንጌላዊነትን ጥሪ ስንፈልግ ስለ ስሕተት ጥሪዎች መጠንቀቅ አለብን ። የስሕተት ጥሪ የማያስፈልጋቸውን ሰዎች ይጠራቸዋል ። ባልተጠራው ሰው ዘንድ ለመንፈሳዊ ተግባር ለተሰበሰቡት ከመስበክ ይልቅ ከእግዚአብሔር ጋር መገናኘት በጣም ከባድ ይሆንበታል ።

ሀ) የሰው ጥሪ ።

የሰው ፍላጐት ጥሪውን ያመለክተዋል ። ለመስበክ ነው እንጂ ለማሳመን አልተጠራንም ። ዋናው ጥሪያችን በትምህርት ፣ በንግድ ወይም በሕክምና የሆነ እንደሆነ ባልተጠራንበት መስክ መሠማራት ሥራችንን ከንቱ ያደርገዋል ።

ለ) አዲስ ነገር እንይ ወዳለው ጥሪ መሄድ ።

ይህ ዓለምን የማየት ጥሪ ነው ። በመፈለግ መጠባበቅ ደግሞ የጉብዞች ጥሪ ነው ። (ጴጥሮስ በውኃው ላይ ሄደ ፤ ነገር ግን ኋላ ጥገዱ ሊውጠው ቀርቦ ነበር ።)

ሐ) የሰው መስል ጥሪ ።

ወንጌላዊ መሆን የተለመደ ነው ። ወንጌላውያን ሁሉ የክርስቲያን ግኀበር አባሎች እንደመሆናቸው መጠን ክርስቲያን ወንጌላውያን ሆኑ ። ነገር ግን የተባለውን አስታውሱ ። ሰው ባለበት ቦታ ወንጌላዊ ከመሆን እንዲያቆም ሰይጣን ወደ ሌላ የወንጌላዊነት ሥራ ይሰደዋል ። የሌላውን ሥራ ብቻ መቅሰም ጥቅም የለውም ።

መ) እራስን የመካድ ጥሪ ።

በጸጋ ያለውን የደኅንነት ሥራ ቸል በማለት ውጫዊ ሕይወታቸውን ለእርሱ በመስጠት በሥራቸው ለመዳን ይህንን ተጋድሎ ይተኩበታል ። ከሌሎቹ ተለይቶ መኖር ሰውዮውን ወደዚህ ዓይነት ሕይወት ይመራው ይሆናል ።

አንድ ቀንም እምላክ ሆይ ፥ ሁሉን ነገር ለአንተ ተውኩ ብሎ ሲጮህ መልሱ አላውቅህም የሚል ይሆን በታል ።

ሠ) ለራስ የመፈለግ ጥሪ ።

በዚህ ክፍል አንዳችን በቀኝህ አንዳችን በግራህ እንቀመጥ ወይ ? የሚሉ ናቸው ።

እነዚህ የዓለምን ታላቅነት የሚፈልጉ ናቸው ። ይኸንንም በወንጌላዊነት አቋማቸው ወዲያው ስለሚያገ ኙት ነው ።

እኛ ተግባራችን ንጹሕ ቢሆን እርሱ ነው እንጂ እኔ ማለት አያስፈልገንም ።

## ፴፪ኛ ። ዳግም ምጽዓት ።

ይኸን ስንል የክርስቶስን የዳግመኛ ጊዜ መምጣት ሁናቴ ስንገልጽ ነው ። ይህ ገና ለወደፊት የሚሆን ነው ። ከዚህም በቀር መጽሐፍ ቅዱስን በትሕትና ብናነብ በበ ለጠ የክርስቶስን ዳግመኛ መምጣት በመንፈሱ ገላጭነት ለመረዳት እንችላለን ።

ነገር ግን ሰው በሚተረጉመው መንገድ ሐሳብን ማሳረፍ መልካም አይደለም ። በግሪክኛ ፓሩሲያ ፣ አፓ ስካሉፕሲስ ፣ አፒፋንያ የሚለው ቃል ትርጉም ክርስቶስ በመታየት ዳግመኛ መምጣቱን ያስረዳል ።

የክርስቶስ ወደ ዓለም መምጣት እንደሚታይ እን ዴት እናውቃለን ? በብሉይ ኪዳን ውስጥ ክርስቶስ መጀ

መሪያ እንዴት እንደሚመጣ በመሰቀሉም እንደሚሞት ይገልጻል ። ነገር ግን እንዴት እንደሚመጣ ወይም ምን እንደሆነ ለማየት የአብዛኛዎቹ ዓይኑ ልበና ታውሮ ነበር ። መጽሐፍ ቅዱስ እንደ መጀመሪያው ሁለተኛ መምጣቱን ይገልጻል ። አመጣጡም በሥልጣንና በትልቅ ክብር ይሆናል ። ክርስቶስ ስለ ራሱ ዳግመኛ መምጣት ከሃያ ለሚበልጥ ጊዜ ተናግሯል ። በአዲስ ኪዳን ውስጥ ስለ ዳግም ምጽዓት ከሁለት መቶ ጊዜ በላይ ተጽፏል ። በመጀመሪያ ምጻቱ እንደሚመጣ ተስፋ ሰጥቶ እንደፈጸመ ፣ እንዲሁ ደግሞ የሁለተኛ ጊዜ የመምጣቱን ተስፋ ይፈጽማል ። ይህ ደግሞ በሐዋርያት ሥራ ፩ ፣ ፲፩ና በ፩ኛ ተሰሎንቄ ፬ ፣ ፲፬ የሰፈረው ጽሑፍ ከቀሩት በግልጽ ስለ ዳግመኛ ምጻቱ ያስረዳል ።

መዝሙር ፻፩ (፻፪) ፣ ፩ ፣ ፯ ፣ ፲፫ - ፲፰ ።
የሐዋርያት ሥራ ፩ ፣ ፲፩ ።
ማቴዎስ ፳፬ ፣ ፳፩ - ፴ ።
ዮሐንስ ፲፬ ፣ ፫ ።
ሮሜ ፲፩ ፣ ፳፮ ፣ ፳፯ ።
፩ኛ ቆሮንቶስ ፩ ፣ ፯ ።
ፊልጵስዩስ ፫ ፣ ፳ ፣ ፳፩ ።
፩ኛ ተሰሎንቄ ፩ ፣ ፱ ፣ ፲ ፤ ፬ ፣ ፲፬ ፤ ፫ ፣ ፲፪ ፣
፲፫ ፤ ፬ ፣ ፲፯ ፣ ፲፰ ።
ቲቶ ፪ ፣ ፲፫ ።
ዕብራውያን ፱ ፣ ፳፰ ።

ከመመለሱ በፊት አንዳንድ ነገሮች ይፈጸማሉ ፤ እነዚህም ነገሮች በዓለም ላይ ይደረጋሉ ።

ሀ) በእግዚአብሔር ፊት አጭር የሆነው ጊዜ ምንም በኛ አስተያየት ረጅም ቢመስል ጌታ ከመምጣቱ በፊት ያልፋል ። በመጽሐፍ ቅዱስ የተገለጸው ዋናው ትእዛዝ የእርሱን ዳግመኛ ምጻት በዝግጅት እንድንጠ

ብቅ የሚያስረዳ ነው ።

ማቴዎስ ፳፬ ፥ ፯ - ፰ ፣ ፴፰ ፤ ፳፭ ፥ ፭ ፥ ፲፱ ።

ለ) አሁን ተበትነው የምናያቸው አይሁዶች ከመጥፋት የሚድኑት በመጨረሻ ፓለስቲን ወደሚባለው አገራቸው ሲመለሱ ነው ። በዚህ ትንቢት ምክንያት በአሁኑ ዘመን አይሁዶች ወደ አገራቸው ተመልሰው መንግሥት አቁመዋል ።

ዘዳግም ፴ ፥ ፫ ።
ኢሳይያስ ፲፩ ፥ ፲ - ፲፪ ፤ ፳ ፥ ፱ ።
ኤርምያስ ፴ ፥ ፲፩ ፣ ፲፰ ፣ ፴፩ ፤ ፲ ፥ ፲፫ ።
ሕዝቂኤል ፴፯ ፥ ፳፩ - ፴፯ ፤ ፴፯ ፥ ፩ - ፲፩ ።
ሉቃስ ፳፩ ፥ ፳፱ ።
ሮሜ ፲፩ ፥ ፳፭ ።

ሐ) ወንጌል በዓለም ሁሉ መሰበክና መታወቅ አለበት ። ዘመናውያን አታሚዎችና በራዲዮን ተናጋሪዎች ይህን አድራጐት አነስተኛ ተግባር ያደርጉታል ። በ፲፱፻፷፯ ዓ. ም. የተባበረው የመጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር ፫ ሚልዮን ፻፳ ሺ ፳፱፻፵፩ መጻሕፍት አሳትሟል ። በዚህ ሁሉ መጽሐፍ መሰራጨት የጥሪው ትእዛዝ ስላልተፈጸመ ለጥሪው ፍጻሜ የወንጌላውያን መጠራት አስፈላጊና አስቸኳይ ነው ።

ማርቆስ ፲፫ ፥ ፲ ፤ ማቴዎስ ፳፬ ፥ ፲፬ ።

መ) በክርስቶስ ስም ብዙ ሃይማኖቶች ይነሳሉ ። ብዙም ሐሰተኞች ነቢያት ይመጣሉ ። በለፉት መቶ ዓመታት ብዙ የክህደት ትምህርቶች በዝተው ነበር ።

ለምሳሌ ፤ ሞርማኒዝም ።
ራሳሉዝም ።
ክርስቲያ ደልፋኒስም ።
ክርስቲያን ሳይንስ ።
የሚባሉት የከሐዲያን ትምህርቶች ናቸው ።

ማቴዎስ ፳፬ ፡ ፭ ፡ ፲፩ ፡ ፳፬ ።
ሉቃስ ፲፯ ፡ ፳፫ ።
፪ኛ ጴጥሮስ ፪ ፡ ፩ ፡ ፪ ።
፪ኛ ተሰሎንቄ ፪ ፡ ፫ ።

ሠ) አሕዛብ በኢየሩሳሌምና በፓለስቲን ላይ የነበራቸው የመግዛት ሥልጣን ይቋረጣል ። ይህ እንደሚሆን የሚያረጋግጥልን የኢየሩሳሌም ከቁርኰች እጅ ነፃ መውጣት ነው ።

ሉቃስ ፳፩ ፡ ፳፬ ።

በመመለሻው ጊዜ በዓለም ብዙ ነገሮች ይደረጋሉ ።

ሀ) ቀድሞ ተሰምተው የማይታወቁ አደጋዎች ለምሳሌ ያህል እንደ የምድር መንቀጥቀጥና መለያየት ፣ ደግሞም አምላክ እንዳለ አለማመንና የሃይማኖት መሳደድ ጭምር በዓለም ይበዛሉ ።

ዳንኤል ፲፪ ፡ ፱ ፡ ፲ ።
ኢዩኤል ፪ ፡ ፴፩ ።
ሶፎንያስ ፩ ፡ ፲፬ – ፲፰ ።
ማቴዎስ ፳፬ ፡ ፱ ፡ ፲ ፡ ፳፩ ።
ሉቃስ ፳፩ ፡ ፲፩ ፡ ፳፭ ።
፪ኛ ጢሞቴዎስ ፫ ፡ ፩ – ፭ ።

ለ) በምድር የሚታየው የክርስቲያን ማኅበር ደክሞ ከዓለም ጋር ይተባበራል ። ደግሞ በዓለም ሁሉ ከክርስቶስ ተለይቶ መውደቅ አለ ።

የሕዝብ መሪዎች የነበሩ (ፈሪሳውያን) በመጀመሪያ ምጽዓት ሳይዘጋጁ በመቀዝቀዝ ተኝተው እንዳገኘቻቸው ፤ በዳግም ምጽዓትም የክርስቲያን ማኅበርተኞች ተዘጋጅተው በመጠባበቅ ፋንታ ተኝተው ይገኛሉ ።

ማቴዎስ ፳፬ ፡ ፫ ፡ ፬ ፡ ፱ ፡ ፲፪ ፡ ፳፬ ፡ ፵፬ ፤
፳፭ ፡ ፩ – ፲፫ ።
ሉቃስ ፲፯ ፡ ፳፮ ፡ ፳፯ ፡ ፴ ፤ ፲፰ ፡ ፰ ፤

፳፩፡ ፴፬፡ ፴፮።

ማርቆስ ፲፫፡ ፴፯።

፩ኛ ተሰሎንቄ ፭፡ ፩-፯።

፪ኛ ጴጥሮስ ፫፡ ፫፡ ፬።

ራእይ ፫፡ ፲፩፡ ፲፰።

ሐ) በሚመጣው ጊዜ ይሆናል ተብሎ ይገመት የነበረው ነገር አሁን በዓለም ይደረጋል።

ሉቃስ ፳፩፡ ፳፭፡ ፳፮።

መ) አንዳንድ የእርሱን መምጣት በዓለም ውስጥ ሆነው የሚጠባበቁ ክርስቲያኖች ከወገን ሁሉ ተለይተው የተመረጡ ይሆናሉ።

ዳንኤል ፲፪፡ ፱ ፲።

ማቴዎስ ፳፭፡ ፩-፫፡ ፳

ሉቃስ ፳፩፡ ፴፭፡ ፴፮።

ሠ) ቁጥራቸው የበዛ አይሁዶች ወደ አገራቸው ተመልሰው ይገኛሉ።

ኢሳይያስ ፲፩፡ ፲፩፡ ፲፪።

ሕዝቅኤል ፴፯፡ ፲፩ ፲፪፡ ፳፩፡ ፳፪።

ረ) ታላቅ ብርቱ ንጉሥ ይነሣል። እርሱም ምናልባት በአውሮፓ ወይም በዚያ አካባቢ ከትርፉ አገር ተነስቶ ዓለሙን ሁሉ በሥልጣኑ ይገዛል። ስሙም ፦ አውሬ፡ የኃጢአት ሰው፡ ወይም ትንሹ ቀንድ ይባላል። (ዳንኤል ፯፡ ፰) በሃይማኖቱ ብዙ ተከታዮች ያሉትና የተፈራ ሰው ይሆናል። ድል ከነሣ በኋላ ምናልባት ፓስቲንን ለመውሰድ ያስብ ይሆናል። ከዚህም በቀር ይህ ንጉሥ ከወደቀው ከክርስቲያን መሪ ማለት ከሐሰዊ መሲህ ጋር በመስማማት አንድ ይሆናል ተብሎ ይገመታል።

ዳንኤል ፯፡ ፳ ፲፩፡ ፴፯-፵፭ ፲፪፡ ፩።

ማቴዎስ ፳፬፡ ፲፬-፲፯።

፪ኛ ተሰሎንቄ ፪፥፫-፲፪።

ራእይ ፲፫፥፫-፲፰፤ ፲፱፥፲፯-፳፩።

ሰ) ለመጨረሻ ጊዜ በዓለም ጦርነት ይሆናል። በእግዚአብሔር ላይ ጦርነት ለማድረግ በአይሁዶች መከከል ፓለስቲንን ይከባል። ይህም ጦርነት አርማጌዶን ይባላል። መጽሐፍ ቅዱስ አሕዛብ ክፉ አሳብ ያስባሉ ይላል።

ጠባቂ የሌላት የተከማቸችቱ የፓለስቲን ሀብት ትወድማለች። አይሁዶችም ሲጨንቃቸው ወደ ክርስቶስ ይመለሳሉ።

ሕዝቅኤል ፴፰፥፰-፲፪፥፲፮፥፳፩፥፳፪።

ኢዩኤል ፫፥፩፥፪፥፱-፲፩፥፲፬።

ዘካርያስ ፲፪፥፩-፱፤ ፲፬፥፩-፱።

ሮሜ ፲፩፥፳፭፥፳፮።

ራእይ ፲፯፥፲፬፥፲፯።

የጌታ ምጽዓት ሁለት አስተያየት አለው፤ ሁኔታውም አንድ አይደለም። በሌሊት እንደሚመጣ ሌባ ይመጣል። ይህም ሳይታሰብ መጥቶ ቅዱሳኖችን ወደ አየር እንደሚነጥቃቸው ሲያመለክት ነው። ከዚህም በኋላ በታላቅ ግርማ ቅዱሳንን መልሶ ወደ ምድር ያመጣቸዋል። የመጀመሪያውን እርምጃ መነጠቅ እንለዋለን። መነጠቅ ወደ ምድር ዳግመኛ ከመውረዱ በፊት የሚወስደው እርምጃ ነው። በዚህም ጊዜ የአርማጌዶን ጦርነት ይከሄዳል። በዳግም ምጻት የጌታችንና የቤተ ክርስቲያን ክብር ይታያል።

ሙሽራይቱም ከነገድና ከቋንቋ ማለት ከዓለም ሕዝብ መኃል ተጠርታ በመጨረሻ መነጠቅ ድል ትነሳለች።

መነጠቅ።

፩ኛ ቆሮንቶስ ፲፭፥፶፩-፶፫።

፩ኛ ተሰሎንቄ ፬፥፲፫፥፲፯።

ሉቃስ ፲፯ ፥ ፳፬ ፣ ፴፬ - ፴፯ ።

ወደ ምድር መምጣቱ ።

፩ኛ ተሰሎንቄ ፫ ፥ ፲፫ ።

ዘካርያስ ፲፬ ፥ ፬ ፣ ፭ ።

ዳግመኛ መምጣቱ ።

ማቴዎስ ፳፬ ፥ ፳፯ - ፴፩ ፣ ፴፱ ።

ሉቃስ ፲፪ ፥ ፴፱ ፣ ፵ ።

ማቴዎስ ፳፭ ፥ ፮ ፣ ፲፫ ፣ ፴፩ ፣ ፴፪ ።

ሉቃስ ፳፩ ፥ ፳፯ ፣ ፳፰ ፣ ፴፬ ፣ ፴፮ ።

የሐዋርያት ሥራ ፩ ፥ ፱ ፣ ፲ ፣ ፲፩ ።

ቆላስይስ ፫ ፥ ፬ ፤ ፩ኛ ጴጥሮስ ፭ ፥ ፬ ።

፩ኛ ዮሐንስ ፪ ፥ ፳፰ ።

የሺህ ዓመት ዘመን ።

ራእይ ፳ ፥ ፩ - ፬ ፤ ኢሳይያስ ፲፩ ፥ ፮ - ፱ ።

ኤርምያስ ፳፫ ፥ ፭ ፣ ፮ ፤ ዘካርያስ ፲፬ ፥ ፱ ።

የክፉት ኃይል መጥፋት ።

ራእይ ፳ ፥ ፯ - ፲ ።

መጨረሻው ፍርድና የዚህ ዓለም ፍጻሜ ።

ዕብራውያን ፩ ፥ ፲ - ፲፪ ።

፪ኛ ጴጥሮስ ፫ ፥ ፲ - ፲፫ ።

ራእይ ፳ ፥ ፲፩ - ፲፭ ።

አዲሱ ሰማይና ምድር ።

ራእይ ፳፩ ፥ ፩ ፣ ፬ ።

የእግዚአብሔር ሁሉ በሁሉነት ።

፩ኛ ቆሮንቶስ ፲፭ ፥ ፳፬ - ፳፰ ።

የመጨረሻው ጸሎት ።

ራእይ ፳፪ ፥ ፳ ።

አዎን ጌታ ኢየሱስ ና ።